Addis Ababa University
አዲስ፡አበባ፡ዩኒቨርሲቲ
SEEK WISDOM, ELEVATE YOUR INTELLECT AND SERVE HUMANITY !


የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር


# የመርሐ ቤቴ ልጃገረዶች የፉሲካ ጨዋታ ክዋኔ እና ፋይዳ

በ


ታደሰ አዳነ ትኩ


ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


ጥቅምት 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የመርሐ ቤቴ ልጃገረዶች የፉሲካ ጨዋታ ክዋኔ እና ፋይዳ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ

በ

ታደሰ አዳነ ትኩ

አማካሪ

የወንድወሰን አውላቸው (ዶ.ር)

ጥቅምት 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

### የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ፡- የወንድወሰን አውላቸው (ዶ/ር) ፊርማ ---------------------

የውጪ ፈታኝ፡- ዘላለም ተፈራ (ዶ/ር) ፊርማ --------------------

የውስጥ ፈታኝ፡- ዓለሙ ካሣዬ (ዶ/ር) ፊርማ --------------------

## ማረጋገጫ

**የመርሐ ቤቴ ልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ ክዋኔ እና ፋይዳ** በሚል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር፣ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብሁት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምሁባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢ የሆኑና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም--------------------------- ፊርማ------------ ቀን--------------------------

# ምስጋና

ለጥናቴ መሳካት የተለያዩ ሰዎችና ተቋማት በተለያየ መልኩ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ የመጀመሪያው በየትኛውም ጊዜ እና ቦታ ያለመሰልቸት ጥናቴን በማረም፣ በማስተካከል፣ አስተያየት በመለገስ፣ አቅጣጫ በማመላከት ላደረጉልኝ ድጋፍ እና ሙያዊ እገዛ አማካሪዬን ዶክተር የወንድወሰን አውላቸውን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ ሙሉ ጊዜና ደመወዝ በመፍቀድ እንድማር እድሉን የሰጠኝን የባህልና ስፖርት ሚኒስቴርን እና በመርሃ ግብሩ እንድማር እድሉን ከመስጠት ባሻገር ለጥናቱ ማካሄጃ የሚሆን መጠነኛ የገንዘብ ድጋፍ ያደረገልኝን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን አመሰግናለሁ፡፡ እንድማር በማበረታታትና አዎንታዊ ግፊት በማድረግ ከጅማሬ እስከ ፍጻሜ ድጋፏ ያልተለየኝን ባለቤቴን ወ/ሮ አብነት ኢሳይያስን እጅግ አመሰግናለሁ፡፡

መረጃ ለመሰብሰብ የሄድሁባቸውን ቦታዎች ሁሉ ያለመታከት አስቀድሞ በማመቻቸት፣ የረዱኝንና መረጃ የሰጡኝን ሰዎች በማገናኘት፣ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዳገኝ በማገዝና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን ሁሉ አቅማቸውና ሁኔታው በፈቀደው መጠን ላደረጉልኝ ድጋፍ የመርሐ ቤቴ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃላፊዎችና ባለሙያዎችን አመሰግናለሁ፡፡ በተለይም ወ/ሮ የማሪያምወርቅ በላይሁን እና ወ/ሮ ህይወት ታደሰ መረጃ ለመሰብሰብ በተጓዝሁባቸው ቦታዎች ሁሉ አብረውኝ በመጓዝ ለአደረጉት እገዛ ከፍያለ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡ በተጨማሪም የሰሜን ሸዋ ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ፣ የዞኑ የመንግስት ኮሚንኬሽን መምሪያ፣ የመርሐ ቤቴ ወረዳ የመንግስት ኮሚንኬሽን ጽ/ቤት እና የወረዳው እቅድና ልማት ጽ/ቤት ላደረጉልኝ ትብብርና ለሰጡኝ መረጃ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በመስክ ቆይታዬ መረጃ በመስጠት ጥናቱ እንዲሳካ ቀና ትብብር ያደረጉ በአባሪው ክፍል ስማቸው የተዘረዘረው መረጃ አቀባዮቼና የየቀበሌዎቹ አስተዳደር አካላት ያለእነሱ ድጋፍ ይህ ጥናት ሊሳካ አይችልም ነበርና ላደረጉልኝ እገዛ አመሰግናለሁ፡፡

## ማውጫ

ምስጋና ........ i
ማውጫ ........ ii
የፎቶግራፍ /ምስል/ ማውጫ ........ v
ሙዳዬ ቃላት ........ vi
የቃላት አጠቃቀም ጥቁምታ ........ vii
አጠቃሎ ........ viii
ምዕራፍ አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 4
1.3. የጥናቱ ዓቢይና ዝርዝር ዓላማ ........ 5
1.3.1 ዓቢይ (ዋና) ዓላማ ........ 5
1.3.2 ንዑሳን ዓላማዎች ........ 5
1.4. የጥናቱ የሚመልሳቸው የምርምር ጥያቄዎች ........ 6
1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት/ፋይዳ ........ 6
1.6 የጥናቱ ወሰን ........ 6
1.7 የአጠናን ሥነ ምግባር ደንብ ........ 7
1.8 ያጋጠሙ ችግሮች፣ የተወሰዱ መፍትሔዎችና የመስክ ገጠመኝ ........ 9
1.8.1 ያጋጠሙ ችግሮች፣ ........ 9
1.8.2 የተወሰዱ መፍትሔዎች ........ 10
1.8.3 የመስክ ልምድ እና ገጠመኝ ........ 12
ምዕራፍ ሁለት ........ 18
ክለሳ ድርሳናት ........ 18
2.1 ጽንሰ ሃሳባዊ ዳሰሳ ........ 18
2.1.1. ቡድን (ፎክ ቡድን) ........ 18
2.1.2. ሃገረሰባዊ ልማድ እና ጨዋታ ........ 20
2.1.3 ክብረ በዓል እና በዓለ ትንሳኤ ........ 24
2.2. ንድፈ ሃሳባዊ ማሕቀፍ ........ 26
2.2.1. ክዋኔያዊ ንድፈ ሃሳብ (Performance Theory) ........ 27
2.2.2. ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ (Functional Theory) ........ 29
2.3. የቀደምት የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 32
ምዕራፍ ሶስት ........ 37
የአጠናን ዘዴ ........ 37

3.1 የጥናቱ ናሙና አመራረጥ ስልት .......................................................... 37
3.1.1 የመረጃ ሰጪዎች ንሞና .......................................................... 38
3.1.2 የጥናት ቦታ አመራረጥ .......................................................... 39
3.2 መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች .......................................................... 40
3.2.1 ምልከታ .......................................................... 40
3.2.2 ቃለ መጠይቅ .......................................................... 41
3.2.3 ተተኳሪ የቡድን ውይይት .......................................................... 43
ምዕራፍ አራት .......................................................... 45
የመርሐ ቤቴ ወረዳ አጠቃላይ ገጽታ .......................................................... 45
4.1 መልክዓ ምድራዊ ገጽታ .......................................................... 47
4.1.1 የመሬት አቀማመጥና የአየር ሁኔታ .......................................................... 47
4.1.2 የመሬት አጠቃቀምና መተዳደሪያ .......................................................... 48
4.2 የህዝብ ብዛት፣ ቋንቋና ኃይማኖት .......................................................... 49
4.3 መሰረተ ልማት .......................................................... 49
4.4 የባህልና የተፈጥሮ የመስህብ ሐብቶች .......................................................... 50
ምዕራፍ አምስት .......................................................... 52
የልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ ክዋኔና ፋይዳ .......................................................... 52
5.1 የመርሐ ቤቴ ልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ ምንነትና ታሪካዊ ዳራ .......................................................... 52
5.2 ለጨዋታው የሚደረግ ቅድመ ዝግጅት .......................................................... 55
5.3 በጨዋታው የወጣት ወንዶችና ተሳታፊዎች ሚና .......................................................... 59
5.4 የጨዋታዎቹ ዓይነት እና ክዋኔ .......................................................... 61
5.4.1 በዜማ /በግጥም/ የሚታጀቡ ጨዋታዎች .......................................................... 62
5.4.1.1 አጋጋሙዬ/እቶት እቶቴ/.......................................................... 62
5.4.1.2 ማሬ ዘንባባዬ.......................................................... 65
5.4.1.3 ሸወይባ.......................................................... 69
5.4.1.4 ቡፍጨ ገላ.......................................................... 70
5.4.1.5 አሽም እምቧ.......................................................... 71
5.4.1.6 ሰላም ሰላሙ.......................................................... 73
5.4.2 የውድድራዊ ጨዋታዎች ዓይነትና ክዋኔ .......................................................... 75
5.4.2.1 ዝሎሽ.......................................................... 75
5.4.2.2 ቅርጭፋት/ቅርጥፋት.......................................................... 78
5.4.2.3 እባብ ወጣዬ እባብ ወረዳ.......................................................... 79
5.4.2.4 ቅጥልጥሎሽ.......................................................... 81

5.5 ጨዋታው ለማህበረሰቡ ያለው ፋይዳ ........ 82
5.6 በጨዋታው ላይ የሚታዩ ስጋቶች........ 86
5.6.1 የሚታዩ ስጋቶች ........ 86
ምዕራፍ ስድስት ........ 89
ማጠቃለያና ይሁንታ ........ 89
6.1. ማጠቃለያ ........ 90
6.2. ይሁንታ ........ 92
ዋቢ ጽሑፎች........ 94
አባሪዎች........ 100

# የፎቶግራፍ /ምስል/ ማውጫ


ምስል 1፡- ድንገተኛ የመደርመስ አደጋ የገጠመው የጀማ ወንዝ ድልድይ ----------- 10

ምስል 2፡- አዲስ የተሰራው የጀማ ወንዝ አማራጭ/ጊዜአዊ መንገድ ----------------- 11

ምስል 3፡- የዓለም ከተማ ጎድጓዲት የሽክና ጠጅ ቤት --------------------------------- 16

ምስል 4፡- የመርሐ ቤቴ ወረዳ ካርታ ------------------------------------------------- 45

ምስል 5፡- የወረዳው ከፊል መልክዓ ምድራዊ ገጽታ ----------------------------------- 48

ምስል 6፡- በአካባቢው ባለሙያዎች የሚዘጋጅ የቆዳ ጫማ ---------------------------- 56

ምስል 7፡- አሸንክታብ፣ አርጌሽ ልሙት እና የብር አንባር ---------------------------- 57

ምስል 8፡- ልጃገረዶች ለጨዋታው የሚሆኑ አልባሳትና ጌጣጌጥ ሲገዙ ------------- 58

ምስል 9፡- ወጣት ወንዶች የልጃገረዶቹን ጨዋታ ሲመለከቱ ------------------------- 60

ምስል 10፡- ልጃገረዶች አጋጋሙዬ ሲጫወቱ ------------------------------------------- 65

ምስል 11፡- ልጃገረዶች ማሬ ዘንባባዬ ሲጫወቱ ---------------------------------------- 68

ምስል 12፡- ልጃገረዶች ሸወይባ ሲጫወቱ ----------------------------------------------- 69

ምስል 13፡- ልጃገረዶች ቡፍጨ ገላ ሲጫወቱ ------------------------------------------ 71

ምስል 14፡- ልጃገረዶች እሽም እምቧ ሲጫወቱ ---------------------------------------- 73

ምስል 15፡- ልጃገረዶች ሰላም ሰላሙ ሲጫወቱ ---------------------------------------- 74

ምስል 16፡- የልጃገረዶች የገመድ ዝላይ ጨዋታ --------------------------------------- 75

ምስል 17፡- ልጃገረዶች በአንድ አጎንባሽ ዝሎሽ ሲጫወቱ ---------------------------- 76

ምስል 18፡- ልጃገረዶች የጥንድ ዝሎሽ ሲጫወቱ -------------------------------------- 77

ምስል 19፡- የቅርጭፋት ጨዋታን የሚያሳይ ፎቶ-------------------------------------- 78

ምስል 20፡- ልጃገረዶች ቅጥልጥሎሽ ሲጫወቱ --------------------------------------- 81

# ሙዳዬ ቃላት

| ቃላት | ትርጉም (ፍች) |
|---|---|
| መጎነፍ | ለጨዋታ እንዲመችና አቧራ ወደ ውስጥ አካል እንዳይገባ የቀሚስን የፊትና የኋላ ጫፍ  በእግር መካካል ማሰር፣ |
| መፎረሽ | መሳሳት ወይም በትክክል አለመፈጸም |
| ሴት አውል | ሰነፍ፣ ልግመኛ |
| ሽክና | ከቅል የሚዘጋጅ የጠላና የውሃ መጠጫ |
| ቁርበተ ሐሊም | ከአይነ ጥላ ወይም ከሌላ ክፉ ነገር እንዲከላከል አንገት ላይ የሚታሰር |
| ቅዳም ሹር | ከፋሲካ (እለተ እሁድ) ቀድማ ያለችው እለተ ቅዳሜ ወይም የእለተ ፋሲካ ዋዜማ |
| አርጌሽ ልሙት | የልጃገረዶች የአንገት ጌጥ |
| አሳቻ | ድንገተኛ፣ ያልታሰበ |
| አስብይን | ተረኛ ሆነሽ አጫውችን |
| አሸንክታብ | የልጃገረዶች የአንገት ጌጥ |
| አጎንባሽ | በዝሎሽ ጨዋታ ሌሎቹ እንዲዘሉ አጎንብሳ (ከወገቧ ዝቅ ብላ) የምታጫውት ልጃገረድ |
| እናትያ | የቡድን መሪ /አለቃ/ |
| እጅ ማሚሻ | ከዳግም ትንሳኤ /እሁድ/ ቀጥሎ ያለው ሰኞ አርሶ አደሩ ከእረፍት መልስ ስራ የሚጀምርበት ቀን፣ |
| የእጅ አመል | የሌብነት ወይም የስርቆት ልማድ |
| ደረቆት | ጠላ  ለመጥመቅ የሚያስፈልግ ግብዓት/ቂጣ |
| ጅና | ዱላ/ሽመል እንዳይሰነጠቅ የሚያደርግ ጫፉ ላይ የሚገባ የቆዳ ማፈኛ |
| ጋንች | በወጣቶች አልባሳት ላይ እንደ ጌጥ የሚሰፉ ተለጣፊ ባለቀለም ጨርቅ |

# የቃላት አጠቃቀም ጥቁምታ

በዚህ ጥናት ውስጥ "ጨዋታ" የሚለውን ቃል በነጠላና በብዙ በሁለት መንገድ ተጠቅሜአለሁ፡፡ ቃሉ የየጨዋታዎቹ ስያሜ በተጠቀሰበት ክፍል በነጠላ ቁጥር ያገለገለ ሲሆን የጨዋታው ስያሜ ባልተገለጠበት የጥናቱ ክፍል ደግሞ ሁሉንም ጨዋታዎች በመወከል በብዙ ቁጥር ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

በሌላ በኩል "ልጆች" የሚለው አጠቃቀም በዚህ ጥናት ውስጥ ዕድሜያቸው ከ13 እስከ 25 የሚሆኑ የጨዋታውን ከዋኞች ለመግለጥ የቀረበ ነው፡፡ የፋሲካ ጨዋታ የሚጫወቱ ከዋኞች በማህበረሰቡ "ልጆች" እየተባሉ ስለሚጠሩ/ስለሚገለጡ/ እኔም ይህን አገላለጥ በጥናቱ ውስጥ ተጠቅሜአለሁ፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን፣ በመርሐ ቤቴ ወረዳ  የፋሲካ በዓልን መሰረት በማድረግ በሚከበረው የልጃገረዶች ባህላዊ የፋሲካ ጨዋታ ክዋኔ እና ፋይዳ ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን ይህን ጥናት ለመስራት ምክንያት ከሆኑት ምክንያቶች መካከል አንደኛ የመርሐ ቤቴ ልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ እየደረሰበት ካለው የመደብዘዝና የመጥፋት ስጋት ለመታደግ የየጨዋታዎቹን ክዋኔና ፋይዳ ሰንዶ የማቆየት ፍላጎት ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ባደረግሁት የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ የተሰሩ ጥናቶች ባለማግኘቴ ይህን ክፍተት ለመሙላት በማሰብ ነው። የጥናቱ ዋና ዓላማ "የመርሐ ቤቴ ልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታን አከዋወንና ፋይዳ መመርመር" ነው። ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በወረዳው የሚከወነው የልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ ታሪካዊ አጀማመር መነሻ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው? ስንት አይነት ኢና ምን ምን ዓይነት ጨዋታዎች ይከወናሉ? በወረዳው የሚከወነው የፋሲካ ጨዋታ ክዋኔ  ሂደት ምን  ይመስላል? የፋሲካ ጨዋታ ለተጠኚው ማህበረሰብ ምን ፋይዳ አለው? በጨዋታዎቹ ክወኔ ቀጣይነትና ይዘት ላይ ምን ዓይነት ስጋቶች ይስተዋላሉ? የሚሉ መሰረታዊ የምርምር ጥያቄዎች ተዘጋጅተው ምላሽ አግኝተዋል። ጥያቄዎቹን ለመመለስና የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት የመርሐ ቤቴ ወረዳን ይወክላሉ ተብለው ከተመረጡት ከዓለም ከተማ፣ ከአፈዘዝ በርቃቶ፣ ከግሬት ወቸዋርኝ፣ ከአገሪት ቁምአምባ እና ሰባጌ ሃሮገንዳ ቀበሌዎች ስለጨዋታው ታሪክ ያውቃሉ ከተባሉ የሃገር ሽማግሌዎች፣ ከሃይማኖት አባቶች፣ ተጫውተው ካሳለፉ እናቶች፣ ከጨዋታው ተሳታፊ ልጃገረዶችና ወጣት ወንዶች እና ከባህልና ቱሪዝም ባለሙያዎች በአጠቃላይ ከአርባ አራት መረጃ አቀባዮች በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በተተኳሪ የቡድን ውይይት መረጃዎች ተሰብስበዋል። የጥናቱን ቦታ እና መረጃ ሰጭዎች ለመምረጥ የዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን መቅረፀ ድምፅ፣ የእጅ ስልክ፣ የቪዲዮና ፎቶ ካሜራና ማስታወሻ ደብተር መረጃ ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ ውለዋል። ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውና ጥናቱ የተነሳበትን ዋና ጉዳይ የሚያጠናክሩ ማጣቀሻዎች፣ ዋቢ ጽሑፎች፣ ቀደምት ተዛማጅ ጥናቶች ካዕላይ የመረጃ ምንጮች ከአብያተ መጻሕፍና ከኤሌክትሮኒክስ የመረጃ መረብ በንባብ ተቃኝተዋል። በዚህ መሰረት ስለርእሰ ጉዳዩ አስረጅ የሆኑ ጽንሰ ሃሳቦችና ቀደምት ጥናቶች ተዳስሰዋል። ጥናቱ አይነታዊ እንደመሆኑ መጠን በምልከታና በቃለ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ በአግባቡ ተደራጅቶ ገላጭ የትንተና ዘዴን በመጠቀም ተተንትኗል። ለመረጃ ትንተና የክዋኔያዊና ተግባራዊ ንድፈ ሃሳቦች አገልግለዋል። የመርሐ ቤቴ ልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ ታሪካዊ ዳራው/መነሻው/ የክርስትና ሃይማኖት እንደሆነና ከትንሳኤ እስከ ዳግም ትንሳኤ ድረስ አንድ ሳምንት በሚቆየው በዚህ ሁነት ልጃገረዶች ቀደም ብለው በሁለት መንገድ ቅድም ዝግጅት በማድረግ ከጫና ነጻ ሆነው በጨዋታው ላይ እንደሚሳተፉ እና አስር ዓይነት ጨዋታዎች ባህሉ የሚፈቅደውን ህግ በመከተል በቡድን እንደሚከውኑ ጥናቱ አሳይቷል። ጨዋታው ማህበራዊ መስተጋብርን በማጠናከር፣ ባህልና ሃይማኖትን በማስቀጠል፣ ወጣቶች በባህላቸውና በማንነታቸው እንዲኮሩ በማድረግ፣ አካላዊና ሥነልቡናዊ ጥንካሬአቸውን በማዳበር፣ በራስ መተማመናቸውን በማጎልበትና ሃሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ በማድረግ በኩል ከፍተኛ ማህበራዊ፣ ሥነለቡናዊና አካላዊ ፋይዳዎች ቢኖሩትም በውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች ምክንያት ስጋት እንደተጋረጠበት የጥናቱ ውጤት አመላክቷል። ከዚህ በመነሳትም የአካባቢው ማህበረሰብና የሚመለከታቸው አካላት የጨዋታውን ፋይዳ በመገንዘብ ሃላፊነታቸውን ቢወጡ፤ በማህበራዊ፣ ሥነ ለልቡናዊና ስፖርታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ተቋማትና የመስኩ ምሁራን  ከዚህ ጥናት በበለጠ ሰፊ ጊዜና በጀት መድበው በእያንዳንዱ ጨዋታ የሚታዩ ጉዳዮችን አጥንተው የሚያበረክተውን ፋይዳ ቢያሳውቁ፤ ጨዋታው እንዲታወቅና ጎብኝዎች እንዲኖሩት ለማድረግ ባህልና ቱሪዝም፣ መገናኛ ብዙኀንና የሚመለከታቸው የመንግስትና የግል ተቋማት ትኩረት ሰጥተው በጋራ ቢሰሩ የሚሉ የይሁንታ ሃሳቦች ተጠቁመዋል።

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

ይህ ጥናት በሃገረሰባዊ ልማድ ስር ከሚከወኑ ልዩ ልዩ ሁነቶች መካከል በባህላዊ ጨዋታ ውስጥ የሚካተተውን የልጃገረዶች ጨዋታን የሚተነትን ነው፡፡ በዚህ ጥናት በዋነናነት የመርሐ ቤቴ ወረዳ ማህበረሰብ ባህልና ወግ በባህላዊ ጨዋታ አማካይነት  ለተገለፀበት ባህላዊ ጥበብና ፋይዳ ትኩርት ይሰጣል፡፡ በዚህም መሰረት ጥናቱ የክዋኔው ምክንያት፣ የክዋኔዉ ሂደትና ክዋኔው ለማህበረሰቡ ያለውን ጠቀሜታ ይመረምራል፡፡ በዚህ ክፍል የጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ የተጠኝነት አግባብ፣ ዓላማ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች፣ የጥናቱ አስፈላጊነትና ወሰን ቀርበዋል፡፡

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

በሃገረሰባዊ ልማድ ስር ከሚካተቱ የፎክሎር ዓይነቶች ውስጥ አንዱ ሃገረሰባዊ ጨዋታ ሲሆን ይህም እራስን ለማዝናናት፣ ለአካል ጥንካሬ፣ ማህበራዊ መስተጋብርን ለማጠናከር፣ ለስነ ልቡና እድገት፣ ለግለሰባዊ ጠባይ እድገት ሲባል የሚከወኑ ጨዋታዎችን የሚዳስስ የፎክሎር ዘርፍ መሆኑን Dorson (1972:4) ይገልጻሉ፡፡

ሃገረሰባዊ ጨዋታ የሚለው ቃል የሚይዘው ጽንስ ሀሳብ ሰፊ ነው፡፡ ይህንን ስፋቱን በሚያሳይ መልኩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ባዘጋጀው መዝገበ ቃላት ውስጥ “ጨዋታ (ጫወታ) ንግግር፣ ውይይት፣ ልፊያ፣ ድሪያ፣ ቀልድ፣ የሚያስቅ የሚያዝናና ወሬ፣ ውድድር ወይም ፉክክር ያለበትና የሌለበት፣ የቤትና የውጭ ስፖርት፣ መዝናኛ፣ ዘፈን፣ ዳንስ፣ ውዝዋዜ…” (1993፤571) በሚል ተገልጧል፡፡ ይህ ፍቺ እንደሚያስረዳው ጨዋታ በቃል በአንደበት፣ በሰውነት እንቅስቃሴ፣ በግጥሚያ (ልፊያ)፣ በውድድር፣ ወዘተ በቤት ውስጥ ወይም ከቤት ውጭ የሚከወኑ የፎክሎር አሃዶችን ለመግለጽ ጥቅም ላይ እንደሚውል ነው፡፡

ሃገረሰባዊ ጨዋታዎች ራስን ለማዝናናት በማህበረሰቡ ባህል ውስጥ ልዩ ስፍራ የሚሰጣቸውን የተለያዩ ፌስቲቫሎች፣ ክብረ በዓላትን፣ ስነ ስርዓቶችን፣ ስርዓተ ከበራዎችን ለመከወን እንዲሁም በፎክሎር ቡድን ውስጥ ሊኖር የሚገባውን የእርስ በእርስ መስተጋብር

ለማጠናከር በሚል የሚከወኑ ሲሆኑ በሁሉም የማህበረሰብ ክፍሎች ያሉ የስሜት መግለጫና የማህበረሰብ መስተጋብር ማጠናከሪያ ጥበቦች ናቸው፡፡

ሃገረሰባዊ ጨዋታን በልዩ ልዩ መንገድ መመደብ ይቻላል፡፡ ከተጫዋቾቹ እድሜ አንፃር የህፃናት፣ የታዳጊዎች፣ የወጣቶች፣ የጎልማሶች፣ የሽማግሌዎች ጨዋታ ብሎ መመደብ ይቻላል፡፡ ከፆታ አንፃር ደግሞ የወንዶች፣ የሴቶች እና የድብልቅ ተብለው የሚመደቡ ሲሆን፣ ካላቸው ባህሪ አንፃር አዝናኝ፣ አስተማሪ፣ አስፈሪ እንዲሁም ከሚቀርቡበት ዓላማ አንፃር ሃይማኖታዊ ወይም ባህላዊ ተብለው ሊመደቡ እንደሚችሉ ሰሎሞን (2007፣171) ያስረዳሉ፡፡

ባህል ለማህበረሰቡ ከሚሰጠው ጥቅም አኳያ ታይቶ መዳኘት እንዳለበት Sims & Stephens (2005፤174) ያስረዳሉ፡፡ ይህም አንድ ባህል፣ ባህል ሆኖ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ እያደገ/እየበለጸገ እንዲሁም እየተጠበቀ ለመዝለቅ ለማህበረሰቡ የሚሰጠው አንዳች ረብ መኖር እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡ ማንኛውም የፎክሎር ዘርፍ በህይወት የሚኖረው የሚያበረክተው አስተዋፅኦ እስካለው ድረስ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም ማንኛውም የፎክሎር ዘርፍ የተወሰኑ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ ወይም ስነልቦናዊ ፍላጎቶችን የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡

ከላይ የቀረቡትን ገለጻዎች መነሻ በማድረግ ስንመለከት የመርሐ ቤቴ የልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ በሀገረሰባዊ ልማድ ስር ከሚካተቱት ንዑሳን ዘርፎች መካከል በሀገረሰባዊ ጨዋታ ውስጥ ሊመደብ የሚችል ሎር እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ኢትዮጵያ የበርካታ ብሄረሰቦች አገር በመሆኗ የብዝሃ ባህል ባለቤት እንደሆነች ይታወቃል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተለይዩ የአገሪቱ ክፍሎች እንደዚህ ያሉ በርካታ ሃገረሰባዊ ጨዋታዎች በስፋት ይከወናሉ፡፡ ክዋኔዎቹ እያንዳንዳቸው በመካከላቸው አውድ ተኮር ልዩነት ቢኖራቸውም ለማህበረሰቡ በሚሰጡት ፋይዳ እና እርካታ የሚጋሯቸው የወል ባህሪያት እንዳላቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡

ይሁን እንጅ እንደዚህ አይነት የተለየ አቀራረብና ፋይዳ ያላቸው ክዋኔዎች በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች እንዳሉ ቢታመንም በቂ ትኩረት ሲሰጣቸው አይስተዋልም፡፡ በተለያዩ አብያተ መጻህፍትና የበይነ መረብ ምንጮች በነበረኝ ዳሰሳ የተመለከትኳቸው ጥናቶች በህጻናት ጨዋታዎች ሰብእና እና ሥነልቡና ግንባታ (ይትረፍ፣ 2012 ፤ ሰሎሞን፣ 2013፤

ምስጋናው፣ 2012) ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው። በተለይ ጾታን መሰረት አድርገው የሚቀርቡ እንደፋሲካ ጨዋታ አይነት ክዋኔዎች በአዳሚው ዘርፍ በስፋት የጥናት ርእሰ ጉዳይ ሆነው እየቀረቡ ነው ለማለት አያስደፍርም። ስለሆነም ይህ ጥናት ክፍተቱን በመሙላት ረገድ የራሱ አወንታዊ አስተዋጽኦ ይኖረዋል የሚል እምነት አለኝ። ምክንያቱም የመርሐ ቤቴ ልጃገረዶችን የፋሲካ ጨዋታ ታሪካዊ ዳራ፣ ክዋኔ፣ ፋይዳ እና እየገጠሙት ያሉትን ተግዳሮቶች መመርመር የዚህ ጥናት ትኩረት ነው። የጨዋታውን መነሻ ምክንያት ይዳሰሳል፤ ቅድመና ጊዜ ክዋኔው  በጽንሰ ሃሳብና ንድፈ ሃሳብ መተንተኛዎች ተተንትነዋል፤ ጨዋታው በይዘትና ክዋኔ ሂደት ላይ እየገጠሙ ያሉት ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች ተፈትሸዋል።

በመርሐ ቤቴ ወረዳ ሐይማኖትና ባህልን መሰረት አድርገው የሚከወኑ በርካታ የጨዋታ ዓይነቶች አሉ። በወረዳው በድምቀት ከሚከወኑ ሃገረሰባዊ የጨዋታ ዓይነቶች መካከል ከትንሳኤ በዓል ጋር ተያይዞ የሚከወነው የልጃገረዶች ጨዋታ ተጠቃሽ ነው። ይህ ክንውን የተለያዩ ዘፈኖችና ጨዋታዎች የሚቀርቡበትና በማህበረሰቡ ዘንድ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ሲሆን እንደ ጥምቀትና ሌሎች ዋና ዋና ክብረ በዓላት ጨዋታዎች ሁሉ በልጃገረዶቹ በጉጉት የሚጠበቅ ነው።

አንድ ሳምንት በሚቆየው የፋሲካ ጨዋታ በዜማ የሚታጀቡና ውድድራዊ ባህሪ ያላቸው ጨዋታዎች የሚቀርቡበት ሲሆን ልጃገረዶቹ ከጓደኞቻቸው ጋር በደስታና በቡረቃ ሳምንቱን ያሳልፋሉ። የመርሐ ቤቴ የፋሲካ የልጃገረዶች ጨዋታዎች ልፊያ፣ ፉክክር፣ ዘፈን፣ ጭፈራ፣ ወዘተ የሚንጸባረቅባቸው ሲሆኑ የትንሳኤ በዓልን ጠብቀው በዓመት አንድ ጊዜ ከቤት ውጭ የሚከወኑ ማህበራዊ መስተጋብር የሚፈጠርባቸው ጨዋታዎች ናቸው።

በዚህ የሰሞነ ትንሳኤ ሳምንት ጨዋታ ከአስር በላይ ጨዋታዎች በልጃገረዶቹ ይከወናሉ። ከጨዋታዎቹ መካከል ከፊሉ በዜማና በግጥም የሚታጀቡ ሲሆኑ ከፊሉ ደግሞ በዜማ ወይም በግጥም የማይታጀቡ ውድድራዊ ባህርይ ያላቸው ናቸው። በጨዋታው የሚሳተፉት እድሜያቸው በአማካይ ከ13 እስከ 25 ዓመት የሚሆናቸው ልጃገረዶች ናቸው። ሴት ህጻናት በጨዋታዉ ላይ ልጃገረዶቹን በመከተል ወይም ከኋላ በመሆን ይሳተፋሉ። ይህም ህጻናቱ ቀጣይ ተረካቢ በመሆናቸው ለክዋኔው ሽግግር ተግባራዊ ልምምድ እንደሚያደርጉ ያመላክታል።

በጨዋታው ላይ ወጣት ወንዶችና ሌሎች ተመልካቾች የመታደምና የተወሰነ የተሳትፎ ድርሻ አላቸው፡፡ ታዳሚዎቹ ዙሪያውን በመቆም ጥሩ የሚጫወቱትን ያደንቃሉ፤ በጭብጨባና በድምጽ ያበረታታሉ፡፡ ጨዋታውን ያደምቃሉ፡፡ ደካማ ተጫዋቾችን ይተቻሉ፡፡ ጨዋታው በርካታ ልጃገረዶች የሚሳተፉበት በመሆኑ እና ውበትን ለማድነቅ እድል ስለሚሰጥ ወጣት ወንዶች ከታዳሚነት ባሻገር ልባቸው የከጀላትን የወደፊት የትዳር ጓደኛቸው የምትሆን ኮረዳ የሚመርጡበት አጋጣሚ ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በባህልና ቱሪዝም ዘርፍ በባለሙያነት በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ውስጥ በነበረኝ ረዘም ያለ የስራ ቆይታ በየወረዳዉ የሚከወኑ በርካታ ጨዋታዎችንና ባህላዊ ክዋኔዎችን የመመልከትና የመታደም አጋጣሚ ነበረኝ፡፡ ባህላዊ ጨዋታዎች፣ ዘፈኖችና ሥርዓቶች እንዲተዋወቁና እንዲለሙ የዞኑ አስተዳደርና ወረዳዎች ሰፊ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ በክልልና በዞን የሚዘጋጁ ዓመታዊ ትእይንቶች የዚህ ጥረት ማሳያ ናቸው፡፡

በእነዚህ ዝግጅቶች የመርሐ ቤቴ ወረዳም እንዲተዋወቁና እንዲለሙ የሚፈለጉ ልዩ ልዩ ባህላዊ ጨዋታዎችንና ዘፈኖችን ይዞ ይቀርባል፤ ለማስተዋወቅ ጥረት ያደርጋል፡፡ ነገር ግን ይህ የፋሲካ ጨዋታ ከዓመት ዓመት ጨዋታውን ሊያደበዝዙ የሚችሉ የተለያዩ ስጋቶች እንደተጋረጡበት ከተሳታፊዎች መስማቴና አንዳንድ ቦታዎች ላይም እንደበፊቱ እንዳይከወንና የጨዋታው ይዘትና የአከዋወን ስርዓት እንዲቀየር የሚያደርጉ ተጽእኖዎች እንደተፈጠሩበት ማወቄ ጨዋታው ሙያዊ በሆነ መንገድ ቢጠናና ማህበራዊ ጠቀሜታውን በአግባቡ ማሳየት ቢቻል ክዋኔው እያጋጠመው ያለውን ስጋት ለመቀነስ ያስችላል በሚል ይህ ርእሰ ጉዳይ ምርጫዬ ሊሆን ችሏል፡፡

ለዚህ ርዕስ መመረጥ አነሳሽ የሆነው ሁለተኛው ምክንያት በልጃገረዶች ጨዋታ ላይ የተሰሩ ጥናቶች በጣም አነስተኛ መሆን ነው፡፡ ምክንያቱም በተለይም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አብያተ መጽሐፍትና በተለያዩ ኤሌክትሮኒክ የመረጃ መረቦች/የበይነ መረብ/ ምንጮች በነበረኝ ዳሰሳ ያገኘኋቸው ጥናቶች ሁለት ብቻ (“የቡሄ አከባበር እና ግጥሞች በአርሲ ነገሌ” በሚል ርዕስ በዮሐንስ ታደሰ በ1986 ዓ.ም ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት እና በብርሀን አሰፋ አራጋው በ1997 ዓ.ም “የአሆላሌ ጨዋታ ክዋኔና የግጥሞቹ ይዘት ትንተና” በሚል ርዕስ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት)

ናቸው፡፡ በዩኒቨርስቲው የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በሃገረሰብ መድሃኒት፣ በግጭት አፈታት፣ በለቅሶ ሥርዓት ወዘተ ላይ ከተሰሩ የመመረቂያ ጥናቶች አንጻር በልጃገረዶች ጨዋታ ላይ የተሰሩ ጥናቶች አነስተኛ ናቸው ለማለት ያስደፍራል፡፡

በሃገራችን በተለያየ የእድሜ ክልል ባሉ የማህበረሰብ ክፍሎች የሚከወኑ ብዙ ዓይነት ሃገረሰባዊ ጨዋታዎች ቢኖሩም እነዚህ ባህላዊ ሁነቶች በቂ ትኩረት ያገኙ አይመስለኝም፡፡ ስለሆነም ይህ የመርሐ ቤቴ የልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ ቢጠና ይህን ክፈተት ሊሞላ ይችላል በሚል ርዕሰ ጉዳዩን ለመመረጥ ያስቻለኝ አንዱ ምክንያት ነው፡፡

ሶስተኛው ምክንያት በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የባህል ጥናት ባለሙያነቴ በተለያዩ የስራ አጋጣሚዎች የተለያዩ ብሄረሰቦችን ባህላዊ ክዋኔዎች የማወቅ፣ የመመልከትና የመሰነድ አጋጣሚዎች ነበረኝ፡፡ እንደ አንድ የባህል ባለሙያ የማህበረሰቡን ሀገር በቀል እውቀቶች፣ እሴቶችና ፋይዳዎቻቸውን የማጥናት ፍላጎት ማሳደሩ ሌላው የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ነው፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓቢይና ዝርዝር ዓላማ

### 1.3.1 ዓቢይ (ዋና) ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና/ዓቢይ ዓላማ በመርሐ ቤቴ ወረዳ የሚከወነውን የልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ ክዋኔ ሂደትና ጨዋታው ለማህበረሰቡ ያለውን ፋይዳ መመርመር ነው፡፡

### 1.3.2 ንዑሳን ዓላማዎች

- በመርሐ ቤቴ ወረዳ የሚከወነውን የልጃገረዶች ጨዋታ ታሪካዊ ዳራ/መነሻ ምክንያት/ መፈተሽ፣
- የጨዋታውን ክዋኔ ሂደት (ቅድመ ክዋኔ፣ ጊዜ ክዋኔና ድህረ ክዋኔ) መተንተን፤
- የፋሲካ ጨዋታ ለተጠኘው ማህበረሰብ የሚያስገኘውን ፋይዳ መግለጽ፣
- በጨዋታው ክዋኔ ዘላቂነት ላይ የሚታዩ ስጋቶችንና መፍትሄዎችን መለየትና ማብራራት፣

## 1.4. የጥናቱ የሚመልሳቸው የምርምር ጥያቄዎች

ይህ ጥናት ሊመልሳቸው የሚገቡ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. በመርሐ ቤቴ ወረዳ የሚከወነው የልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ ታካዊ አጀማመር መነሻ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?
2. በወረዳው የሚከወነው የፋሲካ ጨዋታ ክዋኔ ሂደት (ቅድመ ክዋኔ፣ ጊዜ ክዋኔና ድህረ ክዋኔ) ምን ይመስላል?
3. የፋሲካ ጨዋታ ለተጠኝው ማህበረሰብ ምን ፋይዳ አለው?
4. በጨዋታዎቹ ክወኔ ቀጣይነትና ይዘት ላይ ምን ዓይነት ስጋቶች ይስተዋላሉ?

## 1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት/ፋይዳ

ይህ ጥናት በወረዳው ህዝብ ላይ ለሚደረጉ አጠቃላይ ባህላዊና ማህበራዊ ተግባራት አጋዥ ሊሆን ይችላል፡፡ በተለይም ወጣቶች ሃሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ፣ የወደፊት ህይወታቸውን እንዲተልሙ፣ ማህበራዊና ሥነልቡናዊ ጥንካሬ እንዲኖራቸው፣ በባህላቸው እንዲኮሩና ለባህላቸው እንዲቆረቆሩ ጥናቱ ስለሚያሳይ ክዋኔውንና ማህበራዊ ፋይዳዉን መሰረት በማድረግ ለሚከናወኑ ማህበራዊና ሥነልቡናዊ ስራዎች ጠቀሜታ ይኖረዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ሌላው የልጃገረዶቹን ዓመታዊ የፋሲካ ጨዋታ ክዋኔ እና ፋይዳ በማስተዋወቅ፣ በማልማትና በማሳደግ እንደ አሸንዳ፣ ሻደይ፣ አሸንድዬ ጨዋታዎች የቱሪዝም ግብዓት ለማድረግ በየደረጃው በሚገኙ የባህልና ቱሪዝም መዋቅሮች ለሚሰሩ ስራዎች ይህ ጥናት ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

በተጨማሪም በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ጥናት ለሚያካሂዱ አጥኝዎች/ተመራማሪዎች/፣ በሴቶችና በሥርዓተ ጾታ ላይ ትኩረት አድርገው ለሚሰሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በመነሻነትና በምንጭነት በማገልገል አዎንታዊ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በሰሜን ሸዋ ዞን በመርሐ ቤቴ ወረዳ የሚካሄድ ነው፡፡ በወረዳው የሚከወኑ በርካታ ባህላዊ ሥርዓቶች፣ ወጐች፣ እሴቶች፣ ልማዶች እና ባህላዊ የጨዋታ አይነቶች ቢኖሩም የዚህ ጥናት ትኩረት በሃገረሰባዊ

የልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ ክዋኔና ፋይዳ ላይ ነው፡፡ በክዋኔው ላይ ወጣት ወንዶች የሚጫወቷቸው የራሳቸው ጨዋታዎች ቢኖሩም የዚህ ጥናት ትኩረት አይደለም፡፡ ይህ ጥናት ገላጭ የምርምር ዘዴን የሚከተል ሲሆን ክዋኔያዊና ተግባራዊ ንድፈ ሃሳቦችን ለጥናቱ መተንተኛነት ተጠቅሟል፡፡

ጥናቱ አንድ ሳምንት በሚቆየው የፋሲካ ጨዋታ ልጃገረዶች በነጻነት በጨዋታው ለመሳተፍ /ለመታደም/ የሚያደርጉትን ቅድመ ዝግጅት ይዳስሳል፡፡ በዚህም መሰረት ከዋናው የክዋኔ ጊዜ ቀደም ብሎ በልጃገረዶቹ የሚከናወኑ የስራ ዝግጅቶች፣ የጸጉር ስራ፣ ለጨዋታው የሚገለገሉባቸው አልባሳትና ጌጣጌጥ ዓይነትና ምርጫ፣ የመዋቢያ ቁሶች በዚህ ጥናት ተቃኝተዋል፡፡

በክዋኔ ጊዜ ደግሞ የሚከውኗቸው የጨዋታ አይነቶች፣ የጨዋታዎቹ አካላዊ እንቅስቃሴ፣ የታደሚ ተሳትፎ፣ የክዋኔው ማህበራዊ ጠቀሜታ በአጠቃላይ በጨዋታው የአንድ ሳምንት ጊዜ በየእለቱ የሚከወን እያንዳንዱ ጨዋታ የክዋኔው ሂደ በጥናቱ ትኩረት ተደርጎ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ የጨዋታው ክዋኔ እና ማህበራዊ ፋይዳ የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረት ቢሆንም ከክዋኔው ጋር የሚቀርቡ/የሚነገሩ ስነቃሎች መጠነኛ ዳሰሳ ተደርጎባቸዋል፡፡

ከቦታ አኳያ ከመርሐ ቤቴ ወረዳ ውጭ ተመሳሳይ ክዋኔ ቢኖር እንኳን የዚህ ጥናት ትኩረት አይሆንም፡፡ ለጥናቱ ከተያዘው ጊዜና በጀት አንጻር በመርሃ ቤቴ ወረዳ ውስጥ ያሉ ሁሉንም ቀበሌዎች ማካተት ስለማይቻል ወካይ ቀበሌዎችን በዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ በመለየት በተመረጡ ቀበሌዎች ላይ ብቻ መረጃ የማሰባሰብ ስራ ተከናውኗል፡፡

## 1.7 የአጠናን ሥነ ምግባር ደንብ

ማነኛውም ጥናት የራሱ የሆነ የሥነ-ምግባር ደንብ ማክበር እንዳለበት ድርሳናት ያስረዳሉ፡፡

> *Typically, we record the folklife of particular communities and groups because we respect them and think their traditions are important and interesting. Obviously, we don't want to do anything to harm the communities we study, or the individuals within them. Since our interviewees are giving us their time and trust, it's also important that we be honest and truthful with them. (Winick and Bartis 2016:10)*

የተወሰኑ ማህበረሰቦች እና ቡድኖችን ባህል/ትውፊት ስለማረከን ወይም ስለምናከብራቸው፣ ባህሎቻቸው ጠቃሚ እና አስደሳች ናቸው ብለን ስለምናስብ እናጠናለን፤ በተለያዩ ዘዴዎች ልንቀርጽ እንችላለን፡፡ በዚህ ሂደት እኛ የምናጠናቸውን ማህበረሰቦች ወይም በውስጣቸው ያሉትን ግለሰቦች የሚጎዳ ምንም ነገር ማድረግ እንደሌለብን እና የቃለ መጠይቅ መረጃ አቀባዮቻችን ጊዜያቸውን እና አመኔታቸውን እየሰጡን ስለሆነ፣ እኛም ለእነሱ ታማኝ እና እውነተኛ መሆናችን አስፈላጊ እንደሆነ ከቀረበው ገለጻ እንረዳለን፡፡

ስለሆነም ለጥናት ስራ ወደ መስክ ስንሄድና መረጃ ስንሰበስብ የተጠኘውን ማህበረሰብ ባህል፣ ልማድ፣ ሃይማኖት፣ ወዘተ ማክበርና ማህበረሰብን ወይም ግለሰብን ሊጎዱ ከሚችሉ ተግባራት መቆጠብ እንደሚገባ ነው፡፡ በተጨማሪም መረጃ አቀባዮች ለቃለ መጠይቅ የሚመቻቸውን ቦታና ጊዜ እንዲመርጡ መፍቀድና ታማኝ ሆነን መቅረብ እንደሚገባ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ይህ ጥናትም ይዞት ከተነሳው ርዕሰ ጉዳይ አንፃር የሚከተሉትን የስነ ምግባር ደንቦች ተግባራዊ አድርጓል፡፡

- ጥናቱ ስለሚካሄድበት አካባቢ ተገቢ የአካልና የስነ ልቡና ዝግጅት በማድረግና ለመስክ ስራዬ ተገቢ ጌዜ በመስጠት ለጥናቴ በቂ መረጃ ማሰባሰብ ችያለሁ፡፡
- ስለሚጠናው ርዕሰ ጉዳይ አስፈላጊ ትብብር እና ድጋፍ ለማግኘት ይረዳኝ ዘንድ በትምህርት ክፍሉ እና በዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ የተጻፉልኝን ህጋዊነቴን የሚያሳዩ የትብብር ደብዳቤዎችን መረጃ ለምፈልግባቸው ተቋማት በማሳየት ምርምር የማደርግበትን ዓላማ በማስረዳት ፈቃደኝነታቸውን አረጋግጫለሁ፡፡
- ወደ መስክ ጉዞ ከማድረጌ በፊት ተገቢ የመረጃ መሰብሰቢያ ቁሳቁሶችን አሟልቻለሁ፤ መረጃ በሰበሰብሁበት ወቅት የመረጃ ሰጭዎቸን ግላዊ ጉዳዮች፣ ማህበረሰበራዊና ባህላዊ ወግ፣ ስርዓትና ልማድ አክብሬ መረጃ አቀባዮቸን በአክብሮትና በትህትና በመቅረብ አስፈላጊውን መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡
- ለጥናቴ አስፈላጊ የሆኑ መረጃ ለሚሰጡ መረጃ አቀባዮች በግልጽ ስለ ራሴ እና ስለማጠናው ርዕሰ ጉዳይ ዓላማ እና ጠቀሜታ በማስረዳት የጋራ መግባባት ላይ በመድረስ ተጨባጭ መረጃዎችን እንዲሰጡ አድርጌአለሁ፣

- ለመረጃ አቀባዮች ፍላጎት ቅድሚያ በመስጠት በመረጡት ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ መረጃ እንዲሰጡ ዕድሉን ሰጥቻለሁ፡፡
- መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት የፎቶ ግራፍ፣ የድምጽና የምስል መቅረጫ መሳሪያዎችን ከመጠቀሜ በፊት የመረጃ አቀባዮቼን ፈቃደኝነት በመጠየቅ ስማቸውን፣ ሃሳባቸውንና ምስላቸውን በፈቃደኝነት ብቻ አስፍሬአለሁ /ተጠቅሜአለሁ፡፡
- ለጥናቴ የተባበሩኝን ተቋማትና መረጃ አቀባዮችን በአግባቡ ማመስገንን ጨምሮ ሌሎች የጥናት ሥነምግባር ደንቦች ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡

## 1.8 ያጋጠሙ ችግሮች፣ የተወሰዱ መፍትሄዎችና የመስክ ገጠመኝ

### 1.8.1 ያጋጠሙ ችግሮች፣

ጥናቱን ከማካሄዴ በፊት ቀድሜ የለየኋቸውና የተዘጋጀሁባቸው ተግዳሮቶች ነበሩ፡፡ ሆኖም መረጃ ለማሰባሰብ በተንቀሳቀስሁ ጊዜና በነበረው ሂደት ከገመትሁት በላይ የሆኑ ችግሮች አጋጥመውኛል፡፡ በተለይ የጸጥታ ችግር፣ የጀማ ድልድይ በድንገት መፍረስና ከትንሳኤ በዓል ጋር ተያያዞ የነበረው የትራንስፖርት ችግር ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

**1ኛ/ ወቅታዊ የጸጥታ ችግር**፡- በወቅታዊ ጸጥታ ችግር ምክንያት አንዳንድ ቀበሌዎች ላይ ጨዋታው እንዳይካሄድ መከልከል እና ከመደበኛ የክዋኔ/የጨዋታ ሰዓታቸው ቀድመው እንዲበተኑ ማድረግ፤

**2ኛ/ የትራንስፖርት ችግር፡-** ይህ ሁኔታ በሁለት መልኩ የሚታይ ነው፡፡ አንደኛ ከአዲስ አበባ ወደ ዓለም ከተማ እና ከዓለም ከተማ አዲስ አበባ የተደረገውን ጉዞ የሚመለከት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከዓለም ከተማ ወደ ተመረጡ የገጠር ቀበሌዎች የነበረው የትራንስፖርት ችግር ነው፡፡

ከአዲስ አበባ ወደ ዓለም ከተማ በቀን የሚሄደውና ተመላሹ መደበኛ /ተረኛ መኪና/ አንድ ብቻ ሲሆን የተሳፋሪው ቁጥር እጅግ ከፍተኛ ነበር፡፡ በተለይ እኔ በተጓዝሁበት ሰሞን የትንሳኤ በዓል ሳምንት በመሆኑ የመንገደኛው ቁጥር ቀድሞ ከነበረው ከፍ ሳይል አልቀረም፡፡ ያሉትን የከተማ ትራንስፖርት አማራጮች ተጠቅሜ ሌሊት 10፡30 መነሃሪያ ብደርስም፣ እንኳን ወንበር ማግኘት ቆሞ ለመሄድም ከባድ ነበር፡፡

ሁለተኛው ከዓለም ከተማ ለመረጃ ወደተመረጡ ቀበሌዎች ያለው የትራንስፖርት ችግር ነው፡፡ ቀበሌዎቹ ከዓለም ከተማ በአማካይ ከ12-16 ኪሎ ሜትር ድረስ ይርቃሉ፡፡ ወደ ቀበሌዎቹ የሚሄድ መደበኛ የትራንስፖርት አማራጭ አለመኖር ሌላው ችግር ነበር፡፡

**3ኛ/ የወቅቱ የአየር ሁኔታ፡-** በብዙ አካባቢዎች ዝናባማ እንደሆነ ለቅድመ ጥናት ከአዲስ አበባ ደብረ ብርሃንና ዓለም ከተማ በተንዝሁበትና ቀጥሎም መረጃ ለመሰብሰብ ከአዲስ አበባ በሙከ ጡሪ ዓለም ከተማ በተንዝሁበት ጊዜ መመልከት ችያለሁ፡፡

መረጃ በምሰበስብባቸው ቀበሌዎችም ተመሳሳይ የዝናብ ሁኔታ በመኖሩ ጨዋታዉ በደራበትና መረጃ በምሰበስብበት ጊዜ ድንገተኛ ዝናብ ሲዘንብ ጨዋታው ይበተናል፡፡ ይህም በጊዜው የገጠመኝ አንዱ ችግር ነበር፡፡

**4ኛ/ የጀማ ወንዝ ድልድይ ድንገት መሰበር/መደርመስ/፡-** ለቅድመ ጥናት ስራ ዓለም ከተማ ቆይቼ ስመለስ አንድ ሰዓት አካባቢ እኔ የተሳፈርሁበት ተሽከርካሪ ተሻግሮ ወደ አራት ሰዓት ገደማ ድልድዩ መሰበሩን ሰማን፡፡ ወደ መርሐ ቤቴ ወረዳ ለመሄድ የተሻለውና ብቸኛው መንገድ ድንገተኛ አደጋ ሲገጥመው ስራዬ ይስተጓጎልብኝ ይሆን? የሚል ከፍተኛ ስጋት ፈጥሮብኝ ነበር፡፡

ምስል 1፡- ድንገተኛ የመደርመስ አደጋ የገጠመው የጀማ ወንዝ ድልድይ



(በአጥኚው የእጅ ስልክ (Tecno CAMON 17) የተነሳ፣ ሚያዝያ 2015 ዓ.ም)

### 1.8.2 የተወሰዱ መፍትሄዎች

ከአዲስ አበባ ወደ መርሐ ቤቴ የነበረውን የትራንስፖርት ችግር በተመለከተ ያለኝ አማራጭ ለአስቸኳይ ስራ እንደምሄድ ተራ አስከባሪዎችን በመለመን፣ ከታሪፍ በላይ በመክፈልና በትርፍ ቆመው ከሚሄዱት ተሳፋሪዎች መካከል አንዱ ሆኘ ከ180 ኪ.ሜ ቆሜ ለመጓዝ

ወስኜ ጉዞየን በእቅዴ መሰረት አከናውኛለሁ። ወደየቀበሌዎቹ የሚደረገውን ጉዞም ተጨማሪ ወጭ በማውጣት (200 ብር የሚያስከፍለውን እስከ 500 ብር በመክፈል) የባለሶስት እግር/ባጃጅ/ ተሽከርካሪዎችን በመጠቀም ስራዬን ለማከናወን ችያለሁ።

ሌላው ክልከላ የተደረገበትን ቀበሌ ከወረዳው የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሃላፊና ባለሙያዎች ጋር በመነጋጋር ወደ ሌላ ቀበሌ በመቀየር (ጨዋታው በሁሉም ቀበሌዎች በተቀራራቢ ሁኔታ ስለሚከወን) የመረጃ ማሰባሰብ ስራዬን ማከናወን ችያለሁ።

በዝናብ ምክንያት የገጠመኝን ችግር እስኪያባራ በመጠበቅ እንደገና ሲሰባሰቡ ስራዬን ማከናውን ነበረብኝ። በተለይ የወረዳው የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃላፊና ባለሙያዎች አብረውኝ ስለነበሩ የቀበሌ አመራሮችን በማስተባበር ለመረጃ ማሰባበሰቡ ስራ ምቹ ሁኔታ ይፈጥሩልኝ ነበር። ይህም ችግሩ እንዲቃለል አድርጎልኛል።

በመጨረሻም የጀማ ወንዝ ድልድይ መሰበርን በተመለከተ በሚመለከታቸው አካላት አማራጭ/ተለዋጭ/ ድልድይ በፍጥነት በመሰራቱ የነበረኝ ስጋት /ችግሬ/ ሊቃለል ችሏል።

ምስል 2፡- አዲስ የተሰራው የጀማ ወንዝ አማራጭ/ጊዜአዊ መንገድ



(በአጥኚው Tecno CAMON 17 የእጅ ስልክ የተነሳ፣ ሚያዝያ 2015 ዓ.ም)

### 1.8.3 የመስክ ልምድ እና ገጠመኝ

የትኛውም አጥኚ/ተመራማሪ/ ወደ መስክ ሄዶ ጠቃሚ መረጃዎችን ከመሰብሰቡ በፊት ጥናቱን መጀመር ያለበት በቤተ መጻሕፍት፣ በአርካይቭ፣ በሙዝየም በመገኘት መሆን እንደአለበት የዘርፉ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ “We are accustomed thinking of scholarly work as taking place in a library, and the library is often the first step as either the amateur or the professional folklorist begins his or her investigation.” (Winick & Bartis 2016:3)፡፡ በዚህም መሰረት ጥናቱን ከግብ ለማድረስ የመስክ ስራዬ የጀመረው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና በሌሎች አብያተ-መጽሐፍት ውስጥ የሚገኙ ጽሑፎችን በማንበብ ነው፡፡

ሌላው አንድ ተመራማሪ ወደ መስክ ከመሄዱ በፊት ጥናቱ ስለሚካሄድበት አካባቢና ስለሚጠናው ርዕሰ ጉዳይ በቂ እውቀት ሊኖረው ይገባል፡፡ ይህም ምን አይነት አልባሳት መያዝ እንዳለበት ለመወሰን ይረዳዋል፡፡ በአካባቢው ያለው የትራንስፖርት አማራጭ ምን እንደሚመስል፣ ምግብና መኝታ ቤቶች፣ የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ ወዘተ መኖር አለመኖሩን አስቀድሞ ማወቅ ይጠበቅበታል፡፡ እንደ Goldstein (1964፡37) አካባቢውን ቀደም ብሎ ማወቁ አጥኚው አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት አድርጎ እንዲንቀሳቀስ እና በጥናት ስራ ቆይታው ከማህበረሰቡ ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

በዚህም መሰረት የተጠቀሱትን ቁም ነገሮች ግምት ውስጥ በማስገባት መረጃ ለማሰባሰብ ወደ መስክ ከመሄዴ በፊት ስለ አካባቢውና ስለ ማህበረሰቡ በምልከታ ዳሰሳ አድርጌአለሁ፡፡ ይህንን ተግባር ለማከናወን በቅድሚያ ያቀናሁት ወደ ሰሜን ሸዋ ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ነበር፡፡ ቀደም ሲል የመምሪያው የስራ ባልደረባ ስለነበርሁ መልካም አቀባበልና ትብብር ተደርጎልኛል፡፡ ምንም እንኳን ስለመርሐ ቤቴ ልጃገረዶች ጨዋታ የጽሁፍም ሆነ የምስል መረጃ በመምሪያው ባለመኖሩ ማግኘት ባልችልም በተለይ የመምሪያው ኃላፊ ወ/ሮ ቅመም አሸኔና እና የባህል ዘርፍ ሃላፊው አቶ እምነተመድህን አብተው በመርሐ ቤቴ ወረዳ የምሰራው የጥናት ስራ የተቃና እንዲሆን የትብብር ደብዳቤ በመጻፍና ለወረዳው የስራ ሃላፊዎች በስልክ በማስገንዘብ ተገቢ ትብብር አድርገውልኛል፡፡ በተጨማሪም የዞኑ ኮሚኒኬሽን መምሪያ ኃላፊ አቶ አማረ አስፈላጊው ትብብር እንዲደረግልኝ በተዋረድ በስልክ በማስገንዘብ እዚያ ሄጄ ላገኘሁት መልካም ትብብር እገዛ አድርገውልኛል፡፡

በመቀጠል ከትምህርት ክፍሌና ከዞኑ ባህልና ቱሪዝም መምሪያ የተጻፉልኝን የትብብር ደብዳቤዎች ይዤ ለቅድመ ጥናት ስራ የሄድሁት ወደ መርሐ ቤቴ ወረዳ ነበር፡፡ ይህ የቅድመ ጥንት ዳሰሳ የተከናወነው ከመጋቢት 22/2015 ዓ.ም እስከ መጋቢት 26/2015 ዓ.ም ድረስ ባሉት አምስት ቀናት ነው፡፡ በነዚህ ቀናት በወረዳው በነበረኝ ቆይታም ስለአካባቢው የጸጥታ ሁኔታ፣ መልክዓ ምድር፣ የአየር ሁኔት፣ ሆቴሎች፣ የትራንስፖርት ሁኔታ/አማራጭ፣ መረጃ ስለምሰበስብባቸው ቀበሌዎች ሁኔታ/ርቀት፣ መረጃ ሊሰጡኝ ስለሚችሉ የመንግስት ተቋማት እና አጠቃላይ ስለማህበረሰቡ በምልከታና በቃለ መጠይቅ መረዳት ችያለሁ፡፡ በተጨማሪም ስለ ጥናት ስራው አጠቃላይ ሁኔታ በመግለጽ በመረጃ ስብሰባ ወቅት ምን እንደምፈልግና በምን መልኩ ሊያግዙኝ እንደሚችሉ ለወረዳው የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሃላፊና ባለሙያዎች ገለጻ በማድረግ የጋራ ስምምነት መፍጠር ችያለሁ፤ፈቃደኝነታቸውንም አግኝቻለሁ፡፡ ይህንንም የቅድመ ጥናት ዳሰሳ ስራ አከናውኝ መጋቢት 27/2015 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ተመልሻለሁ፡፡

ለቅድመ ጥናት ስራ ዓለም ከተማ ቆይቸ ስመለስ ያጋጠመኝ አንድ ክስተት ተፈጠረ፡፡ ይሄውም ከአዲስ አበባ ወደ መርሃ ቤቴ ወረዳ የሚያስኬደው የጀማ ወንዝ ድልድይ በድንገት መደርመስ/መፍረስ ነው፡፡ እኔ የተሳፈርኩበት አውቶቢስ አንድ ሰዓት አካባቢ ተሻግሮ ወደ አራት ሰዓት ገደማ ድልድዩ መሰበሩን መንገድ ላይ እያለሁ ሰማሁ፡፡ በዚህ ጊዜ ከአዲስ አበባ ወደ መርሐ ቤቴ ወረዳ ለመሄድ የተሻለውና ብቸኛው መንገድ ድንገተኛ አደጋ ሲገጥመው ስራዬ ይስተጓጉልብኝ ይሆን? የሚል ከፍተኛ ስጋት ፈጥሮብኝ ነበር፡፡ ሆኖም ወደ አዲስ አበባ በተመለስሁ በጥቂት ቀናት ውስጥ አማረጭ መንገድ ተሰርቶ አገልግሎት መጀመሩን በብዙሃን መገናኛ በመስመቴ ስጋቴ ሊወገድ ችሏል፡፡

ሁለተኛውና ለዋናው የመረጃ ስብሰባ ስራ ወደ ወረዳው ጉዞ ያደረግሁት ሚያዝያ 9/2015 ዓ.ም ነው፡፡ ወቅቱ የፋሲካ ሰሞን በመሆኑ የትራንስፖርት ችግር ሊገጥመኝ እንደሚችል ብገምትም ያን ያህል የከፋ ይሆናል ብዬ ግን አልጠበቅሁም፡፡ ከአዲስ አበባ ወደ ዓለም ከተማ በቀን የሚሄደው መደበኛ መኪና አንድ ብቻ ሲሆን የተሳፋሪው ቁጥር በጣም ብዙ ነበር፡፡ ያለውን የከተማ ትራንስፖርት አማራጭ (ራይድ ትራንስፖርት) ተጠቅሜ ሌሊት 10፡30 አውቶቢስ መነሃሪያ ብደርስም እንኳን ወንበር ማግኘት ቆሞ ለመሄድም ከባድ ነበር፡፡ የትራንስፖርት ክፍያውም ከመደበኛው በሶስትና አራት እጥፍ የሚልቅ ነበር፡፡ ሆኖም ከምሄድበት ስራ ልቀር ወይም ጉዞውን ላዘገየው የምችለው ባለመሆኑ ያሉትን

አማራጮች ሁሉ መጠቀም ግድ ነበር፡፡ ስለሆነም የሚከፈለውን ለመክፈል ተስማምቼ ተራ አስከባሪዎችን ለአስቸኳይ ስራ እንደምሄድ በመለመን በትርፍ ቆመው ከሚሄዱት ተሳፋሪዎች አንዱ ሆኘ ቆሜ ለመሄድ ወስኜ ጉዞየን በእቅዴ መሰረት አከናውኛለሁ፡፡ በመቀጠል ዓለም ከተማ እንደደረስሁ ማረፊያዬን ካመቻቸሁ በኋላ ስለቀጣዩ ቀን ስራ ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃላፊና ባለሙያዎች ጋር በአካልና በስልክ በመወያየት ቀጠሮ በመያዝና እቅድ በማውጣት የእለቱን መርሐ ግብር ማጠናቀቅ ችያለሁ፡፡

በንግግራችን መሰረት ሚያዝያ 10/2015 ዓ.ም ከጽ/ቤት ኃላፊዋ ከወ/ሮ የማሪያምወርቅ በላይሁንና ከባህል ዘርፍ ባለሙያዋ ወ/ሮ ህይወት ታደሰ ጋር ጧት ሶስት ሰዓት ተገናኝተን ወደ አፈዘዝ በርቃቶ ቀበሌ የሚደረገውን ጉዞና በቀበሌው አስተዳደር ሊደረግ የሚገባውን ቅድመ ዝግጅት አመቻቸን፡፡ ወቅቱም ሆነ አካባቢው የጸጥታ ስጋት ያለበት ስለነበር የእነሱ እገዛና አብሮነት በጣም አስፈላጊ ነበር፡፡ ከዚያም ባለ ሶስት እግር ተሽከርካሪ (ባጃጅ) ኮንትራት ይዘን የመጀመሪያ ምልከታ ወደምናደርግበት አፈዘዝ ቀበሌ ጉዞ አደረግን፡፡ እንደ ወረዳው እቅድና ልማት ጽ/ቤት መረጃ ቀበሌው ከዓለም ከተማ በ12 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ የገጠር ቀበሌ ነው፡፡ በቀበሌው 3,194 ወንድና 2,791 ሴት በድምሩ 5,987 ህዝብ የሚኖርበት ሲሆን ከዓለም ከተማ ወደ ቀበሌው ማእከል የሚያደረስ የጠጠር መንገድ አለው፡፡ ወደቦታው እንደደረስን የቀበሌው ምክትል ሊቀመንበር አቶ ስንታየሁ በፈገግታ ተቀበለን፡፡ ምንም እንኳን የወረዳው የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሃላፊዋ ቀድማ ማስረዳቷን ባውቅም ጨዋታው እስኪጀምር ድረስ የመጣንበትን ዓላማ በድጋሚ በማስረዳት ፈቃዳቸውን አገኘን፡፡

ቀጥሎ ያመራነው ጨዋታው ወደሚከወንበት በአካባቢው አጠራር “ጋርዳ” ወደሚባለው ሜዳ ነበር፡፡ ሜዳው በየዓመቱ ጨዋታው የሚከወንበት ቦታ ሲሆን በቀበሌው አማካይ ቦታ ላይ የሚገኝ የወል መሬት ነው፡፡ ስንደርስ ወጣት ወንዶችና ጥቂት እናቶች የሜዳውን ዙሪያ ከበው አብዛኛዎቹ ተቀምጠው፣ ጥቂቶች ደግሞ ቆመው ትዕይንቱን ይመለከቱ ነበር፡፡ በሜዳው መሃል በእድሜና በቁመት የሚቀራረቡ ልጃገረዶች በቡድን በቡድን በመሆን የተለያዩ ጨዋታዎችን ይከውኑ ነበር፡፡ እኛም በየቡድኖቹ ጨዋታ በመቅረብ የመመልከት፣ አስፈላጊ መረጃዎችን በጽሁፍ፣ በድምጽና ምስል የመያዝ፣ ለቃለ መጠይቅና ለቡድን ወይይት ፈቃደኛ የሆኑ መረጃ ሰጭዎችን በተናጠልና በቡድን የመጠየቅና የማወያየት

ስራችንን እስከ ምሽቱ 12፡30 ድረስ ስናከናውን ቆይተንና የእለቱን መርሃ ግብር አጠናቀን ለቀጣዩ ቀን ተግባር ቀጠሮ በመያዝ በመጣንበት ሁኔታ ወደ ዓለም ከተማ ተመለስን፡፡

በሚቀጥለው ቀን ማለትም በ11/08/2015 ዓ.ም ያመራነው ወደ ግሬት ወቸወርኝ ቀበሌ ነበር፡፡ ግሬት ቀበሌ ከዓለም ከተማ በ16 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ ቀበሌ ስትሆን 3,346 ወንድና 2,953 ሴት በድምሩ 6,299 ህዝብ የሚኖርባትና ወደቀበሌው የሚያስኬድ የጠጠር መንገድ ያላት የገጠር ቀበሌ ናት፡፡ ወደ ቀበሌው የሄድነው በየእለቱ ወደ አካባቢዉ እቃና ሰው በምታጓጉዝና ክላሽንኮቭ ጠመንጃውን ጭኑ ላይ አስቀምጦ በሚነዳ/በሚሾፍር/ ሾፌር የምትዘወር ብቸኛ ፒክ አፕ ተሽከርካሪ ነበር፡፡ እንግድነቱ ጠቅሞኝ ጋቢና አግኝቼ ብጓዝም መኪናዋ ካላት የመጫን አቅም በላይ ብዙ እቃና ሰው በጀርባዋ ተሸክማ ነበር፡፡ የመኪናዋ ጭነት ከመንገዱ አስቸጋሪነት ጋር ተዳምሮ ጉዞውን አስፈሪ ቢያደርገውም ሌላ አማራጭ ባለመኖሩ ነባራዊውን ሁኔታ መጋፈጥ ነበረብኝ፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በዚህ ቀበሌም ሊቀመንበሩ አቶ ደረሰ አቀባበል አድርጎልናል፡፡ ምንም ዓይነት ስጋት እንዳይሰማንና ስራችንን እስክንጨርስ አብሮን እንደሚቆይ ከነገረን በኋላ እኛም ወደ ቀበሌው የመጣንበትን ዓላማ አስረዳን፡፡ የጋራ ስምምነት ከፈጠርን በኋላ በአካባቢው "ገበያ" እየተባለ ወደሚጠራው ሜዳ አመራን፡፡ በዚህ ቀበሌም የተመለከትነው ተመሳሳይ ሁኔታ ነው፡፡ በርከት ያለ ታዳሚ የሜዳውን ዙሪያ ከብቦ የሚመለከት ሲሆን በቡድን በቡድን የሆኑ ወጣት ሴቶች/ልጃገረዶች/ በሜዳው መሐል ልዩ ልዩ ጨዋታዎችን ይከውኑ ነበር፡፡ ዙሪያውን ያለው ሰው ጥሩ የሚጫወቱትን ያበረታታል፣ በድምጽና በጭብጨባ ይደግፋል፣ አልፎ አልፎም አስተያየት ይሰጣል፡፡ እኛም ወደየጨዋታው ከዋኞች በመቅረብ የጽሁፍ፣ የድምጽና የምስል መረጃዎችን መውሰድ ችለናል፡፡ ፈቀደኛ ተወያዮችንና መረጃ ሰጭዎችን በግልና በቡድን በማወያየትና በመጠየቅ ለጥናቱ ጠቃሚ መረጃ ሰብስበናል፡፡ በዚህ ሁኔታ የእለቱን መርሐ ግብር ጨርሰን ወደ ማረፊያችን ተመልሰናል፡፡

ከሚያዝያ 12/2015 ዓ.ም እስከ መጋቢት 15/2015 ዓ.ም ድረስ ባሉት አራት ቀናት ዓለም ከተማን ጨምሮ ከወረዳው መቀመጫ ከተማ በ5 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምተገኘውና 3,052 ወንድና 2,707 ሴት በድምሩ 5,759 ህዝብ በሚኖርባት በአገሪት ቁም አምባ ቀበሌ እና የ3,020 ወንድና 2,586 ሴት በድምሩ የ5,606 ህዝብ መኖሪያ በሆነችውና ከዓለም

ከተማ በ12 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘዉው የሰባጌ ሀሮገንዳ ቀበሌ (የወረዳው ፕላንና ልማት የ2014 በጀት ዓመት ስታትስቲካል መጽሄት) በተመሳሳይ ሁኔታ የልጃገረዶቹን ጨዋታ በአካል በመገኘት የጽሁፍ፣ የድምጽና የምስል መረጃዎችን መሰብሰብ ችለናል፡፡

ከሚያዝያ 16/2015 ዓ.ም እስከ ግንቦት 10/2015 ዓም ድረስ ባሉት ቀናት ደግሞ በዓለም ከተማና በአካባቢው የሚኖሩ ታሪክ አዋቂዎችን፣ የሐይማኖት አባቶችን፣ ስለጨዋታው ያውቃሉ የሚባሉ የሐገር ሽማግሌዎችን፣ ተጫውተው ያሳለፉ እናቶችን፣ የባህልና ቱሪዝም ኃላፊዎችንና ባለሙያዎችን በቃለ መጠይቅና በውይይት መረጃ የማሰባሰብ ስራ ተከናውኗል፡፡ ስለወረዳው አጠቃላይ የማህበረ-ኢኮኖሚ ሁኔታ ከወረዳው የእቅድና ልማት ባለሙያዎች የጽሁፍና የምስል መረጃዎችን የመሰብሰብ ስራ ተከናውኗል፡፡ በተጨማሪም ከላይ በተጠቀሱት ቀናት የድምጽ መረጃዎችን ወደ ጽሁፍ በመቀየርና የመረጃ ጉድለት በታየባቸውና የሃሳብ መጣረስ በተስተዋለባቸው ጉዳዮች ላይ መረጃ የሚሰጡ ሰዎችን በማፈላለግ ተጨማሪና አስታራቂ ሃሳቦችን የማካተት ስራ ማከናወን ተችሏል፡፡

በወረዳው በነበረኝ የመስክ ቆይታ የህዝቡን እንግዳ ተቀባይነት፣ አክባሪነትና ተባባሪነት ለመታዘብ ችያለሁ፡፡ በሄድንባቸው ቀበሌዎች ሁሉ ብዙ ሰዎች በቤታቸው እንድንጋበዝ ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ ነበር፡፡ በገባንባቸው ቤቶችም ቤት ያፈራውን በማቅረብ በሞቀ ፈገግታና በትህትና እንድመገብ ይጋብዙን ነበር፡፡ ሌላው የታዘብሁት 'የሸካና ጠጅ' ነው፡፡ በብዙ አካባቢዎች ጠጅ በብርሌ እንደሚቀርብ ነው የማውቀው፡፡ ከነአባባሉስ "ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ" ይባል የለ፡፡ በዓለም ከተማ "ጎድጓዲት ጠጅ ቤት" ግን ጠጅ የሚቀርበው በሸክና ነው፡፡

ምስል 3፦ በጎድጓዲት የሸክና ጠጅ ቤት
(አጥኝው፣ የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሃላፊና ባለሙያ)




(ዓለም ከተማ፣ በአጥኝው ካሜራ የተነሳ፣ ሚያዝያ 2015 ዓ.ም)

ሌላው በቆይታዬ የታዘብሁት ነገር በገጠርና በከተማ አብዛኛው ወጣት መሳሪያ መታጠቅና ምሽት አካባቢ የሚሰማ የጥይት ተኩስ ነው። ከምሽቱ አንድ ሰዓት አካባቢ ጀምሮ ያማያቋርጥ የጥይት ተኩስ ይሰማ ነበር። ተኩሱ እስከ እኩለ ሌሊት ይቀጥል ስለነበር እንኳን ለእኔ አይነቱ እንግዳ ቀርቶ ለነዋሪውም ምቾት የሚነሳ ይመስለኛል።

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ ሦስት ንዑሳን ጉዳዮች ተዳስሰዋል፡፡ እነዚህም የጽንሰ ሃሳብ ማሕቀፍ፣ የንድፈ ሃሳብ ቅኝትና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ናቸው፡፡ የጽንሰ ሃሳብ ማሕቀፍ በሚለው ክፍል ከፎክሎርና ሌሎች ተዛማጅ የሙያ መስኮች የተወሰዱ ጽንሰ ሃሳባዊ ጉዳዮች ተካትተዋል፡፡ የተዳሰሱት ሃሳቦች ጥናቱ የሚያጠነጥንባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ በመለየት የቀረቡ ናቸው፡፡

የንድፈ ሃሳብ ቅኝት በሚለው ክፍል ደግሞ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች በምን ዓይነት ንድፈ ሃሳብ እንደተተነተኑ የሚያሳዩ ጉዳዮች ቀርበዋል፡፡ ይህ ክፍል መረጃዎችን ለመለየት፣ ለመመደብ፣ ትርጉም ያለው ትንተና ለመስጠት ያገዘ ነው፡፡

ሶስተኛው ጉዳይ የተዛማጅ ጥናት ቅኝት የሚለው ንዑስ ክፍል ሲሆን በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች ተዳሰውበታል፡፡ ይህ ጥናት ከቀደምት ጥናቶች በምን ይመሳሰላል? በምንስ ይለያያል? የቀደምት ጥናቶቹ ጥንካሬ የት ላይ ነው? ክፍተታቸውስ ምንድን ነው? ይህ ጥናት የትኛውን ክፍተት ለመሙላት ተሰራ? የሚሉ ነጥቦች ተዳስሰዋል፡፡

### 2.1 ጽንሰ ሃሳባዊ ዳሰሳ

#### 2.1.1. ቡድን (ፎክ ቡድን)

በፎክሎር እሳቤ ቡድን ማለት የጋራ ፍላጎትና ልምድ ያላቸው ሰዎች የፈጠሩት ስብስብ ማለት ነው፡፡ ቡድን ወይም ‹‹ፎክ›› የሚለውን ቃል ለማስረዳት የጋራ ጉዳይ ያሰባሰባቸው ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ስብስብ ፎክ ቡድን/ ቡድን እንደሚባል Dundes እንደሚከተለው ያስረዳል፡፡

> *The term ‘folk’ can refer to any group of people whatsoever who share at least one common factor. It does not matter what the linking factor is it could be a common occupation, language, or religion- but what is important is that a group formed for whatever reason will have some traditions which it calls its own. A member of the group may not know all other members, but he will probably know the common core of traditions belonging to the group, traditions which help the group have a sense of group identity. (Dundes 1980:6)*

የቀረበው ብያኔ ከጋራ ቋንቋ፣ ሃይማኖት ወይም ስራ በላይ የቡድኑ አባላት ለመሰባሰብ ምክንያት የሆናቸውን የጋራ ምክንያት የሚያውቁ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ቡድኑም ሆነ እያንዳንዱ የቡድኑ አባል ማንነቱን የሚገልጽበትና ለምን የቡድኑ አባል እንደሆነ የሚሰጠው ምክንያት አለው ማለት ነው፡፡ ለቡድኑ መሰባሰብ ምክንያት የሆነው ጉዳይ ባህላዊ መሰረት ያለው ነው፡፡ ይህ ባህላዊ መሰረት ደግሞ ኢመደበኛነትን፣ ውስብስብ አለመሆንንና ከመደበኛ ይልቅ ልማዳዊ ገፅታን የሚጠቁም እንደሆነ (Sims and Stephens 2005፡ 34) ይገልፃሉ፡፡

የፎክ ቡድን (ቡድን) መመስረቻዎች ብዙ ናቸው፡፡ ሆኖም Sims and Stephens (2005፡38) የጠቀሷቸው መስፈርቶች ጠቅለል ያሉና ሰፋ ያለውን የመመስረቻ ዘዴ ገላጮች ስለሆኑ ቀጥለን እንመለከታቸዋለን፡፡ የመጀመሪያው ቀረቤታ(proximity) ነው፡፡ የዘር ሃረግን፣ አካባቢን፣ ክልልንና አገርን መሰረት አድርጎ ፎክ የሚፈጠርበት መንገድ ነው፡፡ ሁለተኛው አስፈላጊ፣ አስገዳጅ ወይም አጋጣሚያዊ ሁነት (necessity, obiligation or cercumsitance) ሲሆን ሰዎች ለህይወታቸው አስፈላጊ በሆኑ ምክንያቶች (ምሳሌ፡- ጉርብትና)፣ በተፈጥሮ አስገዳጅነት (ምሳሌ፡- በፆታ) እንዲሁም በአጋጣሚ (ለምሳሌ፡- ሰዎች የሚሰፍሩበት አካባቢና የሚከተሉት እምነት) የፎክ ቡድን እንደሚመሰርቱ የሚያሳይ ነው፡፡) ተመሳሳይ ወይም የተለመደ ግንኙነት (regular interaction) ሌላው ቡድን ለመመሰረት የሚያስችል ምክንያት ሲሆን በጓደኝነት፣ በጉርብትና፣ በትምህርት ቤት ወ.ዘ.ተ. ሰዎች ቋሚና ዘወትር የሚፈጽሙት ተግባር ይኖራል፡፡ ይህም ተግባራቸው አንድ የፎክ ቡድን ለመመስረት ምክንያት ይሆናል፡፡ የመጨረሻው ምክንያት/መስፈርት ፍላጎት ወይም ክህሎት በመጋራት (shared interest or skills) ሲሆን ይህም ልዩ ችሎታና አቅም ያላቸው ሰዎች ያን ችሎታቸውን ለመጋራት ይገናኛሉ፡፡ ያን ልዩ ችሎታ በመጋራት ሂደትም የፎክ ቡድን ይመሰርታሉ፡፡

በጠቅላላው ዘር፣ ጎሳ፣ ፆታ፣ ስራ፣ መደብ፣ ዕድሜ፣ የጋራ ፍላጎት ወዘተ ለመሰባሰባቸው ምክንያት ሆኗቸው ከመደበኛ ህጎች ይልቅ ልማዳዊ በሆነ መንገድ የተመሰረቱና የሚኖሩ ሰዎች ስብስብ ፎክ ቡድን እንደሚባል ከቀረበው ገለጻ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ ጥናት ትኩረት የተደረገባቸው ልጃገረዶች ጾታን፣ እድሜን፣ ፍላጎትንና ሃይማኖትን መሰረት አድርገው የተሰበሰቡ ቡድን መሆናቸውን እንገነዘባለን፡፡

### 2.1.2. ሃገረሰባዊ ልማድ እና ሃገረሰባዊ ጨዋታ

#### 2.1.2.1 ሀገረሰባዊ ልማድ

የፎክሎር ዋና ዋና ዘውጎች ተብለው የሚታወቁት አራት እንደሆኑና እነሱም ሥነቃል (Oral Literature) ፣ ሃገረሰባዊ ልማድ (folk custom) ፣ ሃገረሰባዊ ትውን ጥበባት (folk arts) እና ቁሳዊ ባህል (material culture) እንደሚባሉ (Dorson 1972፡3-4፣ ፈቃደ 1991፣10) ያስረዳሉ።

ከአራቱ ዘውጎች አንዱ ሃገረሰባዊ ልማድ (folk custom) ነው። ሃገረሰባዊ ልማድ አንድ ማህበረሰብ በተደጋጋሚ የሚከውነው፣ ቅደም ተከተላዊ ሥርዓት ያለው ማህበረሰባዊ ጥበቦች መጠሪያ እንደሆነ Dorson (1972፡3) ይገልጻሉ። እንዲሁም Vehrer (2017፡368) ሃገረበሰባዊ ልማድ አንድ ማህበረሰብ አብሮ በመኖር ሂደት በረጅም ጊዜ ልምምድና ድግግሞሽ የሚያዳብረው ማህበረሰቡም ተቀብሎ በየጊዜው የሚደጋግመው ድርጊትና የባህል አካል እንደሆነ ያስረዳሉ።

ከቀረቡት ገለጻዎች ሀገረሰባዊ ልማድ አንድ ማህበረሰብ ደጋግሞ የሚከውነው፣ ቅደም ተከተላዊ ስርዓት ያለው የማህበረሰባዊ ጥበቦች መጠሪያ እንደሆነ እና አብሮ በመኖር ሂደት በረጅም ጊዜ ልምምድና ድግግሞሽ የሚያዳብረው፣ ማህበረሰቡም ተቀብሎ በየጊዜው የሚደጋግመው ድርጊትና የባህል አካል እንደሆነ መረዳት ይቻላል።

ሰዎች በጋራ ሲኖሩ በጋራ የሚቀበሉት፣ የሚያምኑት፣ የሚከተሉት፣ የሚያመልኩት፣ ጀግና አድርገው የሚተክሉት፣ እንደ ነጻ አውጭ የሚቆጥሩት፣ አምላክ፣ መንፈስ፣ የቡድን መሪ፣ ይፈጥራሉ። እነዚህ የተገለጡበት፣ የጀግንነት ስራ የከወኑበት እና መሰል ነገር የፈጸሙት ቀንም ይኖራል። ይህም ቀን በማህበረሰቡ ዘንድ በልዩ ልዩ መንገዶች ይዘከራል፤ይከበራል። ሃገረሰባዊ ልማድ እነዚህን ማሰቢያ፣ ህግና ስርዓታቸውን ማስፈጸሚያ፣ ወግ፣ ልማድና ስርዓታቸውን ማስተማሪያ፣ እለት እለት አልያም በጊዜ ቀመር በሳምንት፣ በወር፣ በዓመት እየደጋገሙ የሚያከብሩበትን ሂደት የሚመለከት ነው።

> *ማህበራዊ ልማድ ሰዎች አጥብቀው የያዟቸው እምነቶችና ልማዶች መነሻ ምንጫቸውና ትርጉማቸው ምንድነው? ሰዎች በአንድ ነገር ለምን ያምናሉ? የሚያምኑባቸው ነገሮችስ ምንድ ናቸው? የተወሰኑ ልማዶችን ስለምን ይከተላሉ? የሚሉና መሰል ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚሞክር የፎክሎር ዘርፍ ነው። (ፈቃደ 1991፣13-14)*

ስለሆነም ሃገረሰባዊ ልማድ አንድ ማህበረሰብ ለህይወቱ ጉዳት ያደርሱብኛል የሚላቸውን ድርጊቶችና አስተሳሰቦች የሚያርቅበት፣ ይጠቅሙኛል የሚላቸውን ደግሞ የሚተክልና የሚያስቀጥልበት በኑሮው ውስጥ በተደጋጋሚ የሚተገብራቸው ልማዶች ናቸው።

### 2.1.2..2 ሃገረሰባዊ ጨዋታ

"ጨዋታ የሚለው ቃል በተለያዩ ማህበረሰቦች ዘንድ የተለያየ ትርጉም የሚሰጠው ቢሆንም በሰው ልጆች አእምሯዊ፣ ስሜታዊ፣ ማህበራዊና ስነ ምግባራዊ እድገት ላይ የላቀ ድርሻ ያለው ስነ ህይወታዊና ስነ ልቡናዊ እርካታ ማግኛ ነው።" (Ambretti & et al 2010፡33)። ጨዋታ ማህበራዊ ኑሮን ለማጠናከር፣ ፍቅርና መተባበርን ለማዳበር፣ ከአድካሚ ሥራ ተላቆ አንፃራዊ እረፍት ለማግኘት ተብለው የሚከወኑ እንደሆኑ ካሕሳይ (2010፣ 209) ይገልፃሉ።

በሀገረሰባዊ ልማድ ስር ከሚካተቱ የፎክሎር ዓይነቶች ውስጥ አንዱ ሃገረሰባዊ ጨዋታ ሲሆን ምንነቱን በተመለከተ ሰሎሞን (2007፣153) እና Dorson (1972፣4) ሃገረሰባዊ ጨዋታ እራስን ለማዝናናት፣ ለአካል ጥንካሬ፣ ማህበራዊ መስተጋብርን ለማጠናከር፣ ለስነ ልቡና እድገት፣ ለግለሰባዊ ጠባይ እድገት ወዘተ ሲባል የሚከወኑ ጨዋታዎችን የሚዳስስ የፎክሎር ዘርፍ እንደሆነ ያስረዳሉ። ይህም ጨዋታ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ታዳጊዎችና ወጣቶች ሁለንተናዊ እድገትና ስብዕና እንዲኖራቸው የሚያደርግ ሎር እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

ሃገረሰባዊ ጨዋታ አንድ ማህበረሰብ ይሁነኝ ብሎ ፈጥሮ የሚከውነው፣ እንደ ልማድ የሚደጋግመው የማንነቱ ማሳያ የሆኑ ጨዋታዎችን የሚመለከት ነው። ሃገረሰባዊ ጨዋታዎች የአንድን አካባቢ ባህላዊ ገጽታ የሚገልጹ እና የማህበረሰቡን እምነት፣ የውስጥ ስሜት፣ የአኗኗር ሁኔታ አፈጣጠራቸውን ጭምር የሚያሳዩ ሲሆኑ በየትኛውም ስፍራ አካባቢያዊ ባህሉ፣ የአሰራር ልምዱ፣ የህይወት ዘይቤው በሚፈቅደው መልኩ የሚከወኑ ናቸው። ሃገረሰባዊ ጨዋታዎች ከባህላዊ ልማድ ቅረሶች ውስጥ እንደ አንድ የሚቆጠሩ እንደሆኑና በልጆች ስነልቡና፣ እውቀት፣ ስሜትና እድገት ግንባታ ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖ እንዳላቸው (Kovačević and Opić 2014፤95) ያስረዳሉ። ይህም ሃገረሰባዊ ጨዋታዎች ልጆች በራስ የመተማመን አቅማቸው እንዲጨምር፣ አካባቢያቸውን እንዲያውቁ፣ ደስታና ንዴታቸውን እንዲቆጣጠሩ በማስቻል በኩል ሚና እንዳላቸው የሚያሳይ ነው።

ሃገረሰባዊ ጨዋታ ልዩ ትርጉም ያለው የማህበረሰቡ እምነት የሆነና አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታን ለማስተጋባት የሚውል የህይወት ፍልስፍና ሲሆን ጨዋታ የሚለው ቃል በቁሙ “Game” or “Play” ለሚሉ የእንግሊዝኛ አቻዎቹ ጥቅል መጠሪያ ሆኖ ሲያገለግል ይስተዋላል፡፡ የመስኩ ምሁራን እንዳሉት የእንግሊዝኛው “Game” የሚለው ቃል የራሱ የሆነ የጨዋታ ህግ ኖሮት በሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ግለሰቦች (ቡድኖች) መካከል የሚደረግ የውድድር መንፈስ ያለው የጨዋታ አይነቶችን የሚያካትት ሲሆን፣ “Play” የሚለው ደግሞ ምንም አይነት የጨዋታ ህግና የውድድር መንፈስ ሳይኖረው ሰዎች ለመዝናኛነትና ለጊዜ ማሳለፊያነት የሚገለገሉባቸው ጨዋታዎች ናቸው፡፡ (Tucker 1948፣ Eichberg 2015፣ Kramer 2000)፡፡

በሌላ በኩል የጨዋታ ዓይነቶችን ማኅተመሥላሴ ወልደመስቀል (1962፤ 86) ዝክረ ነገር በተሰኘው ስራቸው ውስጥ በአራት ከፍለዋቸዋል፡፡ እንደ ፈረስ ግልቢያ፣ ውሃ ዋና፣ አለማ ተኩስ፣ አውሬ አደን፣ ሰንጠረዥ፣ በገና መደርደር ወዘተርፈ ከሙያ የሚቆጠሩ በማለት ሲመድቧቸው ምክክት፣ ቅምምጦሽ፣ ሽምጥ፣ ገና ጨዋታ፣ እርግጫ (የእግር ቦክስ) ፣ ጮቤ መምታት ያሉትን ደግሞ የሰውነት ማፍታቻና ማጠንከሪያ በሚለው ምደባ ውስጥ አካትተዋቸዋል፡፡ አካንዱራ፣ ገበጣ፣ ተላቲን ብለው የዘረዘሩዋቸውን ጨዋታዎች ሒሳብ ያላቸው ጨዋታዎች በሚለው ምድብ ያካተቱ ሲሆን መሰንቆ፣ ዋሽንት፣ ክራር፣ እንቢልታ ወዘተ ያሉትን ጨዋታዎች ደግሞ የዜማ ድምጽ የሚሰጡ የዘፈን መሳሪያዎች በሚል ምድብ አካተዋል፡፡

ይህ የብላቴን ጌታ ማኅተመሥላሴ አመዳደብ ጨዋታ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ መሰረት ያደረገ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህንንም ሲያብራሩ “ጨዋታ አንድ የታወቀ ሙያ ባለቤት ያደርጋል፤ ሰውነትን ያፍታታል፤ ያጠነክራል፤ ጥልቅ አሳቢ እንድንሆን ያደርጋል፤ ድምጻዊ እና የዜማ ተጫዋች መሆን የሚያስችል ተሰጥኦ እንዳለን በማረጋገጥ እንድንጠቀምበት በር ይከፍታል” በማለት ስለ ጠቀሜታው ያስረዳሉ፡፡

ጨዋታ ለአካላዊ ጥንካሬና ለአእምሯዊ ንቃት ያለው ጠቀሜታ ከፍ ያለ ነው፡፡ ጨዋታዎችን የመልመድ ሂደቱም ሌሎች በትኩረት ሲፈጽሙት በማየትና በእነሱ መንገድ በመለማመድ ነው፡፡ የመልመድ ሂደቱ በፍላጎት ላይ የተመሰረተ ሆኖ በውይይትና በክርክር የበለጠ አድርጎ ለመከወን ጥረት ይደረጋል፡፡ “ጨዋታ ስራ ከሚፈጥርብን ጫና ለመነጠል፣

ለመዝናናት፣ የተለያዩ ልምዶችን ለመውሰድና ራስን ለመቆጣጠር ትልቅ አስተዋጽኦ አለው” (Reinecke 2009፡461) ።

ጨዋታ የማስተማር (ልምድ የማቅሰም) ፣ የማከም፣ መረጃ የማቀበል፣ የመጠበቅ፣ አካልን የማበርታት አምስት ተግባራት እንዳሉት Schechner (2002፤ 101) ይገልጻሉ። የተገለጹት እያንዳንዱ የጨዋታ ጥቅሞች እንደሚከተለው ተብራርተው ቀርበዋል።

**ሀ. የማስተማር (ልምድ የማቅሰም) ተግባር፡-** የሰው ልጅ ውስብስብ የሆነ ማህበራዊ ዓለም ይመራል። ይህንን ማህበራዊ ዓለም ምን እንደሚመስል? እንዴት እንደሚመራ? በማን እንደሚመራ? ወዘተ ልጆችና ወጣቶች ማወቅ እና መማር አለባቸው። ይህንን ማህበራዊ ዓለም ከማህጸንና በዘር ተምሮና ተለምዶ የሚመጣ የለም። ይህንን ማህበራዊ ዓለም የሚለማመዱት በጨዋታ መልክ ነው።

**ለ. የማከም ተግባር፡-** አሁን ባለው ዘመናዊ ጨዋታ ማከም (playe teraphy) የሚባል ህክምና ይሰጣል። ይህም ጨዋታ ለህክምና አገልግሎት እንደሚውል ማሳያ ነው። ጨዋታ ከውጥረት፣ ከጭንቀት ለማምለጥና ለመዳን ያግዛል።

**ሐ. መረጃ የማቀበል ተግባር፡-** ጨዋታ ስለአካባቢያችንና በዚያ ስለሚኖሩ ፍጥረታት መረጃ የማቀበል ተግባራት አሉት።

**መ. የመጠበቅ ተግባር፡-** ልጆችና ወጣቶች በማህበራዊ ህይወታቸው ውስጥ ያላቸውን ቦታ እንዲያውቁ፣ ባላቸው የፎክ ቡድን ውስጥ አካባቢያቸውንና የቡድኑን አባላት እንዲጠብቁ እድል ይሰጣል።

**ሠ. ለአካል ብርታት፡-** ጨዋታ ዝላይ፣ ፈንጥዝያ፣ ልፊያ፣ መውደቅ መነሳት፣ ውድድር (ፉክክረ) ስላለበት ለአካል ግንባታና ብርታት ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል።

ሃገረሰባዊ ጨዋታዎች ባህልን ለማስተዋወቅና ማህበራዊነትን ለማጠናከር የላቀ ሚና አላቸው። በዚህም መሰረታዊ ልምዶችን ለትውልድ በማሻገር፣ አዎንታዊና አሉታዊ አስተሳሰቦችን በማስገንዘብ፣ ክህሎትን በማላበስ፣ ልምድን በማበልጸግ ከፍ ያለ ጠቀሜታ እንዳላቸው የዘርፉ ምሁራን ያስገነዝባሉ። ጨዋታ ሰዎች ስለሚኖሩበት አካባቢ፣ ስላደጉበት ባህል፣ እሴትና የዓለም አተያይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ በበጎ ምግባር እንዲቀረጹና ማህበራዊ ሰላም እንዲያገኙ ያደርጋል።

### 2.1.3 ክብረ በዓል እና በዓለ ትንሳኤ

#### *2.1.3.1 ክብረ በዓል/በዓል*

በዓል የሚለውን ቃል/ሃሳብ/ ኪዳነወልድ ክፍሌ (1948፣278-279) አብዓለ፣ አከበረ፣ አስከበረ፣ አበለጠገ፣ ዕለትን በዓል አደረገ፤ ከሚለው ግስ የወጣ ሲሆን፣ በቁሙ ሲፈታም የደስታ፣ የዕረፍት ቀን፣ የዓመት፣ የወር፣ በሳምነት የሚከበር፣ ያለፈ ነገር የሚታሰብበት፣ ተዝካር፣ ሕዝብ በዓሉን በምስጢር እያሰበ ደስ ብሎትና ለብሶ አጊጦ የሚዘፍንበት፣ የሚዘምርበት፣ ዕልል የሚልበት፣ ሽብሸባ፣ ቀኒጽ/መፈንጨት፣ መዝለል፣…/፣ ነፈርዓጽ/ዝላይ/ የሚያደርግበት፣ ሲያረግድ እስክስታ ሲወርድ ባንገቱ የሚቀጭበት፣ እንደ ጥጃ የሚፈነጥዝበት ዕለት እንደሆነ ያብራራሉ፡፡

ክብረ በዓል ለበዓል ክብር ሲባል የሚደረግ ማህሌት፣ ዘፈን፣ ንግስ፣ እልልታና ደስታ እንዲሁም ስራ አለመስራት መንገድ አለመሄድ እንደሆነ በማስረዳት፣ ኃይማኖታዊና ባህላዊ ይዘት እንዳለው ደስታ (1962፣63) ይገልጻሉ፡፡ ክብረ በዓል ሲባል በዓላቱ የሚታሰቡበት ቀናት ብቻ ሳይሆኑ ከበዓላቱ ጋር ተያይዘው የሚከወኑትንም ፎክሎራዊ ጉዳዮች ማለትም እንደ ዘፈን፣ እልልታ፣ ጭፈራ፣ ጌጣጌጥ፣ ወዘተ ያሉትን ያጠቃልላል፡፡

ክብረ በዓላት በቋሚነት በተያዘ ጊዜ እየተደጋገመ በራሱ ደንብ መሰረት የሚከወን ስርዓት ነው፡፡ በአጠቃላይ ክብረ በዓላት ማህበረሰቡ በተደራጀና በተቀናጀ ሁኔታ የሚያከብራቸውና በርካታ የፎክሎር ዓይነቶች የሚከወኑባቸው ዕለት/ዕለታት/ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡

የበዓልን አጀማመር በተመለከተ በዓልን የጀመረው ራሱ እግዚአብሔር እንደሆነ ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ በዘፍጥረት ምእራፍ ሁለት ቁጥር ሁለት እንደተገለጸው ክርስቶስ ዓለምንና በውስጧ የሚኖሩትን ሁሉ ለስድስት ተከታታይ ቀናት ከፈጠረ በኋላ በሰባተኛው ቀን እረፍት አድርጓል፡፡

> *እግዚአብሔር ስራን ፍጥረትን በመፍጠር ሲጀምር ለፈጠረው ፍጥረት መለኪያ መወሰኛ ጊዜንም አብሮ ፈጥሮአል፡፡ ጊዜውንም በሰባት ዓይነት ምህዋራት /አምዶች/ ከፍሎታል፡፡ በሰባቱ ዕለታት፣ ዑደቱንም ብርሃንና ጨለማን በማፈራረቅ እንዲታወቅ ካደረገ በኋላ "ጠዋትም ሆነ ማታም ሆነ አንድ ቀን" በማለት ወስኖታል፡፡ ከዚህ በኋላም በስድስቱም ቀናት አከታትሎ ከፈጠረ በኋላ በሰባተኛው ቀን ዐረፈ፡፡ (ዘፍጥረት ምዕ.1-2)*

የበዓላትን መከወኛ ምክንያት በተመለከተ ዘሪሁን (1998፣ 54) ሰዎች እንደየአካባቢያቸውና እንደየባህላቸው ወቅታቸውን እየጠበቁ የሚመጡ ክብረ በዓላትን ያከብራሉ፡፡ አንዳንዶቹ ክብረበዓላት በእምነት ላይ የተመሠረቱ ሀይማኖታዊና መንፈሳዊ ሲሆኑ የቀሩት ደግሞ ዓለማዊ ናቸው፡፡ የዘመን መለወጫ፣ የጥምቀት፣ የታቦት ንግስ፣ የጾም ፍች፣ የልደት፣ የአረፋና የመውሊድ በዓላትን በምሳሌነት መጥቀስ እንደሚቻል ያስረዳሉ፡፡

ክብረ በዓላቱ ሃይማኖታዊ፣ መንፈሳዊና ዓለማዊ እንደሆኑ ሁሉ በየክብረ በዓላቱ የሚከወኑ ቃላዊ ግጥሞችና ልዩ ልዩ ክዋኔዎች መንፈሳዊና ዓለማዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከዋኙ ማህበረሰብ ወይም ቡድን እነዚህን ቃል ግጥሞች በመጠቀም በበዓላት ቀናት ክንዋኔዎችን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

በመርሐ ቤቴ የፋሲካ ጨዋታም ልጃገረዶች የትንሳኤ በዓልን በመጠበቅ በዓመት አንድ ጊዜ በመሰባሰብ የተለያዩ ጨዋታዎችን በመከወን በደስታና በፈንጥዝያ ያከብራሉ፤ መስተጋብራቸውን ያጠናክራሉ፡፡

### *2.1.3.2 በዓለ ትንሳኤ*

በዓለ ትንሳኤ የሚባለው ከእለተ ፋሲካ እሁድ እስከ ዳግም ትንሳኤ እሁድ ያሉትን ቀናት በመውሰድ ነው፡፡ የጌታችን ትንሳዔ አስቀድሞ በትምህርቱ (ዮሐ. 10፡17-18) “ነፍሴን ደግሞ አነሳት ዘንድ አኖራታለሁና ስለዚህ አብ ይወደኛል፡፡ እኔ በፈቃዴ እኖራታለሁ እንጅ ከእኔ ማንም አይወስዳትም፡፡ ላኖራት ስልጣን አለኝ፤ ይህችን ትዕዛዝ ከአባቱ ተቀብያለሁ” ተብሎ እንደተገለጸው ለሰው ልጆች ቤዛ ለመሆን ሲል ያን ሁሉ መከራ በመቀበል በመስቀል ላይ ውሏል፤ የሞትን ጽዋም ተቀብሏል፡፡ በሶስተኛወም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነስቷል፡፡ በመለኮታዊ ኀይሉ ከሙታን ተለይቶ የተነሳባትን ቀን ክርስቲያኖች በልዩ ሁኔታ ያከብሯታል፡፡

> *በዚህም መሰረት ጌታችን አስቀድሞ እንደተናገረው ራሱን ለዓለሙ መስዋዕት አድርጎ አቀረበ፤በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞተ፡፡ በእለተ ዓርብ በአዲስ መቃብር ከተቀበረ በኋላ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል፣መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል በሦስተኛው ቀን ተነሣ፡፡ ይህች ጌታችን ከሙታን ተለይቶ የተነሳባት ዕለት ትንሳዔ ትባላለች፡፡ ትንሳኤ ከሁለት ወር /54 ቀናት/ ዐቢይ ጾም በኋላ የምትመጣ ዕለት በመሆኗ እጅግ በናፍቆት ትጠበቃለች፡፡ (ብርሃኑ 2013 ፡83-84)*

የትንሳዔ በዓል መከበር የጀመረው በዚያው በመጀመሪያዎቹ ዘመናት እንደነበረ ቅዱስ ጳውሎስ ራሱ ለቆሮንቶስ ምዕመናን በጻፈት በመጀመሪያይቱ መልዕክቱ ላይ ስለትንሳዔ

በዓል አከባበር ጽፏል፡፡ ሐዋሪያው በ1ኛ ቆሮ. 5፡6-8 ባሰፈረው መልዕክቱ "እንዲህ ያለ እርሾ እንዳላችሁ አዲሱን ሊጥ ትሆኑ ዘንድ አሮጌውን እርሾ አስወግዱ፡፡ ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዷልና፡፡" እያለ የሚገልጸው የሚገስጻቸውም ወገኖቹ ከአሮጌው በዓል /ከቂጣ በዓል/ ወጥተው ወደ አዲሱ በዓል ወደ በዓለ ትንሳኤ እንዲሸጋገሩ ነው፡፡ (ብርሃኑ 2013፡85)

*ዕለተ ትንሳኤ የሰው ልጆች ከመከራ ቀንበር የተፈቱበት የድኅነትና የነጻነት ዕለት መሆኗን የሃይማኖቱ አባቶች በልዩ ልዩ ስያሜ እናደሚጠሯት ፍትሐ ነገስትን በመጥቀስ ብርሃኑ* (2013) እንደሚከተለው ያስረዳል፡፡

> *ከዚያም በኋላ ያሉት አበው ስለዚህ በዓልና ስለአከባበሩ ተናግረዋል፡፡ ዮስጢኖስ ሰማዕት (100-165) በዓሉን በዓለ ፋሲካ እያለ ሲጠራው፣ ቂርሎስ ዘኢየሩሳሌም (315-386) ደግሞ የድኅነታችን ቅዱስ ቀን፣በዓለ ድኅነታችን /holy day of saluation/ ይለው ነበር፡፡ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙም (1323-389) ዕለቲቱን የእለታት ንግስት፣ በዓሉንም የበዓላት በዓል፣ የክብራችን ሁሉ ክበር ሲል ይገልጻቸው ነበር፡፡ (ብርሃኑ 2013፡85)*

በአጠቃላይ ትንሳኤ በክርስቶስ ለሚያምኑ የደኅንነታቸው ቤዛ የሆነው እየሱስ ክርስቶስ ስለሰው ልጆች ሐጢአት ማስተሰረያ ሲል ክቡር ደሙን አፍስሶ፣ የመስቀል ሞት ሞቶ፣ ተቀብሮ፣ በሶስተኛው ቀን ሞትን ድል አድርጎ የተነሳበት በክርስቲያኖች ዘንድ በልዩ ሁኔታ የሚከበርና የሚዘከር በዓል ነው፡፡

*ይህን ሃይማኖታዊ በዓል መነሻ በማድረግ በተለያዩ አካባቢዎች የተለያዩ መንፈሳዊና* ባህላዊ ሥርዓቶች ይከወናሉ፡፡ ከነዚህም መካከል በመርሐ ቤቴ ወረዳ የሚከወነው የልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ አንዱ ነው፡፡

## 2.2. ንድፈ ሃሳባዊ ማሕቀፍ

ለዚህ ጥናት የተመረጡ ሁለት ንድፈ ሃሳቦች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ ይሄውም የጨዋታው ክዋኔ ሂደት በክዋኔያዊ ንድፈ ሃሳብ (Performance Theory) መሰረት የተዳሰሰ ሲሆን የጨዋታው ማህበረሰባዊ ፋይዳ ደግሞ በተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ (Functional Theory) መሰረት ታይቷል፡፡

### 2.2.1. **ክዋኔያዊ ንድፈ ሃሳብ** (Performance Theory)

በ20ኛው ክፍለ ዘመን ብቅ ካሉት ዘመናዊ የፎክሎር ጥናት ንድፈ ሃሳቦችና ፈለጎች መካካል የክዋኔ ንድፈ ሃሳብ አንዱና ዋነኛው እንደሆነና ይህ ንድፈ ሃሳብ አንድን የፎክሎር ዘውግ ከነሙሉ ገጽታው፣ ከነአጠቃላይ ምልዓቱና ጥበባዊነቱ ለማጥናት ተመራጭ እንደሆነ Magoulick (2009) ያስረዳሉ፡፡

የፎክሎር ጥናት ቀድሞ ይዘወተር ከነበረው መረጃን የመሰብሰብና የማደራጀት (collecting and documenting) ክንውን ወጥቶ የአንድን ማህበረሰብ ባህል ተፈጥሮአዊና ጥበባዊ አቀራረብ በተሟላ መንገድ ለማጥናት የሚያስችል ንድፈ ሃሳብ የመጣውና ከፍተኛ የአመለካከት ለውጥ ብቅ ያለው በ1960ቹ እንደሆነ የሚከተለው ሃሳብ ያስረዳናል፡፡

> *Folklore and ethnography shifted perspective in the 1960's from collecting and categorizing to synthesizing and understanding peoples and their creations in their own terms. Such re-imaginings gave birth to performance theory. The insights and methods of previous generations of scholars inevitably change based on new or fine-tuned theories that better fit contemporary methods, goals, or insights. Performance theory remains extremely useful and valid for contemporary folklorists, especially those working with field-collected narratives. (Mary Magoulick 2009:1)*

ክዋኔ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ዋና ጉዳይ/ፅንሰ ሃሳብ/ ነው፡፡ ክዋኔ በቦታ፣ በሁኔታና በጊዜ የተወሰነ፣ ተለዋዋጭ ባህሪ ያለው፣ ሂደታዊ፣ በቃል በድርጊትና በቁሳቁስ የሚቀርብ ማህበራዊ ጥበብ ሲሆን ውበት ያለው፣ የተቀናጀ፣ በድምጽ ቅላጼና በአካል እንቅስቃሴ ታጅቦ ተደጋግሞ በመቅረብ የግለሰብን ብሎም የቡድንን ማንነት መገንባት የሚችል ድርጊት/አቀራረብ/ እነደሆን kapchan እንደሚከተለው ያሰረዳሉ፡፡

> *Performances are aesthetic practices - patterns of behavior, ways of speaking, manners of bodily comportment - whose repetitions situate actors in time and space, structuring individual and group identities. Insofar as performances are based upon repetitions whether lines learned, gestures imitated, or discourses reiterated they are the generic means of tradition making. (kapchan1995:379)*

ክዋኔ ውበታዊ የሆነ የድርጊት ባህሪ፣ የንግግር ዘዴ፣ በጊዜና በቦታ የተገደበ፣ በአካል የሚከወን፣ በታወቀ መዋቅር በከዋኞች የሚቀርብ ከመሆኑም በተጨማሪ በተደጋጋሚ የሚፈፀም፣ በግልና በቡድን የሚዋቀር የማንነት ማሳያ ሲሆን የፎክሎርን ፅንሰሃሳብ

የሚመራ ውበት ያለው ጥበባዊ ድርጊት እንደሆነ እና የፎክሎር ጥበባዊ ድርጊት ከዋኝ፣ ቦታ፣ ተመልካች እና የክዋኔውን ሁኔታ እንደሚያካትት Bauman (1992) ያስረዳሉ።

ክዋኔ መጀመሪያና መጨረሻ ባለው ማዕቀፍ ተቀንብቦ የሚቀርብ ክንውን ሲሆን፣ ክንውኑም በዙሪያ ገባው አውድ የሚመነጭ፣ ለታዳሚዎቹ ክፍት የሆነና በእይታ ወይም በቁሳቁስ ይፋ የሚሆን ድርጊታዊ መግባቢያ እንደሆነ ያስረዳሉ።

ከዋኙ ስነቃሉን (ፎክሎሩን) በሚያቀርብበት ባህል ልማዳዊ ህግ መሰረት የሚጠበቅበትን ጥበብ እያሟላ፣ ታዳሚው ደግሞ ከክዋኔው የሚጠበቀውን ትውፊታዊ ውበት እያገኘ እርስ በእርስ የሚፈጥሩት ተግባቦት ነው። እንዲሁም ክዋኔ ታዳሚው የከዋኙን ባህላዊ ክህሎት ገምግሞ የሚመዝንበት እና ልምድ የሚለዋወጡበት፣ ለክወናው መፍዘዝም ሆነ መድመቅ የታዳሚው ሚና ወሳኝ የሆነበት፣ ከቃላዊው ባሻገር የአካል እንቅስቃሴ፣ የፊት ገፅታ መለዋወጥ፣ የቅላፄ መቀያየርን የመሳሰሉ ቃል አልባ (Body Language) ተግባቦቶች የሚገለፁበት ድርጊታዊ የተግባቦት ዘዴ እንደሆነ ቀጥሎ የቀረበው ገለጻ ያስረዳል።

> *Performance required an adequate description of "the social context of folklore," including the time and place for the telling of specific forms; the identity of the narrators and the composition of the audience, as well as the relationship of the narrator to the text; the use of dramatic and rhetorical devices in performance; audience participation; folk classification of traditional genres and the people's attitudes toward them. (Bauman 1975፡ 95)*

ማንኛውም ክዋኔ የማህበራዊ አውድ ገለፃ ይፈልጋል። ማህበራዊ አውድ ደግሞ ፎክሎሩ የሚነገርበት ጊዜና ቦታ፣ የታዳሚዎችን ስብስብ አይነት፣ የተራኪውን ማንነት፣ ተራኪው ከፎክሎሩ ጋር ያለው ግንኙነት፣ በክዋኔው ውስጥ ያሉ ድራማዊና ገለፃዊ ቅንጣቶች፣ የታዳሚዎች ተሣትፎ፣ የፎክሎሩ ማህበራዊ ምደባና ማህበረሰቡ ለምደባው ያለውን አመለካከት ይመለከታል።

እንደ Finnegan (1992: 86-88) ክዋኔ የማንኛውም አይነት እንቅስቃሴ መሰረታዊ ጉዳይ እንደሆነ "Performance is in a sense perhaps an element in every action." ካሉ በኋላ በክዋኔ ትንተና ወቅት ፎክሎሩ ምንድን ነው? የሚቀርብበት መንገድ ምንድን ነው? የቀረበበት ቦታ፣ ጊዜና ሁኔታ ምንድን ነው? ከዋኞች እነማን ናቸው? ምን አይነት ዝግጅት አድርገዋል? ምን አይነት ባህርይ ያሳያሉ? ፎክሎሩን እንዴት እያቀረቡት ነው?

ታዳሚው ምን ምላሽ እየሰጠ ነው? በከዋኞች እንዲሁም በከዋኞችና በታዳሚው መካከል ያለው ተግባቦት ምን ይመስላል? ፎክሎሩ የሚቀርብባቸው ቃላዊና ቃል አልባ ተግባቦቶች ምንድን ናቸው? ፎክሎሩ ከዕለት ዕለት ህይወት አንፃር እንዴት ቀረበ? የተለየ ሁኔታ አለ ወይስ በተፈጥሯዊ ባህርይው ቀርቧል? የሚሉት ነጥቦች ትኩረት ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

በአጠቃላይ ክዋኔያዊ ንድፈሃሳብ አንድ ፎክሎር ምን እንደሆነ፣ መቼ፣ የት፣ በማን፣ እንዴት እንደሚከወንና ከዋኞችን ምን የጋራ ጉዳይ እንዳሰባሰባቸው፣ በመካከላቸው ያለው ጥበባዊ ተግባቦት ምን እንደሆነ የሚመረምር የፎክሎር ማጥኛ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ አንድ የፎክሎር አጥኝ በክዋኔያዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ መረጃውን ሊተነትን ሲነሳ እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች ትኩረት አድርጎ መሆን እንዳለበት መገንዘብ ያሻል፡፡

ስለሆነም ክዋኔያዊ ንድፈ ሃሳብ የዚህ ጥናት አንዱ የመተንተኛ ንደፈ ሃሳባዊ ማሕቀፍ ሆኖ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ የመርሐ ቤቴ ልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ ክዋኔ ሂደት እያንዳንዱ ቅንጣት (እንቅስቃሴ፣ የታዳሚ ተሳትፎ፣ የሚነገሩ ስነቃሎች፣ ወዘተ) ትርጉም ተሰጥቶአቸው የተተነተኑት በዚህ ንድፈ ሃሳብ ነው፡፡

### 2.2.2. ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ (Functional Theory)

ፎክሎር እንደሚከወንበት አላማና አውድ ፋይዳውም የተለያየ ነው፡፡ ፎክሎር የማስተማር፣ የማምለጭ፣ የማጠናከር፣ የመትከል እና የመግለጥ ተግባር እንዳለው ፊቃደ (1991፣17) ይገልጻሉ፡፡ የፎክሎር ተግባር የማህበረሰቡን ባህል ከትውልድ ወደ ትውልድ ከማሸጋገር (ማስተላለፍ) እና ባህላዊ ማንነትን ከማስጠበቅ ተግባርና ሚና ባሻገር ያሉት ፋይዳዎች በ Bascom (1954) እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

> *Folklore operates within a society to insure conformity to the accepted cultural norms, and continuity from generation to generation through its role in education and the extent to which it mirrors culture. To extent which folklore contrast with the accepted norms and offers socially acceptable forms of release through amusement or humor and through creative imagination and fantacy, it tends to preserve the institutions from direct attack and change. (Bascom 1954:348).*

ፎክሎር በማህበረሰቡ ውስጥ (ህግ) ተቀባይነት ያላቸው ልማዶች እንዲዘልቁ፣ እንዲጠበቁና ለትውልድ እንዲተላለፉ ያደርጋል፡፡ ባለው ፈጠራዊና ምናባዊ ባህሪው በማህበረሰቡ

የማይነኩ ወይም የማይደፈሩ ወይም ለመግለጽ የማይመቹ ሃሳቦችንና ድርጊቶች ከልማዱ ባፈነገጠ ሁኔታ ለመግለጽ ወይም ለማድረግ እድል ይሰጣል፡፡ ማህበረሰቡ በተዋዛ አቀራረብ የባህልንም ይሁን የሃይማኖትን አጥር ይጥሳል፤ ድንበር ለመዝለል እድል እንደሚሰጥና አቀራረቡ በፈጠራና በምናብ ስለሚታገዝ ማህበራዊ ግጭት እንደማይፈጥር ከቀረበው ገለጻ መረዳት ይቻላል፡፡

የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ ተገቢ ነው ተብለው ከተመረጡ የፎክሎር ጥናት የመረጃ መተንተኛ ንድፈ ሀሳቦች መካከል አንዱ ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ (functional Theory) ነው፡፡ ይህን ንድፈ ሀሳብ የተመረጠበት ምክንያት ጥናቱ ለሚያተኩርበት ርዕሰ ጉዳይ ተገቢ በመሆኑ ሲሆን፣ ይሄውም ልጃገረዶቹ የሚጫወቱት ጨዋታ ለተጠኘው ማህበረሰብ ያለውን ጠቀሜታ ለመፈተሽና ለመተንተን ተመራጭ ሆኖ ስለተገኘ ነው፡፡

ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ የተለያዩ ሎሮች ለማህበረሰቡ የሚሰጡትን ጠቀሜታ እና በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን አውዳዊ ትርጓሜ ማሳየት ላይ ያተኩራል (ሰሎሞን 2007፡75) ፡፡ ተግባራዊነት ስንል ተራ/ተለምዶአዊ/ የሆኑትን ተግባሮች ማለት ሳይሆን ክዋኔው ለቡድኑና ለማህበረሰቡ የሚሰጠው የተለየ ፋይዳ እንደሆነ "Functionalism means not just attention but exclusive attention to function." Segal (2010፡342) በማለት ያስረዳሉ፡፡ ከገለጻው የምንረዳው ንድፈ ሃሳቡ አንድ ሎር በማህበረሰቡ ውስጥ የሚሰጠውን የተለየ ፋይዳ ለማሳየት እና ለማህበረሰቡ ምን ማለት እንደሆነ ለመመርመር የሚጠቅም መሆኑን ነው፡፡

ተግባራዊነት እንደ አንድ ንድፈ ሃሳብ ብቅ ሲል ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮችን ይዞ እንደተነሳ Elliott Oring እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> *Functionalism thus emerges as a particular theoretical orientation which asserts that (1) sociocultural patterns have consequences which are independent of the conscious intentions of the actors who perform them, (2) these patterns may be explained or understood in terms of these consequences, and (3) these consequences are explanatory only if they contribute and are necessary to the proper integration and functioning of the individual or society. (Oring 976:70).*

ተግባራዊነት እንደ አንድ የተለየ የንድፈ ሃሳብ አቅጣጫ ሆኖ ሲመጣ ማህበረ-ባህላዊ ቅንብሮችን ከሚፈጽሙት ተዋናዮች ንቃተ ህሊና ውጭ የሆኑ ውጤቶች እንደአሏቸው፣ እነዚህ ቅንብሮች ከውጤታቸው አንጻር ሊገለጹ ወይም ግንዛቤ ሊፈጥሩ እንደሚችሉ እና

እነዚህ ውጤቶች (consequences) ገላጭ ሊሆኑ የሚችሉት ለግለሰቡ ወይም ለህብረተሰቡ ትክክለኛ ውህደት እና ተግባር አስተዋፅዖ ካደረጉ ብቻ እንደሆነ ከገለጻው እንረዳለን፡፡

ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ (functional Theory) በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከወን ማንኛውም ክዋኔ ያለውን ተግባርና አገልግሎት ለመመርመር ይረዳል ሲሉ Okpewho (1992:173) ያስረዳሉ፡፡ የዚህ ንድፈ ሀሳብ ዋና ትኩረት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከወን ፎክሎር የራሱ የሆነ ጠቀሜታ እንዳለው ማሳየት ነው፡፡

ማንኛውም የፎክሎር ዘርፍ በህይወት የሚኖረው የሚያበረክተው አስተዋፅኦ እስካለው ድረስ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም ማንኛውም የፎክሎር ዘርፍ የተወሰኑ ማህበራዊ፣ ባህላዊ ወይም ስነልቦናዊ ፍላጎቶችን የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡ ባህል ለማህበረሰቡ ከሚሰጠው ጥቅም አኳያ ታይቶ መዳኘት እንዳለበት Sims & Stephens(2005፤174) ያስረዳሉ፡፡ ይህም አንድ ባህል፣ ባህል ሆኖ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ለመዝለቅና እያደገ፣ እየበለጸገ፣ እንዲሁም እየተጠበቀ ለመኖር ለማህበረሰቡ የሚሰጠው አንዳች ረብ መኖር አለበት፡፡

የተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ ትኩረት ጉዳዩ በሚከወንበት ማሕበረሰብ ውስጥ ለቡድኑ አባላትና ለማህበረሰቡ በሚሰጠው ፋይዳ ላይ ነው፡፡ አንድን ፎክሎራዊ ጉዳይ ለመተንተን በማሕበረሰቡ ውስጥ ያለውን ተግባር ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ አንድ ፎክሎር ተመራማሪም በሚከወነው ጉዳይ ላይ ብቻ ሳይሆን፣ ክዋኔው ለማሕበረሰቡ ምን አይነት ትርጉምና ፋይዳ እንዳለው መገንዘብ ይኖርበታል፡፡

በአጠቃላይ ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ አንድ ፎክሎራዊ ክዋኔ ወይም የፎክሎር ቅንጣት ለማህበረሰቡ የሚኖረውን ፋይዳ ለመመርምር የሚያስችል ንድፈ ሃሳብ ነው፡፡ በዚህም መሰረት በመርሐ ቤቴ ወረዳ በልጃገረዶች የሚቀርበው የፋሲካ ጨዋታ/ክዋኔ/ ለቡድኑና ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን ጠቀሜታ (ፋይዳ) ለመፈተሽ እንዲያስችል ይህ ንድፈ ሃሳብ የጥናቱ መተንተኛ ሆኖ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

## 2.3. የቀደምት የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የተሰሩ ቀደምት ጥናቶችን ለመፈለግ የተለያዩ አብያተ መጽሐፍት እና ኤሌክትሮኒክ የመረጃ መረቦች ላይ ዳሰሳ ተደርጓል፡፡ በተደረገው ዳሰሳም በተለይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ይህ ጥናት ይዞት ከተነሳው ርዕሰ ጉዳይና ከዓላማው አኳያ ቀጥተኛ የሆነ ተዛምዶ ያለው በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተጠና ቀደምት ጥናት ማግኘት አልተቻለም፡፡

ይሁን እንጅ በጥናታቸው ርዕሰ ጉዳይ ውስጥ ባካተቷቸው ይዘቶች እና ባብራሯቸው ጽንሰሃሳቦች በተወሰነ መልኩ ከዚህ ጥናት ጋር የሚቀራረቡ ሁለት(2) የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ እና አምስት የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ቅኝት ተደርጎባቸዋል፡፡ ከጥናቶቹ መካከል ሁለት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት የቀረቡ ጥናቶች ሲሆኑ አምስቱ ደግሞ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ ፋኩሉቲ የፎክሎር (ባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል በድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የተጠኑ/የቀረቡ/ ጥናቶች ናቸው፡፡ ስለሆነም ጥናቶቹ ከእኔ ጥናት ጋር ባላቸው የተመሳሳይነት ደረጃ በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

የመጀመሪያው "የቡሄ አከባበር እና ግጥሞች በአርሲ ነገሌ" በሚል ርዕስ በዮሐንስ ታደሰ በ1986 ዓ.ም ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት ሲሆን ሁለተኛው በብርሀን አሰፋ አራጋው በ1997 ዓ.ም "የአሆላሌ ጨዋታ ክዋኔና የግጥሞቹ ይዘት ትንተና" በሚል ርዕስ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት ነው፡፡

እነዚህ ሁለት ጥናቶች በወጣቶች የሚከወኑ ጨዋታዎችን በማንሳታቸው ካልሆነ በስተቀር በጥናት ቦታ፣ በተጠኝ ጾታ፣ በርዕሰ ጉዳይ፣ በአጠናን ዘዴም ይሁን ሥነዘዴ፣ በጽንሰ ሃሳብ ዳሰሳ፣ በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ወዘተ በአጠቃላይ የኔ ጥናት ከሚከተለው የአጠናን ሂደት ጋር በሰፊው የሚለያዩ ናቸው፡፡

ቀጥሎ የቀረቡት ደግሞ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረቡ አምስት ጥናቶች ናቸው፡፡ ጥናቶቹ በቀረቡበት ጊዜ ከቀርብ ወደ ሩቅ በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ተዳስሰዋል፡፡

የመጀመሪያው ምስጋናው ብርሃኑ “ባህላዊ የልጆች ጨዋታ የማህበራዊነት ሥነልቡናን የመገንባት ፋይዳ በአለፋ ወረዳ ተተኳሪነት” በሚል ርዕስ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ለፎክሎር ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በ2012 ዓ.ም የሰራው ጥናት ነው፡፡

ጥናቱ ከይዘት አንፃር የልጆች ባህላዊ ጨዋታ በማህበራዊ ስነልቦና የመገንባት ፋይዳ ላይ ተወስኖ የተሰራ ነው፡፡ ጥናቱ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲሆን ምልከታ እና ቃለ መጠይቅን ለመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ተጠቅሟል፡፡ በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ እድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች የሆኑ ልጆችን (ተጠኝዎችን) መርጧል፡፡ በዚህ ጥናት ማህበረ ሥነልቦቡናዊ ንድፍ ሀሳብ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለመተንተን ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

በዚህም መሰረት የምስጋናው ጥናት በጨዋታ ላይ የተደረገ መሆኑ፣ ጥናቱ የተከተለው የምርምር ዘዴ፣ የተጠቀማቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡

የምስጋናው ጥናት በተካሄደበት ቦታ፣ በተጠኝዎች ማንነት፣ እድሜ፣ መረጃዎችን ለመተንተን በተጠቀመባቸው ንድፍ ሀሳቦች እና በሚጠናው የጨዋታ አይነት ከእኔ ጥናት ይለያል፡፡ ስለሆነም ፎክሎር ያለ ክዋኔ ህይወት ስለማይኖረው የእኔ ጥናት በስፋት ክዋኔውን  ይዳስሳል፡፡ የእሱ ጥናት ከሃገረሰባዊ ጨዋታዎች ፋይዳ ይልቅ በስብስቦቹ ላይ ትንተና ማድረግ እና ቅርጻቸውን ማሳየት ላይ አተኩሯል፡፡ የኔ የጥናት ትኩረት ደግሞ የጨዋታዎችን ክዋኔ አንድ በአንድ መፈተሽና ጨዋታዎቹ ለተጠኝው ቡድንና ለማህበረሰቡ ያላቸውን ፋይዳ ስለሚዳስስ ልይነቱ ይሰፋል፡፡

ሁለተኛው በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ “የሰብዕና አገነባብ በደብረታቦር ከተማና አካባቢው ሀገረሰባዊ የልጆች ጨዋታ ማሳያነት” በሚል ርዕስ በይትረፍ አየለ ለፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በ2012 ዓ.ም የተሰራ ጥናት ነው፡፡

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በደብረ ታቦር ከተማና አካባቢው አስተዳደር ማህበረሰብ የልጆች ጨዋታዎች ክዋኔን በመመርመር በልጆች አስተዳደግና አቀራረጽ ላይ ጨዋታዎች የሚኖራቸውን ፋይዳ መፈተሽ ነው፡፡ የዘውግ ምድቡን ስንመለከተው በሀገረ ሰባዊ ልማድ ውስጥ ሀገረ ሰባዊ ጨዋታን የተመለከተና በስነቃል የሚመደቡትን ለይቶ ያጠና ነው፡፡፣

ይህ ጥናት የልጆችን የስብዕና አቀራረፅ በመመርመር የተጠኘውን ማህበረሰብ እሴቶች፣ አስተሳሰብ፣ የህይወት ፍልስፍና፣ የአኗኗር ዘይቤና የማሰራጫ ስሌት ለማሳየት ሞክሯል፡፡ ጥናቱ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲሆን ለመረጃ መሰብሰቢያነት ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅና ተተኳሪ የቡድን ውይይትን ተጠቅሟል፡፡ ተግባራዊ እና ስነፍቻዊ ንድፍ ሀሳቦች ለመረጃ መተንተኛነት ውለዋል፡፡

የይትረፍ ጥናት በጨዋታ ላይ የተሰራ መሆኑ፣ በተከተለው የምርምር ዘዴ፣ በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች እና ተግባራዊ ንድፍ ሀሳብን ለመረጃ መተንተኛ መሳሪያነት መጠቀሙ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡

ጥናቱ ከተሰራበት ቦታ አኳያ የተለያየ ሲሆን የተጠኝዎችን የእድሜ ደረጃ በተመለከተ የእኔ ጥናት ታዳጊዎችን እና ወጣት ሴቶችን ያማከለ ሲሆን የይትረፍ ጥናት ደግሞ ከ7-12 ዓመት ያሉ ልጆችን የሚያካትት መሆኑ ይለየዋል፡፡ ይህ የእድሜ፣ የጾታና የቦታ ልዩነት ምክንያት የሚከሰት ለውጥ በጥናታችን ውጤት ላይ ልዩነትን ያመጣል፡፡ የይትረፍ ጥናት ክዋኔያዊ ንድፍ ሀሳብን አልተጠቀመም፡፡ ይህም ሌላው ልዩነት ሲሆን ይህንን ክፍተት ለመሙላት የእኔ ጥናት ክዋኔያዊ ንድፍ ሀሳብን ለመረጃ መተንተኛነት ተጠቅሟል፡፡

ሌላው በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ "'የንሆይ ንሆዬ' ጨዋታ አከዋወንና ስነ ልቡናዊ ፋይዳ በላይ ጋይንት ወረዳ" በሚል ርዕስ በፎክሎር (ባህል ጥናት) ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በ2013 ዓ.ም በሰሎሞን ንጋቴ መኳንንት የተሰራው ጥናት ነው፡፡

ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ በምርምር ዘዴው አይነታዊ ምርምር ዘዴን መጠቀሙ፣ በመረጃ መተንተኛ ንድፈ ሀሳቦቹና በጨዋታ ላይ ትኩረት አድርጎ መሰራቱ ያመሳስለዋል፡፡ ነገር ግን ተጨማሪ የመረጃ መተንተኛ ንድፈ ሀሳብ በመጠቀም ረገድ፣ ከጥናቱ ቦታ አንፃር የተለያየ ዞን ከመሆኑ ባሻገር እኔ ካነሳሁት ርእስ ጉዳይ አኳያ ልዩነት አለው፡፡ ሰሎሞን ስነልቦናዊ ፋይዳን ሲያጠና የእኔ ጥናት ግን ሌሎች ማህበራዊ ፋይዳዎችንም ይዳስሳል፡፡

በሌላ በኩል በውስጡ በይዘትነት የሎሞን ጥናት ያነሳቸው ጨዋታዎች የልጆችን ብቻ አልነበረም፡፡ ከልጅ እስከ አዋቂ ያለው የማህበረሰቡ አባላት የሚጫወቷቸውን ጨዋታዎች

ያካተተ መሆኑ እና ከሰብዕና ግንባታና ሌሎች ማህበራዊ ፋይዳዎች አንጻር ያላቸውን ጠቀሜታ ምን እንደሚመስል አለማመልከቱ ከእኔ ጥናት ጋር ይለያያል፡፡

አራተኛው ሀብታሙ ተሾመ በ2014 ዓ.ም “የጾታዊ ሚና አቀራረጽ ልማድ በልጆች ጨዋታ ውስጥ በሁለት እጁ እነሴ ወረዳ በደብረ ማርያም ቀበሌ ማሳያነት” በሚል ርዕስ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ያቀረበውን ጥናት ነው፡፡

ይህ ጥናት የጾታዊ ሚና አቀራረጽ ልማድ በልጆች ጨዋታ ባህላዊ/ሃገረሰባዊ ጨዋታ/ ውስጥ መመርመርን ዓላማው አድርጎ የተሰራ ጥናት ነው፡፡ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን ተከትሎ የተጠና ሲሆን ምልከታን፣ ቃለ መጠየቅና የቡድን ውይይትን በመረጃ መሰብሰቢያነት ተጠቅሟል፡፡ ባህላዊ ጫወታ፣ የልጆች ጫወታ፣ የልጆች ፎክሎር፣ ጾታዊ ሚና፣ ወዘተ የሚሉ ጉዳዮች በጽንሰ ሃሳብ ዳሰሳ ክፍል ቀርበዋል፡፡ የማህበራዊ ትምህርትና የሥርዓተ ጾታ ንድፈ ሃሳቦችን ለጥናቱ መተንተኛነት ተተቅሟል፡፡ የሃብታሙ ጥናት በጽንሰ ሃሳብ ዳሰሳው ባህላዊ ጨዋታ ማንሳቱና ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን ከመጠቀሙ በስተቀር በሌሎች ጉዳዮች ከእኔ ጥናት ይለያል፡፡ በዋናነትም ጥናቱ ባተኮረበት ርዕሰ ጉዳይ፣ በቦታ፣ በተተኳሪ ተጠኝ ቡድን፣ በመረጃ መተንተኛ ንድፈ ሃሳብ፣ ወዘተ ረገድ ልዩነቱ የሰፋ ነው፡፡

በመጨረሻ የምንመለከተው በሰላማዊት ጌታሁን በ2015 ዓ.ም “የሽውዬ እና ምሻምሾ ባህላዊ ጨዋታ ክዋኔ እና ፋይዳ በዝቋላ ወረዳ ማህበረሰብ” በሚል ርዕስ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ፣ የፎክሎር ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ ፕሮግራም በፎክሎር (ባህል ጥናት) ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የተሰራ ጥናት ነው፡፡

ይህ ጥናት ይዞት የተነሳው ርዕሰ ጉዳይ በሴቶች የሚከወን መሆኑ ወይም ተጠኝዎቹ እንስት መሆናቸው፣ ከትንሳኤ በዓል ጋር ተያይዞ የሚከውን መሆኑ፣ ጥናቱ ክዋኔና ፋይዳ ላይ ማተኮሩ፣ በምርምር ዘዴና ሥነዘዴ፣ በመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች ከእኔ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ እንዲሁም በተነሱ ቁልፍ ጉዳዮች ማለትም ባህላዊ ጨዋታና ፋይዳ ጋር ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ በጥናቱ መግቢያና በተዛማጅ ጽሁፍ ክለሳ ላይ የባህላዊ ጨዋታን ምንነት፣ ማህበራዊ ጠቀሜታ ምሁራን ካሉት አንጻር ተቃኝቶ መብራራቱ ሌላው ተመሳሳይነቱን የሚያሳይ ነጥብ ነው፡፡ በተጨማሪም ጥናቱ በዋናነት በወረዳው የሚከወኑ

የሴቶች ጨዋታዎችን ፋይዳ መመርመር ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በዚህም ከእኔ ጥናት ዓላማ ጋር በመጠኑ ያመሳስለዋል፡፡

በተቃራኒው የጨዋታውን ፋይዳ ወስኖ በማየት በኩል ከእኔ ጥናት የተለየ ነው፡፡ የእኔ ጥናት የተለያዩ ጨዋታዎችን ፋይዳና ክዋኔ አቀናጅቶ የዳሰሰ በመሆኑ ሌላው የሚለይበት ጉዳይ ነው፡፡ በተጨማሪም የሰላማዊት ጥናት ገላጭ የምርምር ዘዴን አለማጠቀሙና የስነ ፍቺ ንድፈ ሃሳብን ለመረጃ ትንተና መጠቀሙ ከእኔ ጥናት እንዲለይ ያደርገዋል፡፡

ከዚህ በላይ ሃገረሰባዊ ጨዋታ በሚለው ርእሰ ጉዳይ ላይ የተሰሩ ጥናቶች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ጥናቶች ጨዋታን ከተለያዩ አቅጣጫዎች፣ ከተለያዩ ማህበራዊና ተፈጥሯዊ መቼቶች፣ ከተለያየ ጥልቀትና ስፋት አንፃር መርምረዋል፡፡ የተዳሰሱት ጥናቶች ከርዕሰ ጉዳይ፣ ከአጠናን ዘዴ፣ ከመስክ ተሞክሮና ከሌሎችም ጉዳዮች አንፃር ሊከናወኑ የሚገቡ ጉዳዮችን በማሳየት ረገድ ለእኔ ጥናት በጎ አስተዋፅኦ አበርክተውልኛል፡፡ ከዚህ ባሻገር ጥናቶቹ በአጠቃላይ ሃገረሰባዊ ጨዋታ ላይ እውቀት ሊጨምሩ የሚችሉ ወሳኝ ነጥቦችንም አንስተዋል፡፡ የዕውቀት መስኩንም ወደፊት ሊያራምዱ የሚችሉ የምርምር ውጤቶችን አቅርበዋል፡፡

ሆኖም ጥናቶቹ ሲመረመሩ አንዳንዶቹ ጥልቅ የሆነ የመስክ ስራ ጉድለት፣ ሌሎቹ በትክክለኛው ማህበራዊና ባህላዊ አውድ መረጃ ያለመሰብሰብ፣ አንዳንዶቹ በጣም ውስን ነገሮች ላይ በተለይም በልጆች ጨዋታ የማተኮር ሁኔታ ይታይባቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እስካሁን በቀረቡ በሃገረሰባዊ ጨዋታዎች ላይ በተደረጉ ጥናቶች ውስጥ በተመሳሳይ የእድሜ ክልል እና በተወሰነ ይዘት ላይ የመታጠር ሁኔታ ይታያል፡፡ በዚህ ጥናት የፎክሎር የአጠናን ዘዴን በመከተል የተዘረዘሩ ክፍተቶችን ለመሙላት ጥረት ተደርጓል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት ዓይነታዊ የምርምር ይዘት (Qualitative) ያለው ስለሆነ ጥናቱ የሚከተለው ገላጭ የምርምር ዘዴን ነው፡፡ ይህ የምርምር ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት ገለጻን ትንታኔንና ፍከራን/ትርጉምን/ መሰረት የሚያደርግ ስልት በመሆኑና የልጃገረዶቹን ጨዋታ ከቅድመ እስከ ድህረ ክዋኔው ድረስ ያለውን ሂደት/ክንውን/ እና ጨዋታው ለማህበረሰቡ ያለውን ፋይዳ ማቅረብ የሚያስችል ዘዴ በመሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም ዘዴው የግለሰቦችን ወይም የሰዎችን አመለካከት፣ እውቀት፣ ስነልቡናዊ ፍላጎታቸውንና ዝንባሌያቸውን ለመፈተሽ፣ ለመተንተንና ለመግለፅ የሚያስችል በመሆኑ ለጥናቱ ተመራጭ ሆኗል፡፡

በዚህ ክፍል ጥናቱ ሲደረግ ምን ምን ተግባራት እንደተከናወኑ፣ ለጥናቱ ያገለገሉ መረጃዎች አይነት፣ የመረጃ ምንጮች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የናሙና አመራረጥ ዘዴና አስፈላጊነታቸው ተገልጿል፡፡

## 3.1 የጥናቱ ናሙና አመራረጥ ስልት

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ስር ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች የሚካተቱ ሲሆን እነሱም የቦታ እና መረጃ አቀባዮች ናሙና አመራረጥ የሚሉት ናቸው፡፡

በአንድ የጥናት ሂደት ውስጥ የናሙና አወሳሰድ ዘዴ መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ዙሪያ ትኩረት ከሚሰጣቸው ጉዳዮችና የጥሩ ናሙና አወሳሰድ (ንሞና) ባህሪያት መካከል የናሙና ልክ፣ ወካይነት፣ የናሙና መገኘት፣ ተተግባሪነት፣ ምክንያታዊነት፣ አዋጭነት፣… ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ Kothari (2004፡58) *ያስረዳሉ*፡፡

ሁለት ዓይነት የናሙና አመራረጥ ዘዴዎች አሉ፡፡ እነሱም ጠቋሚና ዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴዎች ናቸው፡፡ ጠቋሚ የናሙና አመራረጥ ዘዴ በሚጠናው ጉዳይ ዙሪያ ከአንድ ሰው ወይም ቡድን ላይ ውስን መረጃዎችን በመቀበል እነሱ ደግሞ ሌላውን እንዲጠቁሙ የሚያደርጉበት እና የጥቆማ ሂደቱም አንዱ ጠቋሚ ወደ ሌላው ተጠቋሚ እያመለከተ በቂ መረጃ እስከሚገኝ ድረስ የሚቀጥል ነው፡፡ አላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ ደግሞ አንድ አጥኚ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆነ መረጃ ሊያገኝባቸው የሚችሉ

ተሳታፊዎችን ወይም ሌሎች መንገዶችን በመከተል ከጥናቱ አላማ አንጻር የሚመርጥበት ዘዴ እንደሆነ ያለው (2004፣132-134) ያስረዳሉ፡፡

በዚህ ጥናት ሁለቱንም ዘዴዎች መተግበር ተችሏል፡፡ በተለይም ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ሊገኙ የሚችሉባቸውን ቀበሌዎች ለመምረጥ ዓላማተኮር ዘዴን እንዲሁም የተሻለ መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ መረጃ አቀባዮችን ለመምረጥ ደግሞ ዓላማ ተኮርና ጠቋሚ የንሞና ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

ለዚህ ጥናት የተመረጡ የመረጃ ሰጪዎች እና የጥናት ቦታዎች ናሙና ልየታ ስልት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 3.1.1 የመረጃ ሰጪዎች ንሞና

የመርሐ ቤቴ ልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታን ክዋኔና ፋይዳ ለማጥናት ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍል የጥናቱ አካል ማድረግ ስለማይቻል ወካይ የሆነ ናሙና መምረጥ አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ከወሳኝ የንሞና ዘዴዎች መካከል ከጥናቱ አላማ አንፃር ለመጠቀም አመች የሆኑትን ጠቋሚ እና ዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴዎችን በመጠቀም መረጃ ሰጭዎችን መለየት ተችሏል፡፡

ጠቋሚ የንሞና ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት ከአንድ ሰው የተሟላ መረጃ ማግኘት ስለማይቻል ከተመረጡ የጥናቱ ተሳታፊዎች ጋር ቃለ መጠይቅ ሲደረግ በጉዳዩ ላይ እውቀትና ልምድ ያላቸውን ሌሎች ግለሰቦች እንዲጠቁሙ በማድረግ መረጃ ለመሰብሰብ ተመራጭ በመሆኑ ነው፡፡ ዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ደግሞ ለጥናቱ ተገቢ መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ መረጃ አቀባዮችን በመለየት መረጃ ለማግኘት የሚያስችል ዘዴ በመሆኑ በዚህ ጥናት ተግባራዊ ሊደረግ ችሏል፡፡

በመሆኑም የጥናቱን አላማ ለማሳካት ምልከታ በሚካሄድበት ወቅት ንቁ ተሳትፎና ወሳኝ ድርሻ የነበራቸውን እና ስለ ጨዋታው የተሻለ እውቀት ያላቸው የአካባቢው ማህበረሰብ አባላት በመረጃ ሰጪነት ተሳትፈዋል፡፡ በዚህም መሰረት ከ16 — 75 ዓመት የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ 24 (55.8%) ሴቶች እና 20 (44.2%) ወንዶች በድምሩ 43 መረጃ ሰጭዎች በጥቆማና በዓላማ ተኮር የናሙና መምረጫ ዘዴዎች ተለይተው በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት ማሳተፍ ተችሏል፡፡ ከጠቅላላ ተሰታፊዎች መካከል 17 (39.6%) ከ15

— 30፣ 13 (30%) ከ31 — 45፣ 10 (23.3%) ከ46 — 60 ባለው የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሲሆኑ ቀሪዎቹ 3 (7%) ከ61 — 75 ባለው የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው። የመረጃ ሰጭዎችን የትምህርት ዝግጅት ስናይ 16 (37%) ማንበብና መጻፍ የሚችሉ፣ 15 (34.9%) ተሳታፊዎች ከ1ኛ - 12ኛ ክፍል ድረስ ባለው የትምህርት ደረጃ የተማሩ ናቸው። 1 (2.3%) ዲፕሎማ፣ 10 (23.3%) ተሳታፊዎች የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ሲሆኑ ቀሪው 1 (2.3%) መረጃ ሰጭ ሁለተኛ ዲግሪ ያለው ነው።

በአጠቃላይ ለጥናቱ አስፈላጊ መረጃዎችን ለማግኘት ከላይ በተገለጸው መንገድ ጾታን፣ እድሜንና የትምህርት ዝግጅት ባማከለ ሁኔታ መረጃ ሰጭዎችን የመለየት ስራ ተከናውኗል።

### 3.1.2 የጥናት ቦታ አመራረጥ

ለዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ ቦታ አመራረጥን በተመለከተ የታቀደ ናሙና (deliberate or purposive sampling) ተግባር ላይ ውሏል። የታቀደ ናሙና ዓይነት ዓላማ ተኮር ወይም ወሳኝ ስለሆነ ከአጠቃላዩ የተወሰኑትን በዓላማና በታቀደ ሁኔታ የመምረጥ እድል እንደሚሰጥና ሁሉንም አካባቢ ሊወክል እንደሚችል (Kothari 2004 ፤ Bascom 1954) ያስረዳሉ። በመሆኑም ለእዚህ ጥናት የቦታ ምርጫ ጥቅም ላይ የዋለው እድል ከማይሰጡ የናሙና መምረጫ ዘዴዎች መካከል አላማ ተኮር የተሰኘው የናሙና አመራረጥ ዘዴ ነው።

ጨዋታው በሁሉም የወረዳው ቀበሌዎች የሚከወን ቢሆንም ከጊዜና ከበጀት አኳያ ሁሉንም መሸፈን ስለማይቻል በዓላማ ተኮር ንሞና ዘዴ የተወሰኑ ወካይ ቀበሌዎችን መምረጥ አስፈልጓል።

ስለሆነም በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ በተለያዩ አቅጣጫ የሚገኙ አምስት ቀበሌዎች እንዲካተቱ ተደርጓል። በዚህም መሰረት ከትንሳኤ እስከ ዳግም ትንሳኤ ድረስ የሚከወነው የልጃገረዶች ጨዋታ ክዋኔ በስፋትና በድምቀት የሚካሄድባቸው ቦታዎች በመሆናቸው ከታች ቤት ሰባጌ ሀሮገንዳ እና አገሪት ቁም አምባ ቀበሌዎች፣ ከላይ ቤት ደግሞ ዓለም ከተማ፣ ግሬት ወቸዋርኝ እና አፈዘዝ በርቃቶ ቀበሌዎች በጥናቱ ተካትተዋል። ቀድሞ በነበረኝ እቅድ ዘይታ ማጋስ ቀበሌ መረጃ ለመሰብሰብ ተመርጦ የነበረ ቀበሌ ቢሆንም በወቅታዊ የጸጥታ ችግር ምክንያት በቀበሌው ጨዋታው እንዳይካሄድ በመከልከሉ፣

የወረዳውን ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃላፊዎችን፣ ባለሙያዎችን እና የአካባቢውን ባህልና ታሪክ ያውቃሉ የሚባሉ ሰዎችን በማማከር ግሬት ወቸዋርኝ ቀበሌ እንዲተካ ተደርጓል፡፡

## 3.2 መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ይህ ጥናት ዓላማዎቹን ለማሳካትና የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሟል፡፡ ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው የተለያዩ የጥናት መጻሕፍትን፣ የኤሌክቲሮኒክስ የመረጃ መረቦችን እና የተለያዩ ጽሁፎችን (ጋዜጣ፣ መጽሔት፣ በራሪ ጽሁፎች) በመጠቀም ጥናቱን የሚያግዝ መረጃ ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች ተሰብስቧል፡፡ እነዚህ ምንጮች ከቤተመፃህፍት፣ ጥናቱ በሚደረግበት አካባቢ ከሚገኙ የዞንና የወረዳ የእቅድ፣ ኮሚኒኬሽን ወዘተ መስሪያ ቤቶች ውስጥ የተገኙ ናቸው፡፡

በዚህ ጥናት የመስክ መቼቶች ሆነው ያገለገሉት መርሣ ቤቴ የልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ ጥሬ መረጃ የተገኘባቸው መቼቶች ናቸው፡፡ ጥናቱ የመስክ ስራን የሚጠይቅ በመሆኑ በተፈጥሯዊ መቼት ላይ ተሳታፊ በመሆን ከቀዳማይ የመረጃ ምንጮች በምልከታ (Observation)፣ በቃለመጠይቅ (Interview) እና በተተኳሪ ቡድን ውይይት (Focus Group Discussion) የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች መረጃ ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡

### 3.2.1 ምልከታ

ምልከታ በዓይን መመልከትን ብቻ ሳይሆን አጥኚው የሚመለከተውን ጉዳይ በሁሉም የስሜት ህዋሳቶቹ እንዲረዳ እና እንዲገነዘብ የማድረግ ኃይል አለው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ Goldstein እንደሚከተለው ያብራሩታል፡፡ "Observation involve a full range of sensual experience including hearing, feeling, smelling, and tasting…" (Goldstein 1964፡77)

ያለው (2004፤188) "ምልከታ መረጃ ሰብሳቢው ሰው መረጃ ለመሰብሰብ ከሚፈልጋቸው ተጠኝዎች ጋር ወይም አካባቢ በመሆን የሚያደርጉትንና የሚናገሩትን ነገር በቅርበት ሆኖ እያየና እየሰማ በመዘገብ መረጃ የሚሰብሰብበት ዘዴ ነው" በማለት ይገልጻሉ፡፡

በመሆኑም ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ከተጠኝው ማህበረሰብ ጋር በመሆን በክዋኔው/በድርጊቱ/ ውስጥ በመገኘት ሁሉንም የስሜት ህዋሳት በማስተባበር በማየት፣

በማዳመጥ፣ በመቅመስ፣ በማሽተትና በመዳሰስ ኢ-ንቁ ወይም ንቁ ተሳታፊ በመሆን ከመረጃ ሰጭዎችና ከዋኞች መረጃ የሚሰበሰብበት ዘዴ በመሆኑ ወጣቶቹ ጨዋታውን ሲከውኑ አውዱ ላይ በአካል በመገኘት መረጃ ለመሰብሰብ እና ለመያዝ ጠቃሚ/ምቹ ዘዴ በመሆኑ ተግባራዊ ሆኗል፡፡

ይህ ጥናት የፎክሎር ጥናት እንደመሆኑ በተፈጥሯዊ አውድ የሚሰበሰቡ መረጃዎችን ስለሚፈልግ ምልከታ በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት ውሏል፡፡ ዘዴው የመርሃ ቤቴ ልጃገረዶችን የፋሲካ ጨዋታ ክዋኔ ለመረዳት የሚያስችሉ አውዶች በተገኙበት መስኮች አገልግሏል፡፡

መረጃዎችን በአግባቡ ለመያዝ ሲባል የድምፅ መቅጃ (Recorder) ፣ የፎቶና የቪዲዮ ካሜራ፣ የእጅ ስልክ (TECNO CAMON 17) አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ ምልከታ በሚካሄድበት ጊዜ የመረጃ መሰብሰቢያ ቁሳቁሶችን እንድጠቀም ተጠኝዎቼ ባልፈቀዱ ጊዜ በማስታዎሻ ደብተር በመመዝገብ የሚጎድል መረጃ እንዳይኖር ጥረት ተደርጓል፡፡ ምልከታ የተካሄደው ከሚያዝያ 9/2015 ዓ.ም እስከ ሚያዝያ 16/2015 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ሲሆን ይህ ወቅት እና ጊዜ የተመረጠው ጨዋታው የሚከወንበትን የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በማድረግ ነው፡፡

ምልከታ የተካሄደው ልየታ በተደረገባቸው አምስት ቀበሌዎች የመጫወቻ ሜዳዎች/የገበያ ቦታዎች፣ መስኮችና ጎዳናዎች ላይ ሲሆን የጨዋታዎቹ ዓይነትና ባህሪ እኔን በቀጥታ ለመሳተፍ ስለማይጋብዘኝ መረጃው የተሰበሰበው በኢ-ተሳትፎአዊ (Passive Observation) ነው፡፡ በምልከታው በርካታ መረጃዎች የተገኙ ሲሆን በተለይ በጥናቱ አላማ ከተነሱ ጥያቄዎች ውስጥ የመርሃ ቤቴ ልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ ክዋኔ ሂደት ምን ይመስላል? በወረዳው የሚከወነው የፋሲካ ጨዋታ ለተጠኝው ማህበረሰብ ምን ፋይዳ አለው? የሚሉ ጥያቄዎችን ለመመርመር ዘዴው ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

### 3.2.2 ቃለ መጠይቅ

የቃለ መጠይቅ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ጠያቂና ተጠያቂን ፊት ለፊት የሚያገናኝ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ የዚህን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ አስመልክቶ ያለው (2004፣181) ‹‹በቃለ መጠይቅ ወቅት ጠያቂው ጥያቄዎቹን ለመላሹ ያቀርባል፣ ያብራራል፣ ከመላሹ ጋር ፊት ለፊት ሆኖ የተቻለውን ያህል መረጃ ለማግኘት ጥረት ያደርጋል፤ መላሹ ደግሞ

ለተጠየቀው ነገር መልሱን በቃል ይሰጣል፡፡›› በማለት ገልጸውታል፡፡ በተጨማሪም Goldstein (1964፣ 104) ቃለመጠይቅን በሚመለከት የሚከተለውን አስፍረው እናገኛለን፡፡

> *Interview is the most common field methods employed by folklore collectors. interview data way include information on what the informant knows, believes, expects, feels, wants, does or has do which explain or give reason for any of the preceding.*

ከገለጻው እንደምንረዳው ቃለ መጠይቅ በፎክሎር የመስክ ሰራተኞች ተግባራዊ የሚደርግ የተለመደ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ የቃለ መጠየቅ መረጃ አቀባዮች የሚያቁትን፣ የሚያምኑበትን፣ የሚሰማቸውን፣ የፈለጉትን ተግባራዊ የሚያደርጉበት እና ማንኛውንም መረጃ የሚገልፁበት መንገድ  እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ዘዴ በምልከታ ወቅት ግልጽ ያልሆኑ ጉዳዮችን ለመረዳት እና የምልከታ መረጃዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እና ለማጣራት የሚያስችል ነው፡፡

ስለሆነም ስለፋሲካ ጨዋታ ምንነትና ዳራ፣ ቅድም ዝግጅት፣ ክዋኔንና ፋይዳ ለመረዳት ሲባል የአጠቃላይ መረጃዎች ቃለ መጠይቅ በጥናቱ ተተግብራል፡፡ የአጠቃላይ መረጃዎች ቃለመጠይቅ፤ ውስን ቃለመጠይቅ (structured interview) ፣ ከፊል ነፃ ቃለመጠይቅና (Semistructured interview) እና ነፃ ቃለመጠይቅ (Unstructured interview) ተብሎ በሶስት እንደሚከፈል ያለው (2004፣ 183) ያስረዳሉ፡፡ በዚህ ጥናት ሁሉም የአጠቃላይ መረጃ ቃለ መጠይቅ አይነቶች አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡

ውስን የአጠቃላይ መረጃዎች ቃለመጠይቅ አስቀድመው በተዘጋጁ ጥያቄዎች የሚካሄድ የቃለመጠይቅ አይነት ነው፡፡ በዚህ ጥናትም የመርሃ ቤቴ ልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ አጠቃላይ መረጃዎች በዚሁ የቃለመጠይቅ አይነት ተሰብስበዋል፡፡ ሆኖም ውስን ቃለመጠይቅ አስቀድመው በተዘጋጁ ጥያቄዎች እንዲሁም በተመረጡ መረጃ ሰጪዎች ብቻ የሚከናወን በመሆኑ ገደብ አለበትና መረጃ ሰጪዎች በአንፃራዊነት ያለምንም ገደብ የሚያውቁትን እንዲናገሩ ሲባል በከፊል ነፃና በነፃ የአጠቃላይ የቃለመጠይቅ አይነቶች መረጃ ተሰብስቧል፡፡

በዚህ ጥናት 10 (31.3%) ልጃገረዶች፣ 5 (15.6%) ወንድ ወጣቶች፣ 4 (12.5%) ተጫውተው ያሳለፉ እናቶች፣ 8 (25%) ታሪክ አዋቂዎችና የሃይማኖት አባቶች እንዲሁም 5 (15.6%) የባህልና ቱሪዝም ባለሙያዎችና ሃላፊዎች በድምሩ 32 መረጃ ሰጭዎች

በቃለ መጠይቅ የተሳተፉ ሲሆን ከአጠቃላይ ተሳታፊዎች መካከል 17 (53%) ከ15 — 30፣ 8 (25%) ከ31 — 45፣ 5 (15.6%) ከ46 — 60 ባለው የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው። ቀሪዎቹ 2 (6.3%) ተሳታፊዎች ከ61 — 75 ባለው የእድሜ ክልል የሚገኙ ናቸው። የቃለ መጠይቅ ተሳታፊዎችን የጾታ ስብጥር ስንመለከት 15 (46.9%) ወንዶች ሲሆኑ 17 (53%) መረጃ አቀባዮች ደግሞ ሴቶች ናቸው። የመረጃ ሰጭዎችን የትምህርት ዝግጅት ስናይ 7 (21.9%) ማንበብና መጻፍ የሚችሉ፣ 13 (40.6%) ተሳታፊዎች ከ1ኛ - 12ኛ ክፍል ድረስ ባለው የትምህርት ደረጃ የተማሩ ሲሆኑ 1 (3%) ዲፕሎማ፣ 10 (31.3%) የመጀመሪያ ዲግሪ እና ቀሪው 1 (3%) መረጃ ሰጪ ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው ናቸው።

ስለሆነም የክዋኔውን ሂደት እና ጠቀሜታ የሚመለከቱና የሚጠቁሙ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት በአጠቃላይ በመርሐ ቤቴ ወረዳ በሚከወነው የልጃገረዶች ባህላዊ ጨዋታ ላይ የተሻለ እውቀትና ልምድ ካላቸው ታሪክ አዋቂዎች፣ ተጫውተው ካሳለፉ እናቶች፣ ጨዋታውን ከሚከውኑ ወጣቶች፣ ከማህበረሰብ ተወካዮች፣ ከኃይማኖት አባቶች፣ ከወረዳ ባህል እና ቱሪዝም ባለሙያዎች የፆታ እና የእድሜ ስብጥርን መሰረት በማድረግ በውስን፣ በከፊል ነጻና በነጻ ቃለ መጠይቅ መረጃ ለመሰብሰብ ተችሏል።

### 3.2.3 ተተኳሪ የቡድን ውይይት

የቡድን ተኮር ውይይት በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ ያልተገኙ እና ግልፅነት የጎደላቸውን፣ አሻሚና አከራካሪ የሆኑ መረጃዎችን ለማጥራት የሚተገበር የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት ነው። "የቡድን ተኮር ውይይት የሚካሄደው በጉዳዩ ላይ በቂ መረጃ ሊኖራቸው ይችላል ተብሎ የሚታሰቡ ሰዎችን በመምረጥ በሚነሳው ጥያቄ ዙሪያ በቡድን በመሆን እየተወያዩ መረጃ እንዲሰጡ ለማድረግ ሲሆን፣ ተሳታፊዎቹም እስከ 14 ሊደርሱ ይችላሉ።" (ያለው 2004፣191)

የቡድን ውይይት በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ ያልተነሱ ወይም የተዘለሉ ነጥቦች እንዲወጡ፣ በምልከታና በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እና የተጣረሱ መረጃዎችን ለማስታረቅ የሚጠቅም ነው። የልጃገረዶቹ ጨዋታ ስለሚከወንበት ምክንያት፣ የክዋኔ ሂደትና ይዘት፣ ተስተላልፎ፣ የአባላቱ መስተጋብርና አውዱ ላይ ስለሚከወኑ የጨዋታ ዓይነቶች፣ በክዋኔ ወቅት የሚፈጠሩ፣ የሚተገበሩ

የማህበረሰቡ የጋራ ማንነት ማሳያ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችል ዘዴ በመሆኑ ለዚህ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

በቡድን ተኮር ውይይቱ ላይ የተሳተፉት መረጃ አቀባዮች ለጨዋታው/ለመረጃው/ ቅርበት ያላቸው ሰዎች ሲሆኑ በተለይም በእድሜና በልምድ የተሻለ እውቀት አላቸው የተባሉ መረጃ ሰጭዎችን በሶስት ቡድን በማደራጀት መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በውይይቱ የተገኙ መረጃዎችን ሚዛናዊ ለማድረግ ሲባል ፆታን፣ ዕድሜንና የመተዳደሪያ ስራን መሰረት በማድረግ በአፈዘዝ በርቃቶ፣ በግሬት ወቸዋርኝና በአገሪት ቁምአምባ ቀበሌዎች ሶስት ቡድኖች ተደራጅተው መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

የቡድን ውይይቱ የተካሄደው ቀድመው በቃለ መጠይቅ የተሳተፉና ያልተሳተፉትን በማቀለቀል ሲሆን ቀድመው በቃለመጠይቅ መረጃ የሰጡት አስቀድመው የተገኙ መረጃዎችን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ሲባል የተመረጡ ናቸው፡፡ ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሃሳቦች ለውይይት የሚቀርቡበት በመሆኑ፣ ስህተቶች ታርመውበታል፣ ድንግርግሮች ጠርተውበታል፣ የጎደሉ መረጃዎች ተሟልተውበታል፡፡ በተለይ በውይይቱ ጊዜ ተሳታፊዎቹ እርስ በእርስ ስህተትን የሚተራረሙ በመሆኑ የመረጃዎች እውነትነት አስተማማኝ እንዲሆን አድርጓል፡፡ የእያንዳንዱ ጨዋታ ክዋኔ ሂደት እና ፋይዳቸው በውይይቱ ትኩረት የተደረገባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡


መረጃ በሰጭዎቹ በጾታ፣ በእድሜና በትምህርት ዝግጅት ስብጥር ያለው ልዩነት ደግሞ መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት አስተዋጽኦ ነበረው፡፡ ምክንያቱም የተገኘው መረጃ የአንድ ወገን ብቻ እንዳይሆን ስብጥሩ አዎንታዊ ሚና አበርክቷል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የመርሐ ቤቴ ወረዳ አጠቃላይ ገጽታ

በዚህ ክፍል ስለ መረሐ ቤቴ ወረዳ አጠቃላይ ገጽታ ይዳሰሳል፡፡ በዚህም የወረዳው መልክዓ ምድራዊ ገጽታ፣ የመሬት አቀማመጥና የአየር ሁኔታ፣ መተዳደሪያ፣ ቋንቋና ኃይማኖት፣ መሰረተ ልማትና አስተዳደራዊ ሁኔታ ቅኝት ተደርጎባቸዋል፡፡

ምስል 4፡- ጥናቱ የተካሄደበት ወረዳ በኢትዮጵያ እና በአማራ ክልል የሚገኝበትን አካባቢ የሚያሳይ ካርታ




(ምንጭ፡-የወረዳው ፕላን ጽ/ቤት የልማት አመላካች ዓመታዊ መጽሔት)

የመርሐ ቤቴ  ወረዳ በሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር ስር ከሚገኙ ሃያ አራት ወረዳዎች መካከል አንዱ ሲሆን “መርሐ ቤቴ” የሚለው ቃል ከሁለት የግእዝ ቃላት ጥምረት የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም መርሐ ማለት “እፊት እፊት ሄደ፤ መንገድ አሳየ፣ አመለከተ” ማለት ሲሆን ቤት ደግሞ በቁሙ “ቤት” ማለት ነው (ደስታ 1962፣ 802)። በተጨማሪም “መርሐ” የሚለው ቃል ትርጉሙ “መራ፣ መርሕ፣ የሚመራ፣ መራሒ እና መሪ” የሚል ሲሆን “ቤት” ደግሞ በቁሙ “ቤት” ማለት እነደሆነና የሁለቱ ቃላት ጥምረት “ወደ ቤቴ መራኝ” ማለት እንደሆነ (መምህር ካሳዬ አስናቀ ቃለ መጠይቅ፣፣ ሚያዝያ 8/2015 ዓ.ም) ይገልፃሉ።

ማዕዛሽወርቅ (2011 ዓ.ም) እንደገለጸችው መርሐ ቤቴን ወሰን ሰገድና ልጃቸውን  በኩርዬን ጨምሮ እንደ መሸሻ፣ ሰይፉ፣ ራስ ዳርጌ የመሳሰሉ ገዥዎች በተለያየ ጊዜ ያስተዳደሯት ሲሆን ከእነዚህ መካከል እስከ ደራ አስፋፍተው ግዛት የጨመሩላት ራስ ዳርጌ ስማቸው ጎላ ብሎ እንደሚጠቀስ ይነገራል። መርሐ ቤቴ ሚዳን፣ ወረሞን፣ ላይቤትን፣ ታች ቤትን፣ በኋላም ቢጣቢሎን አካትቶ በሸዋ የሚገኝ አንድ አውራጃ የነበረ ሲሆን ከ1983 ዓ.ም በኋላ ደግሞ ሚዳና ወረሞ ወደ አንድ ራሱን ወደቻለ ወረዳ፣ ደራ ወደ ኦሮምያ ክልል ሰሜን ሸዋ፣ ቢጣቢሎ ወደ ደቡብ ወሎ ሲካተቱ፣ መርሐ ቤቴ ላይ ቤትና ታች ቤትን ይዞ አንድ ወረዳ ሊሆን ችሏል። ስለሆነም አሁን በአለው የአስተዳደር መዋቅር መርሐ ቤቴ የሚባለው በዠማና በወንጭት ወንዞች ተከቦ መሃል ላይ የሚገኘው አካባቢ ነው።

አብዛኛው የሸዋ ግዛት በኦሮሞ መስፋፋት በቁጥጥር ስር ሲውል መርሐ ቤቴ ሳይያዝ ቀርቷል። ለዚህም አንዱ ምክንያት መርሐ ቤቴ ጠንካራ ግዛት በመሆኑ ሲሆን ሌላው ደግሞ አካባቢው ገደላ ገደል፣ ዋሻና አቀበት ቁልቁለት የበዛበት ስለሆነ ለፈረስ ምቹ ባለመሆኑ ነው። (ጎሩይ 1923፣ 16 እና ተክለ ጻድቅ 1961፣ 183)

የመርሐ ቤቴ ህዝብ አትንኩኝ ባይና ጠላት በተነሳ ቁጥር ከፊት ቀድሞ የሚገኝ ጀግና ህዝብ እንደሆነ ይነገራል። ለዚህም እንደ ማሳያ የሚነሳው ከ1929 ዓ.ም እስከ 1933 ዓ.ም ድረስ በነበረው የጣሊያን የአምስት ዓመት ወረራ ጊዜ ከአምስቱ የሽንቁጥ ወንድማማቾች (ኃይሌ ሽንቁጥ፣ ተሾመ ሽንቁጥ፣ አበበ ሽንቁጥ፣ ይነሱ ሽንቁጥ፣ ጥላሁን ሽንቁጥ) በተጨማሪ እንደነ ልጅ ስዩም፣ ፊታውራሪ ዱባለ፣ ደጃዝማች ገለታ ቆርቾ፣ ፈለቀ እጅጋየሁ ያሉ በርካታ አርበኞች አካባቢውን አናስደፍርም ብለው መዋደቃቸውን (ዓለማየሁ፣2008) አስፍረዋል። በተጨማሪም ህዝቡ ሃይማኖቱን ጠብቆ እስከዚህ ዘመን

የዘለቀ፣ ጀግናና እንግዳ ተቀባይ፣ እንደ መንዜ፣ ቡልጋ፣ ተጉለቴ ሁሉ የመርሐ ቤቴ(የመሬ) ማንነትን የገነባ ህዝብ እንደሆነ (ማዕዛሽወርቅ 2011፣4-12) ታስረዳለች።

## 4.1 መልክዓ ምድራዊ ገጽታ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን ወስጥ ከሚገኙ ሰላሳ አንድ ወረዳዎች መካከል የመርሐ ቤቴ ወረዳ አንዱ ነው። የወረዳዉ ዋና ከተማ ዓለም ከተማ ስትሆን ከአዲስ አበባ በ180 ኪሎ ሜትር፣ ከዞኑ ርእሰ ከተማ ከደብረ ብርሃን ደግሞ በ138 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች።

ወረዳው በደቡብ ከእንሳሮና ዋዩ ወረዳ፣ በምእራብ ከኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በሰሜን ከሚዳ ወረሞ ወረዳ፣ በምስራቅ ከመንዝ ቀያ ገብርኤል ወረዳ እንዲሁም በደቡብ ምስራቅ ከሞረትና ጅሩ ወረዳ ይዋሰናል። ትልቁ የአባይ ገባር የሆነው የጀማ ወንዝ የወረዳውን ደቡባዊና ምስራቃዊ ድንበር የሚያካልል ሲሆን የወንጭት ወንዝ ደግሞ ምእራባዊና ምስራቃዊ የወረዳውን ድንበር ያካልላል። በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ጥናት መሰረት የወረዳው የቆዳ ስፋት 99,540 ሄክታር (1058.19 ስኩየር ኪሎ ሜትር) የሚሸፍን ሲሆን፣ የመርሐ ቤቴ ወረዳ በ22 የገጠርና በ 2 የከተማ ቀበሌዎች ተደራጅቷል። (የወረዳው ፕላን ጽ/ቤት የሶሽዮ-ኢኮኖሚ ዓመታዊ መጽሄት 2015፣1)።

### 4.1.1 የመሬት አቀማመጥና የአየር ሁኔታ

ወረዳው ከባህር ጠለል በላይ ያለው ከፍተኛ ቦታ ነጥብ 1911.5 ሜትር ሲሆን ዝቅተኛው ደግሞ 14.4 ሜትር ነው። የወረዳው መልክዓ ምድር አቀማመጥ በአብዛኛው ተራራማ፣ ወጣገባና ሸለቆ የሚበዛበት ሲሆን አስር በመቶ ተራራማ፣ አርባ ከመቶው ሸለቋማ፣ አርባ ዘጠኝ ከመቶው ወጣ ገባ ሲሆን አንድ ከመቶው ብቻ ሜዳማ ነው። የአየር ንብረቱ በሶስት ቀጠናዎች የተከፈለ ነው። ይሄውም ስድስት በመቶው ደጋ፣ ሰባ በመቶው ወይና ደጋ እንዲሁም ቀሪው ሃያአራት በመቶው ቆላ ነው። የወረዳው ዓመታዊ አማካይ የዝናብ መጠን ከ928 — 1518 ሚሊ ሜትር እንደሚሆን ይገመታል። (የወረዳው ስታስቲክስ ዓመታዊ መጽሄት 2014:3)።

ምስል 5፦ የወረዳው ከፊል መልክዓ ምድራዊ ገጽታ





(በአጥኝው የእጅ ስልክ የተነሳ፣ ሚያዝያ 2015 ዓ.ም)

### 4.1.2 የመሬት አጠቃቀምና መተዳደሪያ

በወረዳው ከሚኖረው አጠቃላይ ህዝብ 95.53 በመቶው በግብርና (በእርሻ እና እንስሳት እርባታ) ላይ የተመሰረተ ሲሆን ቀሪው 4.47 በመቶው በመንግስት ስራና በንግድ ስራዎች የሚተዳደር ነው፡፡

በወረዳው የተለያዩ ዓመታዊ ሰብልች (የብዕርና የአገዲ እህል) ጥራጥሬ፣ የቅባት እህልች፣ ቃጫና ጥጥ እንዱሁም የስራስር ተክሎች እና ቋሚ ሰብሎች ስነምህዳርን መሰረት በማድረግ ይመረታሉ፡፡ በ2013/14 የምርት ዘመን በመኸር ወቅት ብቻ 1,177,924 ኩ/ል ምርት መገኘቱን ከወረዳው እቅድና ልማት ጽ/ቤት ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡

የእንስሳት እርባታ ዘርፍ ሲታይ ደግሞ 109,258 የዳልጋ ከብት፣ 18,650 በግ፣ 70,163 ፍየል፣ 27,929 የጋማ ከብት፣ 663,106 ዶሮ እና 4,989 የንብ ቀፎ በወረዳው እንደሚገኝና ይህም የህዝቡን የአመጋገብ ስርዓት ከማሻሻሉም ባሻገር አርሶአደሩ በእንስሳቱ ተዋጽኦ (በቆዳና ሌጦ፣ በስጋና እንቁላል) እና በቁም እንስሳት ሽያጭ ኑሮውን እንደሚደጉም ያገኘነው መረጃ ያስረዳል፡፡ (የፕላን ጽ/ቤት ስታትስቲክስ ዓመታዊ መጽሄት 2013፣1-9)፡፡

## 4.2 የህዝብ ብዛት፣ ቋንቋና ኃይማኖት

በ2007 ዓ.ም የህዝብ እና ቤት ቆጠራ (Centeral Statistics Agency) መረጃ መሰረት የወረዳው አጠቃላይ ህዝብ ብዛት 126,501 ሲሆን ከዚህ ውስጥ 63,997 ወንዶች፣ 62,504 ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡ ከወረዳው አጠቃላይ ህዝብ ውስጥ 4.47 በመቶው በከተማ የሚኖር (በመንግስት ስራና በንግድ የሚተዳደር} ሲሆን ቀሪው 95.53 በመቶው በገጠር የሚኖር ወይም በግብርና ስራ የሚተዳደር ነው፡፡ ከአጠቃላይ ህዝቡ 99.78 በመቶው አማርኛ ተናጋሪ ሲሆን፣ 99.63 በመቶ የሚሆነው የወረዳው ነዋሪ የኦርቶዶክስ ክርስትና ኃይማኖት ተከታይ ሲሆኑ ቀሪዎቹ 0.37 በመቶው የእስልምና እና የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ናቸው፡፡ (CSA 2007፡8-16፤ የወረዳው ፕላን ጽ/ቤት የሶሽዮ-ኢኮኖሚ ዓመታዊ መጽሄት 2015፣1-9)፡፡

## 4.3 መሰረተ ልማት

ቀጥሎ የሚዳሰሱት የወረዳው የመሰረተ ልማት አውታሮች ሽፋን ይሆናል፡፡ እነዚህም ጤና፣ ትምህርት፣ መንገድ፣ መብራት፣ የንጹህ መጠጥ ውሃና መሰል ጉዳዮች ናቸው፡፡

የትምህርት ሽፋንን በተመለከተ በወረዳው ትምህርት ጽህፈት ቤት ስር የሚገኙ አራት አፀደ ህጻናት፣ ሃምሳ አንደኛ ደረጃ፣ አራት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ፣ አንድ የመሰናዶ ትምህረት ቤት እና አንድ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ይገኛሉ፡፡ እንደ 2014 ዓ.ም መረጃ በወረዳው የተማሪ ጾታ ተሳትፎ ምጥጥን በገጠር 1፡2፣ በከተማ ደግሞ 1፡1 ሲሆን የተማሪ መምህር ጥምርታ 1፡45 መሆኑን ያመላክታል፡፡

የጤና ሽፋንን በተመለከተ በወረዳው ሃያ ሶስት ጤና ኬላዎች፣ ስድስት ጤና ጣቢያዎች እና አንድ ሆስፒታል አገለግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ በመንግስት ከተገነቡት በተጨማሪ አምስት የግል ክሊኒኮች አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ የእነዚህን የጤና ተቋማት እና የተጠቃሚ ጥምርታ ስንመለከት ደግሞ አንድ ጤና ኬላ ለአምስት ሽህ ሰው (1፡5,000) አገልግሎት ይሰጣል፡፡ አንድ ጤና ጣቢያ ለሃያ አምስት ሽህ ተጠቃሚ (1፡25,000) አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን አንድ ሆስፒታል ደግሞ ለአንድ መቶ አርባ አራት ሽህ ሰባት መቶ አስራ ስድስት ሰው (1፡144,716) አገልግሎት ይሰጣል፡፡ በእነዚህ የጤና ተቋማት 47 የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች፣ 23 አዋላጅና 32 ክሊኒካል ነርሶች፣

18 የጤና መኮንኖች፣ 15 ዶክተሮች፣ 10 ፋርማሲስቶችና 11 ላቦራቶሪ ቴክኒሻኖች አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

በ2014 ዓ.ም መረጃ መሰረት በወረዳው  የበጋና የክረምት ጠቅላላ የመንገድ ሽፋን 156.88 ኪ/ሜ ደርሷል፡፡ ከዚህ ውስጥ መለስተኛ አስፋልት 32.5 ኪ/ሜ ሲሆን፣ 124.38 ኪ/ሜ ደግሞ የጠጠር መንገድ ነው፡፡ በወረዳዉ ከሚገኙት ሃያ ሁለት የገጠርና ሁለት የከተማ ቀበሌዎች መካከል ከሁለት የገጠር ቀበሌዎች በስተቀር ሁሉም ቀበሌዎች ከዋና ዋና መንገዶች ጋር የሚያገናኙ በክረምት በበጋ አገልግሎት የሚሰጡ መንገድ ተጠቃሚ ናቸው፡፡

ወረዳው የጥቁር ዓባይ ገባር የሆኑና ክረምት ከበጋ የሚፈሱ የጀማ እና ወንጭት ወንዞች ባለቤት ነው፡፡ የወረዳውን ውሀ ሽፋን ስናይ ደግሞ በገጠር 69,776 (56.07 በመቶ)፣ በከተማ ደግሞ 5041 (85 በመቶ) ህዝብ የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ነው፡፡ በአጠቃላይ የወረዳዉ የንጹህ መጠጥ ዉሃ ሽፋን 79 በመቶ መድረሱን ያገኘነው መረጃ ያስረዳል፡፡

የስልክ አገልግሎት ሽፋንን በተመለከተ በወረዳው ሰባት የሞባይል ኔትወርክ ማዕከላት በመዘርጋታቸው ሁሉም/ሃያ አራቱም/ የከተማና የገጠር ቀበሌዎች/ የሞባይል ስልክ ተጠቃሚ መሆን ችለዋል፡፡ የወረዳው መቀመጫ የሆነችው ዓለም ከተማ የዲጅታል ስልክ ጠተቃሚም ናት፡፡

በወረዳው አስራ አምስት ቀበሌዎችና የቀበሌ ማዕከላት እንዲሁም ስድስት ጎጦች የሃያ አራት ሰዓት የኤሌክትሪክ መብራት አገልግሎት ተጠቃሚ ሲሆኑ ቀሪዎቹ ቀበሌዎች የኤሌክትሪክ መብራት አገልግሎት የማያገኙ ናቸው፡፡ (የወረዳው ፕላን ጽ/ቤት የሶሽዮ-ኢኮኖሚ ዓመታዊ መጽሄት 2015፣1-9 እና ስታትስቲክስ ዓመታዊ መጽሄት 2014፣1-29)፡፡

## 4.4 የባህልና የተፈጥሮ የመስህብ ሐብቶች

የመርሐ ቤቴ ህዝብ ክርስትናን ቀድመው ከተቀበሉ አከባቢዎች መካከል አንዱ እንደሆነ መምህር ካሳዬ አስናቀ (ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዝያ 2015 ዓ.ም) ገልጸውልኛል፡፡ በወረዳው ፕላን ጽ/ቤት የሶሽዮ-ኢኮኖሚ ዓመታዊ መጽሄት (2015 ዓ.ም) እንደሰፈረው መረጃ ከ99.63 በመቶ የወረዳው ህዝብ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና እምነት ተከታይ ነው፡፡

ህዝቡ ሃይማኖቱን ጠብቆ እስከዚህ ዘመን የዘለቀ፣ ጀግናና እንግዳ ተቀባይ፣ እንደ መንዜ፣ ቡልጋ፣ ተጉለቴ ሁሉ የመርሐ ቤቴ (መሬ) ማንነትን የገነባ ህዝብ ነው። (ማዕዛሽወርቅ 2011፣4-12)።

በዚህም የተነሳ ዘመናትን የተሻገሩ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ክብረ በዓላት በወረዳው ይከበራሉ። እንደ አብዛኛው የእምነቱ ተከታይ ሁሉ እንደ ገና፣ ጥምቀት፣ ፋሲካ፣ እንቁጣጣሽ ያሉ ሃይማኖታዊ በዓላት በወረዳው ህዝብ በድምቀት የሚከበሩ በዓላት ናቸው። በእንዚህ ክብረበዓላትና ሌሎች ማህበራዊ ክንውኖችን መነሻናነት በህጻናት፣ በወጣት ወንዶች፣ በልጃገረዶች፣ በእናቶችና በአባቶች  የሚከወኑ ልዩ ልዩ ጨዋታዎች አሉ። ከእነዚህ የጨዋታ ዓይነቶች መካከል ከፋሲካ በዓል ጋር ተያይዞ የሚከወነው የልጃገረዶች ጨዋታ ተጠቃሽ ነው።

የመርሐ ቤቴ ወረዳ ህዝብ አትንኩኝ ባይና ጠላት በተነሳ ቁጥር ከፊት ቀድሞ የሚገኝ ጀግና እንደሆነ ተጽፎ እናገኛለን። ለዚህም በማሳያነት የሚጠቀሰው በጣሊያን የአምስት ዓመት ወረራ ጊዜ ከአምስቱ የሸንቁጥ ወንድማማቾች በተጨማሪ በርካታ አርበኞች አካባቢውን አናስደፍርም ብለው መዋደቃቸውን ዓለማየሁ (2008) አስፍረው እናገኛለን።

በተጨማሪም ህዝቡ እርስ በእርሱ የሚደጋገፍባቸው እንደ ደቦ፣ እቁብና እድር አይነት ባህላዊ የመረዳጃ ተቋማት ባለቤት ነው። በእርሻ፣ በሰርግ፣ በሃዘንና በመሳሰሉት ማህበራዊ ክስተቶች እነዚህ ባህላዊ ተቋማት  የላቀ ድርሻ አላቸው።

ተፈጥሮአዊ የመስህብ ሃብቶች በተመለከተ ወረዳው በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የተፈጥሮና ጥንታዊ የኃይማኖት ቅዱስ ቦታዎች ባለቤት ነው። ከነዚህም መካከል ኦፍና ቅዱስ አማኑኤል፣ አጤ ዋሻ ጊዮርጊስ፣ ጌብ ልደታ፣ ኮራ ማሪያም፣ ዘይታ የተፈጥሮ ትክል ድንጋይ፣ ዘርዓ ብሩክ ፀበል፣ አብርሃም ዋሻና ኪዳነ ምህረት ዋሻ የሚጠቀሱ በወረዳው የሚገኙ ዋና ዋና የመስህብ ሃብቶች ናቸው። በተጨማሪም የመርሐ ቤቴ ወረዳ እንደ ጀማና ወንጭት ያሉ ታላላቅ ወንዞችና እንደ ሶረኔ እና ሰስ ያሉ ብርቅዬ የዱር እንስሳት የሚገኙበት ነው። (የኦፍና ቅዱስ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን አመሰራረት ታሪክ መጽሄት 1989፡14-15 ፤ የወረዳው ዓመታዊ ስታትስቲካስ መጽሄት 2014፡2)።

# ምዕራፍ አምስት

# የልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ ክዋኔና ፋይዳ

ይህ ምዕራፍ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት የተሰበሰቡ መረጃዎች በመልክ በመልኩ ተደራጅተው የቀረቡበት ክፍል ነው፡፡ በመሆኑም የጨዋታው ታሪካዊ አጀማመር ምክንያቶች ምን ምን ናቸው? የልጃገረዶቹ የፋሲካ ጨዋታ ክዋኔ ሂደት ምን ይመስላል? ጨዋታው ለማህበረሰቡ ምን ዓይነት ፋይዳዎች አሉት? በልጃገረዶቹ ጨዋታ ክዋኔ ሂደት ምን ዓይነት ይዘት ያላቸው ስነቃሎች ይስተዋላሉ? በጨዋታው ቀጣይነት ላይ የሚስተዋሉ ስጋቶች ምን ምን ናቸው? የሚሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ከመስክ የተሰበሰቡ ጥሬ መረጃዎች ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች በተገኙ ፅንሰ ሃሳቦችና እና ከክዋኔያዊና ተግባራዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ጋር እየተገናዘቡ የተተነተኑበትና የተብራሩበት ክፍል ነው፡፡

## 5.1 የመርሐ ቤቴ ልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ ምንነትና ታሪካዊ ዳራ

ሃገረሰባዊ ጨዋታ አንድ ማህበረሰብ ይሆነኝ ብሎ ፈጥሮ የሚከውነው፣ እንደ ልማድ የሚደጋግመው የማንነቱ ማሳያ የሆኑ ጨዋታዎችን የሚመለከት እንደሆነና የአንድን አካባቢ ባህላዊ ገጽታ የሚገልጹ የማህበረሰቡን እምነት፣ የውስጥ ስሜት፣ የአኗኗር ሁኔታ የሚያሳዩ፣ በየትኛውም ስፍራ አካባቢያዊ ባህሉ፣ የአሰራር ልምዱ፣ የህይወት ዘይቤው በሚፈቅደው መልኩ የሚከወን መሆኑን በምእራፍ ሁለት የጽንሰ ሃሳብ የገለጻ ክፍል ተመልክተናል፡፡

የመርሐ ቤቴ የልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ የክርስቶስ መነሳት የሚዘከርበትን በዓል፣ በዓለ ትንሳኤን ጠብቆ በአመት አንድ ጊዜ የሚከወን ጨዋታ ሲሆን ቅደም ተከተል ያለው፣ ልጃገረዶች አምረውና ደምቀው የሚገኙበት፣ በነጻነት የሚደሰቱበት (የሚቦርቁበት)፣ በቃልና በድርጊት የሚቀርብ፣ ተለዋዋጭ ባህሪ ያለው ክዋኔ ነው፡፡ ጨዋታው የአካባቢውን ማህበረሰብ እምነት፣ ስሜትና የአኗኗር ሁኔታ የሚገለጽበት የባህላዊ ገጽታው ማሳያ ሲሆን፣ በሁሉም የወረዳው ቀበሌዎች በተመረጡና አማካይ በሆኑ ቦታዎች (በወል መሬት፣ ገበያ፣ መስክ፣ አውራ ጎዳናዎች) ይከወናል፡፡ የጨዋታው ዋነኛ ተሳታፊዎች ልጃገረዶች ናቸው፡፡

እንደ Sims and Stephens (2005) የፎክ ቡድን ከሚመሰረትባቸው መንገዶች መካከል ቀረቤታ፣ አስገዳጅ ወይም አጋጣሚያዊ ሁነት፣ ጉርብትና፣ የተፈጥሮ አስገዳጅነት፣ የዘር ሃረግ፣ የሚከተሉት እምነት፣ የተለመደ ግንኙነት፣ ጓደኝነት፣ ትምህርት ቤት ሊሆኑ እንደሚችሉ ያስረዳሉ። በፋሲካ ጨዋታዎችም ከተለየያዩ ንዑስ ቀበሌዎች የመጡ ልጃገረዶች በእድሜ፣ በቀረቤታ፣ በፍላጎት የየራሳቸውን ቡድን በመመስረት በአማካይ ቦታ ተሰባስበው ጨዋታውን ይከውናሉ።

በምልከታና በቃለ መጠይቅ በተገኘው መረጃ መሰረት በዚህ የትንሳኤ ሳምንት ጨዋታ ልጃገረዶቹ አስር አይነት ጨዋታዎችን ይጫወታሉ። በጨዋታዎቹ ላይ ወጣት ወንዶች፣ እናቶችና ህጻናት ይታደማሉ። እነዚህ ታዳሚዎች ጨዋታውን በማድመቅ፣ ጥሩ የሚጫወቱትን በማበረታታት፣ በድምጽና በጭብጨባ በማጀብ ላቅ ያለ ሚና አላቸው።

በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ባዘጋጀው መዝገበ ቃላት (1993፤571) ሃገረሰባዊ ጨዋታ ንግግርን፣ ውይይትን፣ ልፊያን፣ ቀልድን፣ የሚያስቅ የሚያዝናና ወሬን፣ ውድድር ወይም ፉክክር ያለበትና የሌለበት የቤትና የውጭ ስፖርትን፣ መዝናኛን፣ ዘፈንን፣ ዳንስን፣ ውዝዋዜን እና መሰል ድርጊቶችን እንደሚያጠቃልል ተገልጾ እናገኛለን። የፋሲካ ጨዋታ በዓመት አንድ ጊዜ የሚካሄድና ልጀገረዶች ከስራ ጫና ተላቅቀው በነጻነት የሚሳተፉበት፣ የሚጫወቱበት፣ የሚደሰቱበት፣ የሚዘፍኑበት፣ የሚጨፍሩበት፣ የሚቦርቁበትና የወደፊት የትዳር አጋራቸውን የሚያገኙበት በመሆኑ በጉጉት የሚጠብቁት ሁነት /event/ ነው። ጊዜው ከመድረሱ አስቀድሞ ልጃገረዶቹ በጨዋታው አምረውና ደምቀው ለመገኘት ልዩ ልዩ ቅድመ ዝግጅቶችን ያደርጋሉ።

ስለ ጨዋታው አጀማመር የተጻፈ መረጃ ማግኘት ባይቻልም ጨዋታው የክርስትና ሃይማኖት መሰረት እንዳለውና ረጅም ዘመን እንዳስቆጠረ ያናገርናቸው የሃይማኖት አባቶችና ታሪክ አዋቂዎች ያስረዳሉ።

> *ይህ አካባቢ ክርስትናን የተቀበለው በ4ኛው ክ/ዘመን ነው። በዚህም የተነሳ ባህሉ መነሻ ያደረገው ሃይማኖቱን ነው። ባህላዊ ክንውኖች ሁሉ ከክርስትና ሃይማኖት ጋር ተቆራኝተው ያሉና የሚተገበሩ ናቸው። እያንዳንዱን ባህላዊ ክንውን ስንመለከት እንደ ገናና ጥምቀት ሁሉ የፋሲካ ጨዋታም መሰረቱ ክርስትና ሃይማኖት ነው። ሌላው ጨዋታው የትንሳኤ በዓልን ጠብቆ መከወኑ ጨዋታው ሃይማኖታዊ መነሻ መሰረት እንዳለው ያመለክታል። (ቀሲስ ካሳዬ ቃለ መጠይቅ፣ ዓለም ከተማ፣ ሚያዝያ 14/2015 ዓም)*

ይህ የልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ አሁን አሁን ባህላዊ ገጽታ ይላበስ እንጅ የጨዋታው ጅማሬ/መነሻ መሰረቱ/ የክርስትና ሃይማኖት እንደሆነና ረጅም እድሜ እንዳለው መምህር ጸጋዘአብ (መምህር ጸጋዘአብ *ቃለ መጠይቅ*፣ *ሚያዝያ* 2015 ዓም) መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎችን በማጣቀስ እንደሚከተለው ዘርዘር አድርገው ያስረዳሉ፡፡

የፋሲካ ጨዋታ አሁን ባህላዊ ይዘቱን ይዞ በባህላዊ ጨዋታነቱ ይታወቅ እንጅ መነሻው ሃይማኖታዊ ለመሆኑ ማስረጃዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ አንደኛው መገለጫው ጨዋታው የሚጀምረው እለተ ትንሳኤን ጠብቆ ነው፡፡ በዓሉ የሚውለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን "የትንሳኤ በዓል ነው" ብላ ያወጀችበትን እለት ጠብቆ መከወኑ ጨዋታው ሃይማኖታዊ ምክንያት እንዳለው አንዱ ማሳያ ሆኖ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

ሁለተኛው ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 20-21፣ በማቲዎስ ወንጌል ምዕራፍ 28፣ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 24፣ በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 16 ላይ የተገለጸውን መነሻ አድርገን ብናይ "የፋሲካ ሳምንት በሆነ ጊዜ በዓልን ሊያከብሩ ወጡ" ተብሎ በአይሁድ ዘንድ የቂጣ በዓል እንዳላቸው ተገልጧል፡፡ በዚህ በፋሲካ/በቂጣ በዓል/ ከየአገሩ ያሉ አይሁዶች በአንድ ቦታ ተሰባስበው ሃይማኖታዊ ሥርዓታቸውን ፈጽመው፣ ዘመዶቻቸውን ተዋውቀውና ተወያይተው ይመለሳሉ፡፡ በአይሁድ በዓል ከተለያየ የእስራኤል ክፍል ማለትም ከገሊላ፣ ከቤተሳይዳ፣ ከኢየሩሳሌም፣ ከኤፌሶን፣ ከገላቲያ፣ ወዘተ እንደሚሰባሰቡ ሁሉ በዚህ የፋሲካ ጨዋታም ልጃገረዶቹ ከተለያዩ ንዑሳን ቀበሌዎች (በመርሐ ቤቴ ወረዳ በአፈዘዝ በርቃቶ ቀበሌ ብቻ ከሰባት ንዑሳን ቀበሌዎች ማለትም ከጭቃ ማሻ፣ ከጎድጎዲት፣ ከቀጣኒት፣ ከሰሞን ምድር፣ ከዝሆን መጠጫ፣ ከቆለሚያና ከበርቃቶ ንዑስ ቀበሌዎች/ጎጦች) በመሰባሰብ በዓላቸውን ያከብራሉ፤ ይደሰታሉ፤ ማህበራዊ መስተጋብራቸውን ያጠናክራሉ፡፡ ስለሆነም ይህ በዓል የዚያ የብሉይ ኪዳን ሃይማኖታዊ ትውፊት ተጽእኖ እንዳለበት እና ረዘም ያለ ታሪክና እድሜ እንዳለው መገመት እንደሚቻል መምህር ጸጋዘአብ ያስረዳሉ፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሁለቱንም (ኦሪትንና ሐዲስን) አስተባብራ የያዘች ናት፡፡ "ፋሲካ" ስንል ብሉይ ኪዳንን የሚመለከት ሲሆን "ትንሳኤ" ስንል ደግሞ ሃዲስ ኪዳንን ይመለከታል፡፡ ፋሲካ የሚለው ቃል አንድ ላይ መሰባሰብን፣ መደሰትን የሚገልጽ ነው፡፡ አንዳንድ በዘመነ ኦሪት የነበሩ ሥርዓቶች በዘመነ ትንሳኤም ሊተገበሩ ይችላሉ፡፡ ምንም እንኳን ይህ የፋሲካ ጨዋታ የተጀመረበትን ጊዜ የሚገልጽ ማስረጃ

ባይኖርም ረዘም ያለ እድሜ እንዳስቆጠረና ከስያሜው ጀምሮ ሃይማኖታዊ መሰረት እንዳለው ከላይ የቀረቡት ገለጻዎች አመላካች ናቸው፡፡

በጨዋታው የሚታዩ የደስታና የፈንጠዝያ ሁኔታዎችን በመጽሃፍ ቅዱስ በማቴ 27፡56 እና ዮሐ 20፡1-18 ከተጠቀሰው የመግደላዊት ማሪያም ታሪክ እና ከቤተክርስቲያን ሥርዓት ጋር በማዛመድ ጨዋታው ሃይማኖታዊ ተምሳሌትነት እንዳለው የገለጹልን አሉ፡፡

> *አብዛኛውን ጊዜ የልጃገረዶች የፋሲካ የጨዋታ መነሻ ተብሎ የሚጠቀሰው በሃይማኖቱ ስንወስድ የክርስቶስ ትንሳኤ ነው፡፡ የጌታን ከሙታን ተለይቶ መነሳት ቀድማ ያየችው ማሪያም መግደላዊት ናት፡፡ ቅድሚያ ያበሰሩት ሴቶች ናቸው፡፡ በዚህ ጨዋታም ዋና ተሳታፊዎቹ ሴቶች ናቸው፡፡ በጨዋታው የሚጨፍሩት የሚደሰቱት ሴቶች ናቸው፡፡ ይህም ከትንሳኤው ብስራት ጋር ይያያዛል፡፡ ከትንሳኤ ማግስት ማለትም ከሰኞ እስከ ዳግም ትንሳኤ ድረስ ቤተክርስቲያን እያንዳንዱን ቀን ሃይማኖታዊ ስያሜ/ትርጉም ሰጥታ ታከብራለች፡፡ ልጃገረዶቹም በተመሳሳይ ሳምንቱን ሙሉ ይጫወታሉ፡፡ (ህይወት ታደሰ ቃለ መጠይቅ፣ ዓለም ከተማ፣ ሚያዝያ 2015 ዓ.ም)*

በዚህ ጨዋታ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ትውፊት ያላቸው ጨዋታዎች ይከወናሉ፡፡ በጨዋታው የሚታዩ የክዋኔ ሂደቶችን በማሳያነት በማንሳት ጨዋታው ከሃይማኖት ጋር ያለውን ቁርኝት ያስረዳሉ፡፡ ይሄውም በአብዛኞቹ ጨዋታዎች (ለአብነትም፡- በዝሎሽ፣ በማሬ ዘንባባዬ፣ በአጋጋሙዬ ጨዋታዎች) የሚስተዋሉ የመንተት፣ የመገፋፋት፣ የመሸከምና የመደብደብ ድርጊቶችና ሁኔታዎች የክርስቶስን እንግልትና መከራ የሚገልጹ ማሳያዎች እንደሆኑ መምህር ጸጋዘአብ *ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዝያ* 2015 ዓ.ም) ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ ጨዋታው በዓመት አንድ ጊዜ እንደሚከወን፣ ማህበራዊ ትስስርን/ግንኙነትን እንደሚያጠናክር፣ በረጅም ጊዜ ሂደት ባህላዊ መሰረት እየያዘ እንደመጣ፣ ሃይማኖታዊ መሰረት እንዳለውና ረዘም ያለ እድሜን እንዳስቆጠረ ከላይ የተገለጹት ምክንያቶች ያመላክታሉ፡፡

### 5.2 ለጨዋታው የሚደረግ ቅድመ ዝግጅት

የትንሳኤን በዓል ጠብቆ በዓመት አንድ ጊዜ የሚከወነው የፋሲካ ጨዋታ በልጃገረዶች በጉጉት የሚጠበቅና ከበዓሉ ቀደም ብሎ ልዩ ልዩ ቅድም ዝግጅቶች የሚደረጉበት ነው፡፡ ቅድመ ዝግጅቱ የሚደረገው በሁለት መንገድ ነው፡፡ አንደኛ በጨዋታው አምረው ለመገኘት በአልባሳትና ጌጣጌጥ በኩል የሚያደርጉት ቅድመ ዝግጅት ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ ከእለት ተዕለት የስራ ጫና ተላቅቀው በነጻነት በጨታው ለመሳተፍ የሚያደርጉት ቅድመ ዝግጅት ነው፡፡

በዚህ ጨዋታ ላይ ለመታደም ልጃገረዶቹ ብዙ ቅድመ ዝግጅቶች ያደርጋሉ፡፡ ከቅድመ ዝግጅቶቹ መካከል የመጀመሪያው በአልባሳትና ጌጣጌጥ ረገድ የሚደረገው ዝግጅት ነው፡፡ ለምሳሌ ጾሙ (ዓብይ ጾም) ከገባ ጀምሮ በአካባቢው ባለሙያዎች የሚሰራ ባህላዊ የቆዳ ጫማ ተሰርቶ ጭስ ላይ ይሰቀላል፡፡ ጭስ ላይ እንዲሰቀል የሚደረገው እንዲለሰልስና መልኩ እንዲያምር ነው፡፡ እሁድ ትንሳኤ ሊሆን የሹር ቅዳም እለት ወርዶ ለስላሳና ለእግራቸው የሚመች እንዲሆን ሎሚና መቅኒ ወይም ቅቤ ይቀባል፡፡ ይህን የቆዳ ጫማ ማዘጋጀት ያልቻለች ልጃገረድ ዘመን አመጣሽ የፕላስቲክ ጫማ ትገዛለች/ታስገዛለች፡፡


ምስል 6፡- በአካባቢው ባለሙያዎች የሚዘጋጅ የቆዳ ጫማ



(በህይወት ታደሰ የእጅ ስልክ የተነሳ፣ መጋቢት 2015 ዓ.ም)

ከልብስ መቀነት፣ አንገት ልብስ፣ ቀሚስ፣ አሁን ቢቀየርም ሙሉ ለሙሉ ከጥጥ የተሰራ ቀሚስ ለጨዋታው ከሚያዘጋጇቸው አልባሳት መካከል የተወሰኑት ናቸው፡፡ መግዛት ያልቻሉ ደግሞ ያላቸውን የክት ልብስ በተለየ ሁኔታ በሳሙና ወይም በእንዶድ አጥበውና የተለያዩ ስራስሮች ፈልገው አጥነው (እንደ ሽቶ ለመጠቀም) ያስቀምጣሉ፡፡ ለጨዋታው የሚጠቀሙባቸውን የተለያዩ ጌጣጌጦች ማሟላት ሌላው የቅድመ ዝግጅት አካል ነው፡፡ ከጌጣጌጦቹ መካከል አርጌሽ ልሙት፤ ማተብ፤ ድንብል፣ አሸንክታብ፣ ቁርበተ ሐሊም፣ መስቀል፣ ጸጉር ላይ የሚደረግ ወለባና አንባር ይጠቀሳሉ፡፡

ምስል 7፡- ልጃገረዶቹ በጨዋታው ከሚያደርጓቸው ጌጣጌጦች መካከል ጥቂቶቹ (ከግራ ወደ ቀኝ አሸንክታብ፣ አርጌሽ ልሙት እና የብር አንባር)



(በህይወት ታደሰ የእጅ ስልክ የተነሳ፣ መጋቢት 2015 ዓ.ም)

ከበዓሉ ቀደም ብለው ዓይናቸውን ይኳላሉ፤ ፀጉራቸውን ይሰራሉ፡፡ ልጃገረዶቹ ከሚያጌጡባቸው የፀጉር አሰራር አይነቶች መካከል ዛሌዋ፣ ልምጭ ከዱላ፣ አሣ ስሬት የሚባሉት ይጠቀሳሉ፡፡ ጨዋታው ከመድረሱ በፊት ፀጉራቸውን ተሰርተው በበዓሉ ለመታደም ዝግጅት ያደርጋሉ፡፡

ለበዓሉ አዲስ ልብስና ጌጣጌጥ ማስገዛት ባይችሉ እንኳን ከሌሎች ይዋሳሉ ወይም አዲስም ባይሆኑ ያሏቸውን የክት ልብሶች ያጥባሉ፡፡ በእለቱ ወንዶች ሚስት የምትሆናቸውን የሚመርጡበት፣ ቤተሰብም የማን ልጅ እንደሆነች፣ ቀድማ መታጨት አለመታጨቷን፣ ለጋብቻ የምትመጥን መሆኗን፣ ዝምድና አለመኖሩን፣ ወዘተ የሚያጠናበት ዝግጅት ስለሆነ አቅም በፈቀደ መጠን አምራና አጊጣ ለመገኘት ትጥራለች፡፡ በአጠቃላይ በዓሉን በጥሩ መንፈስ ለመቀበልና በጨዋታው ላይ አምረው ለመገኘት አቅም የፈቀደውን ሁሉ ያደርጋሉ፡፡

> *ለበዓሉ ተብሎ ልብስና ጫማ ይገዛላቸዋል፡፡ ያልተገዛላቸው የክት ልብሳቸውን ያዘጋጃሉ፡፡ ጌጣጌጥ ይገዛሉ፡፡ በዓሉ ሲቃረብ (ከበዓሉ በፊት) ልብስ ይታጠባል - የቤተሰቦችቸውን ጭምር፡፡ ገላቸውን ይታጠባሉ፡፡ ጸጉራቸውን ሹሩባ ይሰራሉ፡፡ ኩል ይኳላሉ፡፡ ቤት ያጠዳሉ፣ በበህላዊ መንገድ ያስጌጣሉ፡፡ በእለቱ በአልባሳትና ጌጣጌጥ አምረው፣ ደምቀው ወንዶችን በሚያማልል መልኩ ወደጨዋታው ይመጣሉ፡፡ (የማሪያምወርቅ ቃለ መጠይቅ፣ ዓለም ከተማ፣ ሚያዝያ 2015 ዓም)*

ምስል 8፡- ልጃገረዶች ለጨዋታው የሚሆኑ አልባሳትና ጌጣጌጥ ሲገዙ




(ዓለም ከተማ ፣ በህይወት ታደሰ የእጅ ስልክ ገበያ ላይ የተነሳ፣ መጋቢት 2015 ዓ.ም)

በዚህ ጨዋታ የሚታደሙ ልጃገረዶችን እናቶቻቸውና ታላላቅ እህቶቻቸው ያግዟቸዋል። ለጨዋታ ሲወጡ ይበልጥ አምረው እንዲታዩ "እንደዚህ ለብሰሽ፣ እንደዚህ አጊጠሽ፣ እንደዚህ ጫማ አድርገሽ " በማለት የማስዋብ ሚናቸውን ይወጣሉ። በአጠቃላይ ቅድመ ዝግጅታቸውን አጠናቅቀው ለበአሉ የተዘጋጁ ልብሶችን ለብሰውና ጌጣጌጦችን አድርገው በተለየ ሁኔታ  አምረው ወደ ጨዋታው ይሄዳሉ።

ሁለተኛው ከስራ አኳያ የሚኖረው ቅድመ ዝግጅት ነው። ስራ እንዳይደራረብባቸውና በነጻነት በጨዋታው ላይ ለመሳተፍ እንዲችሉ ልዩ ልዩ ቅድመ ዝግጅቶችን ያደርጋሉ። ለሳምንት የሚበቃ እንጨት ለቅመው ያከማቻሉ። ደጋ የሚኖሩ ከሆነ ቀደም ብለው ቆላ ወርደው እንጨት ይሰብራሉ። ለከብት መኖ ያዘጋጃሉ። ከብት የሚቆጣጠረው ከጨዋታው ውጭ ያለ የቤተሰብ አባል ይሆናል። እቤት ያለ ሰው እንስሳቱን ውሃ እያጠጣ፣ መኖ (ጭድና ገለባ) እየሰጠ ይቆጣጠራል።

> *በአዘቦት ቀን ቆላ ሄደው እንጨት የምናመጣው አንድ ጊዜ ሊሆን ይችላል። ፋሲካ ሲመጣ ግን በቀን ሁለት ጊዜ ልንሄድ እንችላለን። በቀን ሁለት ጊዜ ሄደን እንጨት ለቤተሰብ እናከማቻለን። የከብት መኖ እናዘጋጃለን። ስፌት ሰፍተን ለምታገባ ጓደኞችን እንሰጣለን። ያን ሁሉ ስራ የምናጠናቅቀው ከጨዋታው ቀደም ብሎ ባለው ወቅት ነው። ይሄ ይሄን ሁሉ ስራ እንሰራለን። ልክ ከፋሲካ እለት ጀምሮ እስከ ዳግሚያ ትንሳኤ ድረስ ከመብላት፣ ከመጠጣት፣ ራሳችንን ከማስዋብ እና በጨዋታው ላይ ታድሞ ከመጫወት በስተቀር ሌላ ስራ አንታዘዝም። (ወጣት ተናኘ ገላው ቃለ መጠይቅ፣ አፈዘዝ ቀበሌ፣ ሚያዝያ 2015 ዓም)*

በአጠቃላይ የፋሲካ በዓልን ጠብቆ በዓመት አንድ ጊዜ የሚከናወን በመሆኑ በልጃገረዶቹ /በጨዋታው ተሳታፊዎች/ በጉጉት የሚጠበቅ ነው፡፡ ለዚህም ሲባል ከበዓሉ ቀደም ብሎ ከአልባሳትና ጌጣጌጥ  በተጨማሪ ሳምንቱን ሙሉ በነጻነት በክዋኔው ላይ ለመሳተፍ እንዲችሉ በቂ ቅድመ ዝግጅት ያደርጋሉ፡፡

## 5.3 በጨዋታው የወጣት ወንዶችና ተሳታፊዎች ሚና

በዓሉ/ጨዋታው የሴቶች ነው፡፡ ልጃገረዶች ሳምንቱን ሙሉ ከስራ ነጻ ሆነው የተለያዩ ጨዋታዎችን የሚጫወቱበትና የሚደሰቱበት ነው፡፡ ያ ማለት ግን ወንዶች ጭራሽ አይሳተፉም ማለት አይደለም፡፡ ክዋኔ ታዳሚው የከዋኙን ባህላዊ ክህሎት ገምግሞ የሚመዝንበት፣ ለክወናው መፍዘዝም ሆነ መድመቅ የታዳሚው ሚና ወሳኝ የሆነበት እንደሆነ ከ Bauman (1975) ገለጻ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ወጣት ወንዶችና ሌሎች ታዳሚዎች ከልጃገረዶቹ ጋር ደስታቸውን ለማሳለፍ ሲሉ ዙሪያውን ከበው ጨዋታውን ያደምቃሉ፡፡ በጨዋታው የተሻለ ብቃት ያሳዩትን ያደንቃሉ፡፡ ወጣት ወንዶች እንደ ዱላ ምት፣ አንቀባረኝ፣ ድቅ ድቅ፣ ያዕቆብ፣ አልሞ መቀላት የሚባሉ የራሳቸውን (የወንዶች) ጨዋታዎችን ይጫወታሉ፡፡ አልፎ አልፎ ሲፈቅዱላቸው ከሴቶች ጋር  በመሆን በዝሎሽ ጨዋታ ይሳተፋሉ፡፡

ወጣት ወንዶች ጨዋታውን ከማድመቅ ባሻገር ለጨዋታው የመጡ እህቶቻቸውን ወይም እጮኛዎቻቸውን ችግር እንዳይገጥማቸው ሊጠብቁ ይችላሉ፡፡ ልጃገረዶችን ከጸብ አጫሪ ወንዶች፣ ከጠለፋና አላስፈላጊ ጉንተላ ይጠብቃሉ፡፡ በተለይም በተደጋጋሚ ለትዳር ጠይቆ ቤተሰብ በዘር፣ በሃብት ወይም በስንፍና "ለእከሌ ልጃችንን አንድርም" ተብሎ የተከለከለ ጎረምሳ /ጋብቻ ጠያቂ/ አሳቻ ቦታና ጊዜ ጠብቆ ለጠለፋ ሊመጣ ይችላል፡፡ ስለዚህ ይህን ድርጊት ለመከላከል ወይም ሴቶቹን ለመጠበቅ የሚመጡ ወጣቶችም በጨዋታው ይታደማሉ፡፡

ምስል 9፡- ወጣት ወንዶች ዙሪያውን ከብበው የልጃገረዶቹን ጨወታ ሲመለከቱ



(በአጥኚው የእጅ ስልክ የተነሳ፣ ግሬት ቀበሌ ሚያዝያ 2015 ዓ.ም)

ሌላው በጨዋታው ላይ ተመልክቶ ሚስት የምትሆነውን ልጃገረድ ለመምረጥ የሚመጣ ጎረምሳም አለ፡፡ ይህ ጨዋታ ለትዳር የሚፈላለጉ ወጣቶች የሚገናኙበት አጋጣሚ ስለሆነ ወንዱ የሚፈልጋትን ሊመርጥና እንድትታጭለት ለቤተሰብ ሊያሳውቅ ይችላል፡፡ ስለሆነም በክዋኔው አንዱ የወንዶች ሚና ከጨዋታው ተሳታፊዎች ሚስት የምትሆናቸውን መምረጥና ለቤተሰብ ማሳወቅ ነው፡፡

"በዘመድ ልጅ ወይም በሌላ እኩያ ልጀገረድ አማካይነት የመረጣት ልጅ በትክክል እንድትታይ ምልክት ይሰጣል፤ ምርጫውንም ለቤተሰቡ አባል ያሳውቃል፡፡ የልጁን ምርጫ የሰማው ቤተሰብም ተጨማሪ ጥናት አድርጎ 'ልጃችሁን ለልጃችን' ወደሚል ጥያቄ ሊያመራ ይችላል፡፡" (ወ/ሮ ሽቶ አበበ *ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዝያ* 2015 ዓ.ም)

እንደ ልጃገረዶቹ ሁሉ ወጣት ወንዶችም ለጨዋታው ተዘጋጅተው የክት ልብሳቸውን ለብሰው፣ አምረው ይመጣሉ፡፡ አብዛኛዎቹ ወጣት ወንዶች አረንጓዴ ቀለም ካለው ጨርቅ የሚሰራ የአዝራር ጌጥ የበዛበት ጉርድ ሸሚዝና ቁምጣ ይለብሳሉ፤ እህል ውሃ የማያሰኝ ባለ ጅና ዱላ/ሽመል/ ከእጃቸው አይለይም፡፡ ይህ አጋጣሚ የሚፈልጓትን ቆንጆ የሚያዩበት /የሚመርጡበት/ በመሆኑ አምረውና ፀድተው፣ መፋቂያቸውን ሰክተው ነው የሚታደሙት፡፡

በጨዋታው የወጣት ወንዶችን ሚና በሚመለከት (ጸጋዘአብ *ቃለ መጠይቅ፣ አፊዘዝ ቀበሌ፣ ሚያዝያ* 2015 ዓ.ም) *እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡*

*በጨዋታው ውስጥ ልባቸውን የምታማርክ ቆንጆ ካዩ ለሚስትነት ይመርጣሉ። ፍላጎታቸውንም ለቤተሰብ ያሳውቃሉ። ሴቶቹ ወንዶችን ሲያሞግሱ ወይም ሲያንኳዋስሱ ወንዶችም በቡድን በመሆን መልስ የሚሰጡበት ጨዋታ ይጫወታሉ። በጨዋታው ዋነኛው የወንዶች ሚና በጨዋታው ሜዳ ዙሪያ ተቀምጠው የሴቶቹን ጨዋታ መመልከት፣ ማድነቅ፣ ማድመቅ፣ ማበረታታት፣ በጭብጨባ ወይም በድምጽ አድናቆታቸውን መግለጽ፣ ማጀብና ከአላስፈላጊ ትንኮሳ መከላከል ነው።*

ከወንዶች በተጨማሪ ህጻናት እና እናቶች ይታደማሉ። ህጻናቱ ታላላቆቻቸውን በመከተል እድሜአቸው ወይም አቅማቸው የሚፈቅድላቸውን ጨዋታ ይጫወታሉ። ወጣት ሴቶች ሲጫወቱ ከኂላቸው በመሆን/በመከተል/ ከታላላቆቻቸው ልምድ ይቀስማሉ። እናቶች ደግሞ ጨዋታውን ከማድመቅና ጥሩ ተጫዋቾችን ከማበረታታት ባሻገር በአንዳንድ ጨዋታዎች ላይ ይሳተፋሉ፤ እነሱ ከሚያውቁት የተለየና የተሳሳተ አቀራረብ ሲመለከቱ ያርማሉ፤ እንዲስተካከል በማድረግ አዎንታዊ ሚና ይጫወታሉ።

በአጠቃላይ በዚህ ሁነት ከዋነኛ ተሳታፊ ልጃገረዶች ውጭ የሚታደሙ ወጣት ወንዶች፣ እናቶች እና ህጻናት የሜዳውን ዙሪያ ከብበው ለልጃገረዶቹ ጨዋታ ድምቀት ይሰጣሉ፤ የራሳቸውን ጨዋታ ይጫወታሉ። በተጨማሪም በተለይ ወጣት ወንዶች ጨዋታው በሰላም እንዲከወንና ልጃገረዶቹ ችግር እንዳይገጥማቸው በማድረግ በኩል የላቀ ሚና አላቸው። የጨዋታው ተሳታፊዎች ከሩቅና ከቅርብ ንዑስ ቀበሌወች የሚመጡ ስለሆኑ ጨዋታው ተጠናቅቆ ወደየቤታቸው ሲመለሱም የወንዶቹ ጥበቃና አጋርነት የሚዘልቅ ይሆናል።

### 5.4 የጨዋታዎቹ ዓይነት እና ክዋኔ

ክዋኔ በቦታ፣ በሁኔታና በጊዜ የተወሰነ፣ ተለዋዋጭ ባህሪ ያለው፣ ሂደታዊ፣ በቃል በድርጊትና በቁሳቁስ የሚቀርብ ማህበራዊ ጥበብ እንደሆነና ውበት ያለው፣ የተቀናጀ፣ በድምጽ ቅላጼና በአካል እንቅስቃሴ ታጅቦ ተደጋግሞ እንደሚቀረብ በምእራፍ ሁለት ከቀረበው ከ *Kapchan (1995)* ገለጻ መረዳት እንችላለን። የመርሐ ቤቴ ልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታም የተጠቀሱት ገለጻዎች የሚገለጡበት፣ በቦታና በጊዜ የተወሰነ፣ በቃልና በድርጊት ሚገለጽ፣ የተቀናጀና ውበት ያለው ነው።

በዚህ የፋሲካ ሳምንት ጨዋታ ከአስር በላይ ጨዋታዎች እንዳሉ/እንደሚከወኑ/ በወረዳው የባህል ባለሙያዎች (ህይወት ታደሰ *ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዝያ* 2015 ዓ.ም) ቢገለጽም በምልከታ፣ በቡድን ውይይትና በቃለ መጠይቅ ማረጋገጥ የተቻለው አጋጋሙዬ/እቶት

እቶቴ/፣ ማሬ ዘንባባዬ፣  ሽወይባ፣ ቡፍጨ ገላ፣ አሽም እምቧ/ነይ ዞማ/፣ ሰላም ሰላሙ፣ ዝሎሽ፣ ቅርጭፋት/ቅርጥፋት/፣ እባብ ወጣዬ እባብ ወረደይ እና ቅጥልጥሎሽ የሚባሉ አስር ጨዋታዎችን ነው፡፡

“Play” የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ለጨዋታ ጥቅል መጠሪያ ሆኖ በውስጡ ውድድራዊ (game) እና የመዝናኛ (Play) ጨዋታዎችን እንደሚያጠቃልል የ Tucker (1948) ገለጻ ያስረዳል፡፡ የፋሲካ የልጃገረዶች ጨዋታዎችንም ካላቸው ባህሪ አኳያ በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ አንደኛዉ ውድድራዊ ባህሪ የሌላቸው በዜማና በግጥም የሚታጀቡ ሲሆኑ ሁለተኛው ደግሞ በዜማ የማይታጀቡና አሸናፊና ተሸናፊ የሚለይባቸው ውድድራዊ ባህሪ ያላቸው ናቸው፡፡

ስለሆነም ጨዋታዎቹ ካላቸው ባህሪ አኳያ በዜማ የሚታጀቡና የውድድር ጨዋታዎች ተብለው በሁለት ተከፍለዋል፡፡ በዚህም መሰረት ስድስት  ጨዋታዎች በዜማ/ግጥም/ የሚታጀቡ ተብለው የተመደቡ ሲሆን ቀሪዎቹ አራት ጨዋታዎች በውድድራዊ ጨዋታዎች ምድብ ስር ተካተዋል፡፡ አብዛኛዎቹ ጨዋታዎች ስያሜአቸውን ያገኙት በጨዋታው ከሚባሉ/ከሚነገሩ ስነቃሎች ውስጥ ከተገኘ ቃል ወይም ሐረግ እና የጨዋታዎቹን ድርጊታዊ እንቅስቃሴ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ቀጥሎ የቀረበው የጨዋታዎቹ ስያሜ፣ ክዋኔ ሂደትና ከጨዋታው ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጉዳዮች በዝርዝር የተዳሰሱበት የጥናቱ ክፍል ነው፡፡

### 5.4.1 በዜማ /በግጥም/ የሚታጀቡ ጨዋታዎች

#### 5.4.1.1 አጋጋሙዬ /ይቶት ይቶቴ/

የአጋጋሙዬ ጨዋታ ስያሜውን ያገኘው በጨዋታው ክዋኔ ወቅት ከሚነገረው ሥነቃል/አዝማች/ ሲሆን ልጃገረዶች በቡድን ከሚከውኗቸው ጨዋታዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ በአጋጋሙዬ ጨዋታ መጀመሪያ ልጃገረዶች እርስ በእርስ ወገባቸውን በመያያዝ ክብ ይሰራሉ ወይም በሁለት ሰልፍ ይደረደራሉ፡፡ ክብ በሰሩት መካከል እስከ ስምንት የሚደርሱ ልጃገረዶች በጉልበታቸው በመንበርከክ የእጆችችውን ጣቶች እርስ በእርስ አቆላልፈው መሬቱን *በስልት* እየመቱ በማዜም የሚጫወቱት ጨዋታ ነው - አጋጋሙዬ፡፡

*አጋጋሙዬን በክብ፣ ከፊትና ኋላ ወይም ከግራና ቀኝ ሆነን የምንጫወተው ጨዋታ ነው፡፡ ይህን ጨዋታ ስንጫወት ግማሾቹ ወይም በቁጥር የሚበልጡት ቆመው ነው፡፡ አውራጅ ወይም ዘፋኝ የሚሆኑት ደግሞ ከ4-8 ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አውራጆቹ የእጅ ጣታቸውን እርስ በእርስ በማቆላለፍ በጉልበታቸው ተንበርክከው መሬቱን እየመቱ /እየደበደቡ/ "አጋጋሙዬ" እያሉ ያዜማሉ፡፡ አጋጋሙዬ የሚለው ዜማ እንዳለቀ ዙሪያውን የቆሙት በተራቸው ይቶት ይቶቴ የሚለውን ዜማ በማስቅጠል አውራጅና ተቀባይ በመሆን እንጫወታለን፡፡ (የክቴ ቃለ መጠይቅ፣ ግሬት ቀበሌ፣ ሚያዝያ 2015 ዓ.ም)*

በዚህ ጨዋታ "አጋጋሙዬ" የሚለውን ዜማ የሚያወርዱት ልጃገረዶች ወደ ግራና ወደ ቀኝ በመወዛወዝ መሬቱን በእጃቸው ከሚመቱበት ስልተ ምት ጋር በማጣጣም አውራጅና ተቀባይ ሆነው ይከውናሉ፡፡

አጋጋሙዬ  አጋጋሙዬ፣
ከፈረስ ጋራ ስራገጥ ውዬ፣
ከዛ ስመለስ ንፍሮ ቀቅዬ፣
ንፍሮ ቀቅዬ ብላ ብለው፣
ጉልቻ አንስቶ ጎኔን ሊለው፣
ከጎኔም ጎኔን ኩላሊቴን፣
እናቴን ጥሯት መድሃኒቴን፣
እሷ ከሌለች መቀነቷን፡፡

እያሉ ያዜማሉ፡፡

በክቡ መሃል ያሉት አጋጋሙዬ የሚለውን ጨዋታ/ዜማ/ ሲጨርሱ ሁሉም በያሉበት እንዳሉ ዜማውንና ግጥሙን በመቀየር ወደ ሁለተኛው ዜማ ይሸጋገራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ዜማ ብቻ ሳይሆን ሚናም ይቀያየራሉ፡፡ ዜማው ተቀይሮ "ይቶት ይቶቴ" በሚለው ጨዋታ አውራጅ የሚሆኑት ክብ ሰርተው የቆሙት ልጃገረዶች ሲሆኑ፣ በክቡ መሃል በጉልበታቸው የተንበረከኩት እዚያው ባሉበት ሆነው ተቀባይ ይሆናሉ፡፡ ዙሪያውን የከበቡት "ይቶት ይቶቴ" ሲሉ መሃል ላይ ያሉት (አጋጋሙዬ ሲሉ የነበሩት) በመቀበል "ወይ እመቤቴ" በማለት በቅብብሎሽ ጨዋታውን ይቀጥላሉ፡፡ በዚህኛው የጨዋታ ጊዜ የሚና መቀያየር ይፈጠራል፡፡

| *አውራጅ* | *ተቀባይ* |
| --- | --- |
| *ይቶት ይቶቴ* | *ወይ እመቤቴ* |
| *እናትሽ ሞተች በድሎቴ* | *እሷስ ትሙት አወጣላታለሁ ቁና ደረቆት* |
| *ይቶት ይቶቴ* | *ወይ እመቤቴ* |
| *አባትሽ ሞተ በድሎቴ* | *እሱስ ይሙት አወጣለታለሁ ቁና ደረቆት* |
| *ይቶት ይቶቴ* | *ወይ እመቤቴ* |
| *እህትሽ ሞተች በድሎቴ* | *እሷስ ትሙት አወጣላታለሁ ቁና ደረቆት* |
| *ይቶት ይቶቴ* | *ወይ እመቤቴ* |
| *ወንድምሽ ሞተ በድሎቴ* | *እሱስ ይሙት አወጣለታለሁ ቁና ደረቆት* |
| *ይቶት ይቶቴ* | *ወይ እመቤቴ* |
| *አጎትሽ ሞተ በድሎቴ* | *እሱስ ይሙት አወጣለታለሁ ቁና ደረቆት* |
| *ይቶት ይቶቴ* | *ወይ እመቤቴ* |
| *እክስትሽ ሞተች በድሎቴ* | *እሷስ ትሙት አወጣላታለሁ ቁና ደረቆት* |
| *ይቶት ይቶቴ* | *ወይ እመቤቴ* |
| *ወዳጅሽ ሞተ በድሎቴ* | *አወይ ወዳጀ ምን አገኘው ምን?* |
| | *አወይ ወዳጀ ምን አገኘው ምን?* |
| | *አወይ ወዳጀ ምን አገኘው ምን?(ተደጋግሞ የሚባል)* |

በዚህ የጨዋታ ጊዜ የወዳጃቸውን ሞት የሰሙትና ተንበርክከው የነበሩት ልጃገረዶች በፍጥነት ካጎነበሱበት ቀና በማለት በእግራቸው ጫፍ ቁርጢጥ ብለው ወደላይ እየዘለሉ/ጢብ ጢብ እያሉ/ “አወይ ወዳጀ ምን አገኘው ምን” የሚለውን ስንኝ ሃዘንን በሚገልጽ ስሜት ደረታቸውን እየደቁ በመደጋገም ይሉታል ወይም ያዜሙታል፡፡ ከእናት ጀምሮ አባት፣ እህት፣ ወንድም፣ ወዘተ ‘ሞተች/ሞተ’ ሲባል “ግድየለም በቁና ደረቆት ተዝካራቸውን አወጣለሁ” ወይንም “ቁረባናቸውን አወጣለሁ” በማለት ሃዘን ሳይሰማቸው ቆይተው፣ “ወዳጅሽ ሞተ” ሲባል ግን ሃዘኑ ከፍ ያለ መሆኑን “አወይ ወዳጀ ምን አገኘው ምን” እያሉ ደረታቸውን በመምታት ሃዘናቸውን ይገልጻሉ፡፡ ይህም ከሌሎች የቤተሰብ አባላት በላይ የወዳጅ/የፍቅረኛ/ ሃዘን የሚፈጥረው ከፍ ያለ የሃዘን ስሜት የሚገለጥበት ሲሆን በዚህ ዓይነት ክዋኔ ጨዋታው ይጠናቀቃል፡፡

ምስል 10፡- አጋጋሙዬ ሲጫወቱ የሚያሳይ ምስል



(በአጥኚው የእጅ ስልክ የተነሳ፣ አፈዘዝ ቀበሌ ሚያዝያ 2015 ዓ.ም)

### 5.4.1.2 ማሬ ዘንባባዬ

የመርሐ ቤቴ ልጃገረዶች በፋሲካ ጨዋታ ከሚጫወቷቸው ጨዋታዎች መካከል ማሬ ዘንባባዬ አንዱ ነው፡፡ ይህን ጨዋታ ለመጫወት በመጀመሪያ ልጃገረዶቹ እርስ በእርስ በመያያዝ ሁለት ረድፍ ይሰራሉ፡፡ ከዚያም ሽብሽባ በሚመስል ሁኔታ ወደ ፊትና ወደ ኋላ ሄድ መለስ እያሉ፣ እግራቸውን ወደ ፊት እያወናጨፉ፣ ዜማ እያወረዱ፣ አውራጅና ተቀባይ በመሆን የሚከውኑት ጨዋታ ነው፡፡ "ይህ ጨዋታ የቡድን ጨዋታ ነው፡፡ ልጃገረዶቹ በሁለት ረድፍ ይሰለፉና አንዱ ረድፍ 'ማሬ ዘንባባዬ' ሲል ሌላኛው ረድፍ 'ዘንባባዬ' በማለት በቅብሎሽ የሚከውኑት ጨዋታ ነው፡፡" (ወጣት መቅደስ *ቃለ መጠይቅ፣ ሚዝያ* 2015)፡፡ ይህ ጨዋታ በውስጡ የተለያዩ የጨዋታ ሂደቶችን/አይነቶችን/ ያካተተ ሲሆን እንደየጨዋታዎቹ አይነት ዜማና ግጥሙም እየተቀያየረ የሚከወን ጨዋታ ነው፡፡

የማሬ ዘንባባዬ ጨዋታ የመጀመሪያው ክፍል "ዘንባባዬ" በሚባለው ዜማ የሚጀምር ሲሆን ልጃገረዶቹ በሁለት ቡድን/ረድፍ/ በመሆን አንዱ ቡድን/ረድፍ/ በሌላ ወገን የተሰለፈውን ቡድን/ሰልፈኛ/፣ "ዘምባባዬ ኧረ ዘምባባዬ እስቲ ዞር በይ" ሲል፣ በአንድ ላይ ከኋላ ለማየት በሚያስችል ሁኔታ ፊታቸውን አዙረው ይቆማሉ፡፡ "ዘምባባዬ ኧረ ዘምባባዬ እስቲ ዞር በይ" ሲባሉ ደግሙ በአንድነት ወደ ጓደኞቻቸው ይዞራሉ፡፡ "ዘምባባዬ ኧረ ዘምባባዬ እስቲ ቁጭ በይ" ሲባሉ በአንድነት ይቀመጣሉ፡፡ "ዘምባባዬ ኧረ ዘምባባዬ እስቲ ብድግ በይ" ሲባሉ በጋራ ይነሳሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ የማሬ ዘንባባዬ ጨዋታ ክዋኔ የመጀመሪያው ክፍል ይካሄዳል፡፡

| አውራጅ | ተቀባይ |
| --- | --- |
| ዘምባባዬ ኧረ ዘምባባዬ | ዘንባባዬ |
| እስቲ ቁጭ በይ | |
| ዘምባባዬ ኧረ ዘምባባዬ | ዘንባባዬ |
| እስቲ ብድግ በይ | |
| ዘምባባዬ ኧረ ዘምባባዬ | ዘንባባዬ |
| እስቲ ዞር በይ | |

እያሉ በአንዱ ረድፍ ያሉ ልጃገረዶች በሌላ ረድፍ ያሉ ጓደኝቻቸውን አለባባስ፣ አጋጊያጥ፣ ጸጉር አሰራር፣ ተክለሰውነት፣ ወዘተ ያደንቃሉ፤ ያሞግሳሉ፡፡

> *እስቲ ቁጭ በሉ፣ እስቲ ብድግ በሉ በማለት ቁጭ ሲሉ አቀማመጣቸውን፣ ሲነሱ አነሳሳቸውን ተክለ ቁመናቸውን፣ የእግራቸውን ቅርጽ በማየት ይሞጋገሳሉ ወይም ይተቻቻሉ፡፡ በተጨማሪም የተጠቀሙትን ጌጣጌጥ፣ የለበሱትን አልባሳት ለማሞገስ እንዲመቻቸው ተነሱ፣ ተቀመጡ፣ ወደ ፊት ዙሩ፣ ወደ ኋላ ዙሩ በማለት አጠቀላይ አካላዊ ገጽታቸውን በመመልከት አንዱ ረድፍ ገምጋሚ ይሆናል፡፡ በመቀጠል ሌላኛው ረድፍ እየተተተካ በፈረቃ እየተቀባበሉ ይሞጋገሳሉ፡፡ (የማሪያምወርቅ ቃለ መመጠይቅ፣ ዓለም ከተማ፣ ሚያዝያ 2015)*

በጨዋታው አውራጅ የነበረው ቡድን እንደገና ተቀባይ በመሆን ሚናቸውን እየቀያየሩ እርስ በእርስ ይሞጋጋሳሉ ወይም ይነቃቀፋሉ፡፡

ለምሳሌ፡- በጨዋታው ሁሉንም አሟልታ ከተገኘች፣

"ጓዴ ባልንጀሬ ልሁን ከኳላሽ፣

ለመልክሽም አይደል ለቁምነገርሽ፤" በማለት ቁምነገረኝነቷን ያሞግሳሉ፡፡

የማትፈትልና ሰነፍ ከሆነች ደግሞ፣

"ጣቷ ረጃጅም ነው ቂጣ ለመጋገር፣

እንዝርት አታሳዩአት ትጠፋለች ካገር፤" በማለት ሙያ ቢስነቷን ይተቻሉ፡፡

በሁለተኛው የጨዋታ ክፍል ወደ መጓተት የጨዋታ ሂደት ይቀየራል፡፡ "ዙሪ፣ ቁጭ በይ፣ ተነሽ" የሚሉት በሁለት ምክንያት ነው፡፡ አንደኛው ጓደኞቻቸው ለበዓሉ አምረው መምጣት አለመምጣታቸውን በመገምገም ለማሞገስ ወይም ለመንቀፍ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ

አንደኛው ቡድን ከሌላኛው ረድፍ የሚፈልጋትን ለመውሰድ/ለመምረጥ/ ነው፡፡ በዚህም በአንዱ ረድፍ ያሉት በተቃራኒ ሰልፍ ካሉት ልጃገረዶች መካከል አንዷን ልጅ እንዲሰጧቸው ይጠይቃሉ፡፡ ተጠያቂዎቹም "ጎበዝ የሆነ ይውሰድ" የሚል መልስ ይሰጣሉ፡፡ ከዚያም ወደየራሳቸው ቡድን ለመቀላቀል የሚደረገው ግብ ግብ/መሳሳብ/ ይቀጥላል፡፡

አንዱ ቡድን በዜማ "ዛሬ በማለዳ ማንን ትፈልጋላችሁ" ሲል በሌላኛው ቡድን ያሉት ስም ጠርተው "እከሊትን እንፈልጋለን" ይላሉ፡፡ አሁንም የመጀመሪያው ቡድን እንደገና "እሷን መጥቶ እሚወስድ ማን ጎበዝ አለና" ሲል ሁለተኛው ቡድን "ማን አላችሁ እከሊትን የምትወስድላችሁ" በሚል ወደ እጅ ለእጅ መሳሳብ ጨዋታ ይሸጋገራሉ፡፡

ከዚያ ከአንዱ ሰልፍ አንዲት ከሌላኛው አንዲት ልጃገረድ በመሆን ፊት ለፊት እጅ ለእጅ በመያያዝ ለመጓተት ይዘጋጃሉ፡፡ ከእያንዳንዱ ቡድን የተመረጡት ልጃገረዶች በልብሳቸው ወይም በአፈር እጃቸውን ጠራርገው ወደ ራሳቸው ቡድን ለመቀላቀል መጓተት ይጀምራሉ፡፡ በሁለቱም ወገን ያሉት አባላት ደግሞ "የኛ ልጅ በርች በርች እንዳትረች" እያሉ የእነሱ ቡድን አባል እንዳታሸነፍ ያበረታታሉ፤ ጨዋታውን ያደምቃሉ፡፡ ጎትቶ የመውሰድ አቅም ያለው ተጫዋች ወደ ራሱ ቡድን መቀላቀል ይችላል፡፡ የመጓተቱና ወደራስ ቡድን የመቀላለቀሉ ጨዋታ ብዙ የቡድን አባል ባመጣው ቡድን አሸናፊነት ይደመደማል፡፡

የመጓተቱ ጨዋታ እንደተጠናቀቀ የማሬ ዘንባባዬ ጨዋታ ወደ ሶስተኛው የጨዋታ ክፍል/ዓይነት/ ይሸጋገራሉ፡፡ በዚህ ጨዋታ አንዱ ቡድን ሌላኛውን ቡድን የተለያዩ ምርቶችን እየጠሩ እንዲለውጧቸው ይጠይቃሉ፡፡ አንዱ ቡድን "ጌሾ ለውጡን" ሲል ሌላኛው ቡድን "እኛ ለውጠናል እናንተ ለውጡ" በማለት በምልልስ ጨዋታውን ያስቀጥላሉ፡፡

| <u>አውራጅ</u> | <u>ተቀባይ</u> |
|---|---|
| *ጌሾ ለውጡን* | *እኛ ለውጠናል እናንተ ለውጡ፣* |
| *አብሽ ለውጡን* | *እኛ ለውጠናል እናንተ ለውጡ፣* |
| *አተር ለውጡን* | *እኛ ለውጠናል እናንተ ለውጡ፣* |
| *ምስር ለውጡን* | *እኛ ለውጠናል እናንተ ለውጡ፣* |

እየተባባሉ የቀድሞው የገበያ ስርዓት "የልውውጥ" ሂደት እንደነበረው በሚያመላክት ሁኔታ ይጫወታሉ፡፡

በመቀጠል የሴቶች የወግ እቃዎች ጥያቄ የሚቀርብበት አራተኛው የጨዋታ ክፍል ይቀጥላል፡፡ በተለይ ሴቶች ሲያገቡ በስጦታነት የሚበረከትላቸው የወግ እቃዎች ማለትም እንደ አገልግል፣ አደስ ቅል፣ ቅቤ ቅል፣ እንዝርት፣ ወዘተ የመሳሰሉት የወግ እቃዎች በጠያቂና መላሽ መልክ አንድ በአንድ እየተጠቀሱ ጨዋታው ይቀጥላል፡፡ አንዱ ቡድን "አገልግሌን አልኩሻ" ሲል ሌላው ቡድን "የለኝም አልኩሻ" በማለት በምልልስ ጨዋታው ይካሄዳል፡፡

| *__አውራጅ__* | *__ተቀባይ__* |
| --- | --- |
| *አገልግሌን አልኩሻ* | *የለኝም አልኩሻ* |
| *አደስ ቅሌን አልኩሻ* | *የለኝም አልኩሻ* |
| *ቅቤ ቅሌን አልኩሻ* | *የለኝም አልኩሻ* |
| *ተይ ስጭኝ አታስመጭኝ (2)* | |
| *ተይ ስጭኝ አታስሩጭኝ (2)* | |
| *ላታመልጭኝ አታስሩጭኝ (2)* | |

በመጨረሻም "ተይ ስጭኝ አታሩጭኝ" እያሉ ወገባቸውን ሳይላቀቁ ወደፊትና ወደኋላ እያሸበሸቡና እግራቸውን እያስወነጨፉ ወደ ላይ እየዘለሉ በመጫወት የማሬ ዘንባባዬ ጨዋታ ፍጻሜ ይሆናል፡፡

በዚህ ጨዋታ ከመሞጋገስና ከመነቃቀፍ በተጨማሪ አዝዕርትና የሴት የወግ እቃዎች በስም እየተጠቀሱ ይታወሳሉ፡፡ ጨዋታው እነዚህ የምርት ዓይነቶችና የወግ እቃዎች እንዳይረሱና ከትውልድ ወደትውልድ እንዲሸጋገሩ በማድረግ በኩል ድርሻ ይኖረዋል፡፡

ምስል 11፡- ማሬ ዘንባባዬ ሲጫወቱ የሚያሳይ ምስል (አገሪት ቀበሌ ሚያዝያ 2015 ዓ.ም)



### 5.4.1.3 ሽወይባ

ሽወይባ ጨዋታ ከቅርጽ አኳያ እንደ እሽም እምቧ አይነት ሲሆን ከዋኞቹ ክብ ሰርተው ወይም ከግራና ከቀኝ በመሆን ወገብ በመያያዝና በመተቃቀፍ እየዘለሉና እየተሽከረከሩ፣ ወደፊትና ወደኋላ እየሮጡ ስለ አለባበሳቸው፣ ስለተጠቀሙት ጌጣጌጥ፣ ስለ ጸጉር አሰራራቸው፣ ስለ ትዳር ታላቅነት፣ ወዘተ እያዜሙ/እያነሱ/ የሚሞጋገሱበትና የሚተቻቹበት ጨዋታ ነው፡፡

ምስል 12፡- ሽወይባ ሲጫወቱ የሚያሳይ ምስል



(በአጥኚው የእጅ ስልክ የተነሳ፣ አፈዘዝ ቀበሌ ሚያዝያ 2015 ዓ.ም)

ይህ ጨዋታ ልጃገረዶቹ ክብ ሰርተው ወገብ ለወገብ በመያያዝ/በመተቃቀፍ/ አወራጅና ተቀባይ በመሆን የሚከወን ጨዋታ ነው፡፡

| <u>አውራጅ</u> | <u>ተቀባይ</u> |
|---|---|
| *ኧረ ሽወይባ* | *ሽወይባ* |
| *ኧረ ሽወይባ* | *ሽወይባ* |
| *ሽማውም ሽማ ነው* | *ሽወይባ* |
| *የጥፍጥሬ ወንድም* | *ሽወይባ* |
| *አትለመጭብኝ* | *ሽወይባ* |
| *መለመጥ አልወድም* | *ሽወይባ* |
| *ኧረ ሽወይባ ደምሴ ሐር ነው ቀሚሴ* | *ኧረ ሽወይባ ደምሴ ሐር ነው ቀሚሴ* |

እያሉ በሆታ አይነት አጨዋወት ይጫወታሉ፡፡

ወገብ ለወገብ በመያያዝ እየጨፈሩ የጨዋታውን ሜዳ ያካልላሉ፡፡ ጨዋታው በሩጫ ሜዳውን ማካለል ስለሚጠይቅ በእድሜና በአካል ተመጣጣኝ የቡድን አባላት ይሳተፉበታል፡፡ በጨዋታዉ ላይ ንቃት የሚጎድላቸው /ልግመኞች/ ይተቻሉ፡፡ ጎበዞቹ ይደነቃሉ፡፡ በአለባበስና በውበት የላቀችው ትሞገሳለች፤ እንደነገሩ ሆና የመጣችው ደግሞ ዘለፋ ይገጥማታል፡፡

### 5.4.1.4 ቡፍጬ ገላ

ቡፍጬ ገላ ከመርሐ ቤቴ የፋሲካ የልጀገረዶች ጨዋታዎች መካከል ሌላው የጨዋታ አይነት ነው፡፡ ይህ ጨዋታ ፊት ለፊት በመሆን እጅ ለእጅ በመያያዝ እግራቸውን መሬት ላይ ተክለው ወደኋላ በመለጠጥ እየተሽከረከሩ የሚከውኑት የጨዋታ አይነት ነው፡፡

በዚህ ጨዋታ ሁለት ልጃገረዶች እጅ ለእጅ ተያይዘው አውራጅና ተቀባይ በመሆን የሚከተሉትን ዓይነት ስነ ቃሎች እየደረደሩ በፍጥነት ይሽከረከራሉ፡፡ በመጀመሪያ ሁለቱ ተጫዋቾች ፣

*ቡፍጨ ገላ ያብሽ ገለባ*

*ሜዳ ነው ብዬ ገደል ልገባ*

*ቡፍ ቡፍ ቡፍ*

የሚለውን አዝማች በጋራ ካሉ/ካዜሙ/ በኋላ ጨዋታው አውራጅና ተቀባይ በመሆን ተከታዩ የጨዋታ ክፍል ይቀጥላል፡፡

| <u>አውራጅ</u> | <u>ተቀባይ</u> |
|---|---|
| *ባልሽ የት ሄደ* | *ዘመቻ* |
| *ምን ሊያመጣልሽ* | *ስልቻ* |
| *ባልሽ የት ሄደ* | *ከቆላ* |
| *ምን ሊያመጣልሽ* | *ጠገራ* |
| *የባልሽ ቂጣ* | *እንኩትኩቱ ይውጣ (በመደጋገም የሚባል)* |

እያሉ ይሽከረከራሉ፡፡ ሌሎቹ ዙሪያውን ከብበው ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡ በጭብጨባና በድምጽ ያበረታታሉ፡፡ ጨዋታው በዜማና ግጥም ስለሚታጀብ እንጅ ውድድራዊ ባህሪም አለው፡፡

ሁለቱ ከዋኞች እጅ ለእጅ ተያይዘው በሚሽከረከሩበት ጊዜ ቀድማ የደከመች ወይም 'በቃኝ' ያለች ልጅ በጨዋታው ተሸናፊ ትሆናለች፡፡

ምስል 13፡- ልጃገረዶቹ ቡፍጨ ገላ ሲጫወቱ



(በአጥኝው የእጅ ስልክ የተነሳ፣ ዓለም ከተማ/ቂራ ሚያዝያ 2015 ዓ.ም)

### 5.4.1.5 አሽም እምቧ/ነይ ዞማ/

የእሽም እምቧ ጨዋታ ክዋኔ ልጃገረዶቹ/ተጫዋቾቹ/ ክብ በመስራትና ወገብ በመያያዝ ወደ ፊትና ወደ ኋላ እየሮጡ አውራጅና ተቀባይ በመሆን ስንኞችን እየደረደሩ በቡድን የሚጫወቱት ጨዋታ ነው፡፡

> *በዚህ የፋሲካ ጨዋታ ከሚከወኑት ጨወታዎች መካከል እሽም እምቧ ሌላው የጨዋታ አይነት ነው፡፡ ይህ ጨዋታ በዜማ የሚቀርብ ዘፈን አዘል ጨዋታ ነው፡፡ በዚህ ጨዋታ አውራጅና ተቀባይ በመሆን የሚጫወቱት ሆታ የሚመስል ጨዋታ ነው፡፡ አካባቢያቸውን ያሞግሳሉ፤ ቁንጅናቸውን ያሞግሳሉ፡፡ ጀግና እና መልካም ገበሬ ይሞገሳል፡፡ ሰነፍ፣ ፈዛዛ እና ዓይነ ግቡ ያልሆኑ ወጣት ወንዶችንና ጓደኞቻቸውን በግጥም ይተቻሉ፡፡ (አሰገደች ቃለ መጠይቅ፣ ግሬት፣ ሚያዝያ 2015)*

ይህ ጨዋታ እርስ በእርስ ወገብ በመያያዝ ከዋኞቹ የዜማውን ምት ጠብቀው በፍጥነት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የሚታጀብ ነው፡፡ በዚህ ጨዋታ ዋና ዋና ማህበራዊ ጥንካሬዎች ይሞገሳሉ፤ ህጸጾች አንድ በአንድ ተነቅሰው እየወጡ ይተቻሉ፡፡ ፈሪና ሰነፍ በሚደረደሩት ግጥሞች የሰላ ትችት ይደርስባቸዋል፡፡ ልጃገረዶቹ ወደፊት ሰነፍ ባል እንዳያገቡ ወይም እንዳይመርጡ ማስጠንቀቂያ በሚሆን መልኩ እንደሚከተለው ይወርፉታል፡፡

| <u>አውራጅ</u> | <u>ተቀባይ</u> |
| --- | --- |
| *እሽም እምቧ እሽም እምቧ* | |
| *ነይ ዞማ አለም አለም* | *እሽም እምቧ እሽም እምቧ ነይ ዞማ አለም አለም* |
| *ዞማ አለም ዞማ አለም (2)* | *እሽም እምቧ እሽም እምቧ ነይ ዞማ አለም አለም* |
| *ነብር እገላለሁ የሚለው ባልሽ* | *እሽም እምቧ እሽም እምቧ ነይ ዞማ አለም አለም* |
| *አንበሳ እገላለሁ የሚለው ባለሽ* | *እሽም እምቧ እሽም እምቧ ነይ ዞማ አለም አለም* |
| *ዝሆን እገላለሁ የሚለው ባልሽ* | *እሽም እምቧ እሽም እምቧ ነይ ዞማ አለም አለም* |
| *አይጥ ሲያንኮሻኩሽ ገደል ገባልሽ* | *እሽም እምቧ እሽም እምቧ ነይ ዞማ አለም አለም* |
| *ለፈሪው ባልሽ ስጭው በሽሮ ፣* | |
| *ያን እየበላ እሽ ይበል ዶሮ፤* | |

እያሉ የትችት ናዳ ያወርዱበታል፡፡ ሴቷም ብትሆን የማትፈትልና የማትሰፋ በአጠቃላይ በሙያዋ ደካማ ከሆነች ትችቱ አይቀርላትም፡፡ ውበትና ቁንጅና ብቻውን በቂ እንዳልሆነ፣ ባለሙያነት ምን ያህል እንደሚያኮራና እንደሚያስከብር በስንኞቹ ትምህርት ይሰጣሉ፡፡

በ "እሽም እምቧ" ጨዋታ ሰነፍ ሴት እንዴት እንደተተቸች የሚገልጹትን ስንኞች ቀጥለን እንመልከት፡፡

| <u>አውራጅ</u> | <u>ተቀባይ</u> |
| --- | --- |
| *እሽም እምቧ እሽም እምቧ* | |
| *ይ ዞማ አለም አለም* | *እሽም እምቧ እሽም እምቧ ነይ ዞማ አለም አለም* |
| *የዞማን ተራራ የሚያህለው ቂጥሽ* | *እሽም እምቧ እሽም እምቧ ነይ ዞማ አለም አለም* |
| *የታል የፈተልሽው ድርና ማግሽ* | *እሽም እምቧ እሽም እምቧ ነይ ዞማ አለም አለም* |
| *ጣቷ ረጃጅም ነው ቂጣ ለመጋገር* | *እሽም እምቧ እሽም እምቧ ነይ ዞማ አለም አለም* |
| *እንዝርት አታሳዩአት ትጠፋለች ካገር* | *እሽም እምቧ እሽም እምቧ ነይ ዞማ አለም አለም* |

እያሉ በዚህ አይነት ሁኔታ ጨዋታውን ይከውናሉ፡፡ በጨዋታው ስንፍናና ፍርሃት ይወገዛል፤ ጀግንነት፣ ባለሙያነትና ጥንካሬ ይሞገሳል/ ይበረታታል፡፡ በማህበረሰቡ የማይደገፉ ችግሮች ሁሉ በአደባባይ ይነቀፋሉ፡፡

ነቀፌታውና ሙገሳው በጓደኞቻቸው ብቻ ተወስኖ የሚቀር አይደለም፡፡ ዙሪያውን ከብበው ከሚመለከቱትና ጨዋታውን ከሚያደምቁት ወጣት ወንዶች መካከል መልከ ጥፉ ከሆነ፣ የእጅ አመል ካለበት ወይም አውደልዳይ ሴት አውል ከሆነ ትችቱ አይቀርለትም፡፡ ጨዋታው ልጃገረዶቹ ስሜታቸውን በነጻነት እንዲገልጡ እድል ስለሚሰጣቸው ስም ጠርተው ሊተቹም ይችላሉ፡፡ በዚህ ትችት ቂም ይዞ፣ ስሜ ተጠራ ብሎ ለጠብ የሚጋበዝ ወይም የሚነሳሳ አይኖርም፡፡ ይልቅ ድክመቱን ለማስወገድና ለሙገሳ የሚያበቃ ተግባር ለመፈጸም ይገፋፋል፡፡

ይህን ጨዋታ ወንዶች የሚጫወቱት ቢሆንም አንድ ሳምንት በሚቆየው የጨዋታ ጊዜ ምልከታ በተደረገባቸው በሁሉም ቀበሌዎች ልጃገረዶቹ በስፋት ሲጫወቱ ተመልክተናል፡፡

ምስል 14፡- ልጃገረዶቹ እሽም እምቧ ሲጫወቱ የሚያሳይ ምስል



(በአጥኚው የእጅ ስልክ የተነሳ፣ አፈዘዝ ቀበሌ ሚያዝያ 2015 ዓ.ም)

#### 5.4.1.6 ሰላም ሰላሙ

ሌላው የፋሲካ ጨዋታ ዓይነት ሰላም ሰላሙ/ሜ የሚባለው ነው፡፡ ይህ ጨዋታ በልጃገረዶቹ በቡድን የሚከወን ጨዋታ ነው፡፡ ለመሾላለክ እንዲመች ተጫዋቾቹ በእድሜና በቁመት ተመጣጣኝ መሆን አለባቸው፡፡ በዚህ ጨዋታ ጥንድ ጥንድ በመሆን ቡድን ይመሰርታሉ፡፡ ከዚያም እጆቻቸውን በማያያዝ/በማቆላለፍ/ የማሳለፊያ ክፍተት ይፈጥራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ሌሎቹ በእጆቻቸው ስር ያልፋሉ፡፡ ሾልኮ ያለፈው በተራው አሾላኪ/አሳላፊ/ ይሆናል፡፡ በዚህ ሁኔታ አውራጅና ተቀባይ በመሆን አንዱ ቡድን በሌሎቹ በተያያዙ እጆች ስር በመፈራረቅ በማለፍ ጨዋታውን ይከውናሉ፡፡

| *አውራጅ* | *ተቀባይ* |
|---|---|
| *ሰላም ሰላሙ* | *ሆ! ሆ!* |
| *ሰላም ሰላሙ* | *ሆ! ሆ!* |
| *ኩኩ መለኮቴ* | *እኔስ ገባሁ ከቤቴ* |
| *እያያ ጤፍ አረም ውዬ* | *እኔስ ገባሁ ከቤቴ* |
| *ኩኩ መለኮቴ* | *እኔስ ገባሁ ከቤቴ* |
| *እያያ ጤፍ አረም ውዬ* | *እንቁጧጧሽ ነው ብዬ* |

የሁለቱ ከዋኞች የተቆላለፉ እጆች ለሌሎቹ እንደ ቤት ያገለግላሉ፡፡ አሾላኪ የነበረው በተራው ሾላኪ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ሰላም ሰላሙ ጨዋታ ከዋኞቹ እየተቀያየሩ አንዱ በአንዱ ቤት በመግባት/በመሹለክ/ የሚከወን ጨዋታ ነው፡፡

ምስል 15፡- ሰላም ሰላሙ ሲጫወቱ የሚያሳይ ምስል



(በአጥኝው የእጅ ስልክ የተነሳ፣ ዓለም ከተማ/ ቁራ ሚያዝያ 2015 ዓ.ም)

በአጠቃላይ ይህ ጨዋታ አንዱ ቡድን በአንዱ በየተራ እየሾለኩ ወይም አንዱ ቡድን በተያያዘው በሌላው ቡድን እጆች በማለፍና ሌላውም ያንኑ ድርጊት በተራው በመከወን የሚጫወቱት ጨዋታ ነው፡፡ ጨዋታው ብዙ የራሱ የሆነ የሚቀባበሉት ቃል ግጥሞች አሉት፡፡

### 5.4.2 የውድድራዊ ጨዋታዎች ዓይነትና ክዋኔ

ውድድራዊ ጨዋታዎች በቡድን በቡድን በመሆን አሸናፊና ተሸናፊ የሚለይባቸው የጨዋታ አይነቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ጨዋታዎች በመንተትና በመዝለል ድርጊቶች የሚገለጹ ሲሆኑ ጨዋታውን ለማጀብ ዜማ ወይም ግጥም አያስፈልጋቸውም፡፡ ቀጥሎ የእያንዳንዱ ውድድራዊ ጨዋታ ስያሜና ያለው የክወኔ ሂደት ቀርቧል፡፡

#### 5.4.2.1 ዝሎሽ

ከፋሲካ የልጃገረዶች ውድድራዊ ጨዋታዎች መካከል አንዱ ዝሎሽ ነው፡፡ ከስያሜው መረዳት እንደሚቻለው የዝሎሽ ጨዋታ ወደ ላይ መዝለልን የሚጠይቅ የጨዋታ አይነት ነው፡፡ ዝሎሽ በሶስት አይነት መንገድ ይከወናል፡፡ አንዱ የገመድ ዝሎሽ፣ ሁለተኛው የነጠላ ዝሎሽ ሲሆን ሶስተኛው ደግሞ የጥንድ ዝሎሽ ነው፡፡ ሁሉም የዝሎሽ አይነቶች በቡድን የሚከወኑ ሲሆኑ ልጃገረዶች ብቻ የሚሳተፉባቸው ውድድራዊ የጨዋታ ዓይነቶች ናቸው፡፡

አንደኛው የዝሎሽ አይነት የገመድ ዝሎሽ ጨዋታ ነው፡፡ የገመድ ዝሎሽ ሁለት ልጃገረዶች የገመድ ጫፍና ጫፍ በመያዝና በማወዛወዝ ሌሎቹ በነጠላ፣ በጥንድ ወይም ለሶስት በመሆን የገመዱን የውዝዋዜ ፍጥነት፣ አቅጣጫና ምት ጠብቀው እየዘለሉ የሚጫወቱት የጨዋታ ዓይነት ነው፡፡ በጨዋታው ላይ የፎረሸ ተጫዋች ተረኛ ገመድ አወዛዋዥ በመሆን ሌሎቹ እንዲዘሉ አጫዋች ይሆናል፡፡

ምስል 16፡- የገመድ ዝላይ ሲጫወቱ



(በአጥኚው የእጅ ስልክ የተነሳ፣ ግሬት ቀበሌ ሚያዝያ 2015 ዓ.ም)

ሁለተኛው የዝሎሽ ዓይነት ደግሞ ያጎነበሰች ጓደኛቸውን (አጎንብሽ) በየተራ በመዝለል የሚከወን  የጨዋታ አይነት ነው፡፡ አጎንባሿ በእጣ፣ በቁጥር፣ በእርጥብ በደረቅ ምርጫ ወይም በፈቃደኝነት ከተመረጠች በኋላ እግሯን በእጇቿ በመያዝ ስታጎነብስ ሌሎቹ በየተራ እንዲዘሉ የሚደረግበት ጨዋታ ነው፡፡ የጨዋታውን አስጀማሪ አጎንባሽ ለመምረጥ ሌላው አማራጭ ጨዋታው ከመጀመሩ በፊት ሁሉም “ባላጎነብስ” ሲሉ ፈዘዝ ያለችው ወይም ዘግይታ ‘ባላጎነብስ’ ያለችውን ጀማሪ አጎንባሽ  በማድረግ ሊጀምር ይችላል፡፡

በዝሎሽ ጨዋታ የሚሳተፉት በእድሜና በአካላዊ ሁኔታ/ጥንካሬ/ ተመጣጣኝ የሆኑ በቁጥር ከስድስት እስከ አስር ልጃገረዶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ዘላዮቹ በአንድ ረድፍ በመሰለፍ ተራ በተራ አጎንባሿን እየዘለሉ ያልፋሉ፡፡ ሁሉም ዘለው ከጨረሱ በኋላ በተመሳሳይ ሁኔታ ተራቸውን እየጠበቁ ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ ይዘላሉ፡

የአጎንባሿ ከፍታ እንደ ዘላዮቹ ብቃት እየታየ የሚጨምር ሲሆን ከፍታው ከቁርጭምጭሚት፣ ጉልበትና ዳሌ ከፍ እያለ እስከ መቆም ድረስ (ራስን ብቻ ጎንበስ እስከማድረግ ድረስ) ይጨምራል፡፡ ዘላዮቹም እንደየከፍታው በመዝለል ብቃታቸውን ያሳያሉ፡፡ ዘላዮቹ ለመዝለል እንዲመቻቸውና አቧራ ወደ ሰውነታቸው እንዳይገባ ቀሚሳቸውን ይጎንፋሉ፡፡ ከዘላዮቹ አንዷ መዝለል ካቃታት/ከነካች/ ተረኛ አጎንባሽ በመሆን እየተፈራረቁ ይጫወታሉ፡፡

ምስል 17፡- በአንድ አጎንባሽ ዝሎሽ ሲጫወቱ



(በአጥኝው የእጅ ስልክ የተነሳ፣ በርቃቶ ቀበሌ ሚያዝያ 2015 ዓ.ም)

ሶስተኛው ዓይነት የዝሎሽ ጨዋታ የጥንድ ዝሎሽ ነው፡፡ ይህ ጨዋታ በሁለት ልጃገረዶች አጫዋችነት የሚከወን ጨዋታ ሲሆን፣ ሁለቱ ልጆች እጆቻቸውን  በተቃራኒ ጓደኛቸው ትከሻ ላይ በመጫንና ፊት ለፊት ጭንቅላቶቻቸውን አገናኝተው በመቆም ሌሎቹ ከፍታዉን

ጠብቀው እንዲዘሉ የሚደረግበት የጨዋታ ዓይነት ነው። በዚህ ጨዋታ ዘላዮቹና ተዘላዮቹ በአቅምና በእድሜ ተመጣጣኝ/ተቀራራቢ/ ሊሆኑ ይገባል። ያለበለዚያ ዘለዮቹ በሌሎቹ ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ።

ምስል 18፡- ልጃገረዶች የጥንድ ዝሎሽ ሲጫወቱ



(በአጥኝው የእጅ ስልክ የተነሳ፣ ግሬት ቀበሌ ሚያዝያ 2015 ዓ.ም)

የዝሎሽ ጨዋታ ግጥም አይፈልግም ወይም በዜማ አይታጀብም። ጨዋታው የህብረት ቢሆንም መያያዝንም አይፈልግም። አጎንበሿ ከተረከዟ ጀምራ ቁርጭሚጭሚቷን፣ ጉልበቷን፣ ዳሌዋን እያለች ቀጥ ብላ እስክትቆም ድረስ ዘላዮች ከፍታውን ተከትለው የሚዘሉበት የጨዋታ ዓይነት ነው።

በዝሎሽ ጨዋታ ጥሩ ዘላዮች ይደነቃሉ፤ ይጨበጨብላቸዋል። ጨዋታው የአካል ጥንካሬና ብቃትን፣ ፍጥነትና ብልጠትን የሚጠይቅ ነው። ጥሩ ዘላዮች እስካልፎረሹ/እስካልወደቁ/ ወይም መዝለል እስካላቃታቸው ድረስ አጎንባሽ ሳይሆኑ ቀኑን ሙሉ መጫወት ይችላሉ ወይም "አስብይን" ይባሉና በፈቃዳቸው አጎንባሽ ይሆናሉ። የዝሎሽ ጨዋታ መዝለል ያቃተው ዘላይ ወይም ተሸናፊ አጎንባሽ እየሆነ የሚካሄድ እና የዘላዮቹን ውበትና ተክለሰውነት ለመመልከትና ለማድነቅ እድል የሚሰጥ ጨዋታ ነው።

> *በዝሎሽ ጨዋታ ወንዶች ቁጭ ብለው የዘላይዋን ችሎታ፣ የእግሯን ቅርጽ፣ የወገቧን ቅልጥፍና፣ የዳሌዋን ውበት፣ በአጠቃላይ ሁለነገሯን በመገምገም ለሚስት የምትሆነውን ለመምረጥ እድል የሚያገኙበት ጨዋታ ነው። ዝሎሽና ቅርጭፋት ሴቶች ለሚስትነት የሚመረጡባቸው የጨዋታ አይነቶች ናቸው። (ውድነሽ ክብረት ቃለ መጠይቅ፣ አፈዘዝ፣ ሚያዝያ 2015)*

እንደ ሌሎቹ የጨዋታ አይነቶች ሁሉ በዝሎሽ ጨዋታም የጨዋታውን ሜዳ ከብበው የሚታደሙት ተመልካቾች ጥሩ ዘላዮችን ያደንቃሉ፤ ያበረታታሉ። በድምጽ፣ በጭብጨባና

በምልክት ድጋፍ ይሰጣሉ። ወጣት ወንዶች ዘላይ ልጃገረዶችን ከመዝለል ችሎታቸው ባሻገር ውበታቸውን ያደንቃሉ። የዝሎሽ ጨዋታ ወጣቶቹ ልባቸው ያረፈባትንና የወደፊት የትዳር አጋር የምትሆናቸውን ኮረዳ ለመምረጥ እድል የሚፈጥር ጨዋታ ነው።

### 5.4.2.2 ቅርጭፋት/ቅርጥፋት/

ቅርጭፋት/ቅርጥፋት/ በፋሲካ የልጃገረዶች ውድድራዊ ጨዋታዎች ውስጥ የሚካተት ሌላ የጨዋታ አይነት ነው። ይህ ጨዋታ እየዘለሉና ሁለት እግርን ወደላይ እያነሱ መቀመጫን በመምታት የሚከወን ጨዋታ ነው። ተመላካቾች ደግሞ የቆይታ ጊዜአቸውንና የዝላዩን ብዛት በመቁጠር አሸናፊና ተሸናፊዉን ይለያሉ።

ጨዋታውን ወደ ላይ እየዘለሉ መቀመጫን በመምታት አቅም እስከፈቀደ ድረስ ተመሳሳይ ሂደት በመከተል ብዙ በማስቆጠር ጥንካሬ፣ ብቃትና ብልጠት የሚመዘንበት የጨዋታ ዓይነት ነው። የዘላይዋን ፍጥነትና ንቃት ይጠይቃል። የቅርጭፋት ጨዋታ "ይሄን ያህል እመታለሁ፤ አትመችም" የሚል ወርርድ አለው። ያለውን ያልመታ በጨዋታ ይቀጣል፤ የመታና በቃሉ የተገኘ ደግሞ አድናቆት ያገኛል። ይህ ሁኔታ ለጨዋታው ልዩ ድምቀት ይሰጠዋል።

> *ጨዋታው የሰውነት ሚዛንን በመጠበቅ ወደ ላይ እየዘለሉ መቀመጫን/ዳሌን በሁለት እግር እየመቱ መመለስን ይጠይቃል። በጨዋታው አንዷ 50 ብትመታ ሌላኛዋ 80 ልትመታ ትችላለች። የውድድር መንፈስ ስላለው ብዙ ያስቆጠረ ዘላይ በታዳሚው ይደነቃል፣ ይበረታታል። ጨዋታው በፍጥነት ከመሬት ወደላይ ዘሎ ዳሌን በሁለት እግር መትቶ መመለስን ስለሚጠይቅ የአካል ብቃትን/ጥንካሬን፣ ሚዛን መጠበቅን፣ ፍጥነትንና ትንፋሽን ይጠይቃል። (ሽቶ አበበ፣ቃለ መጠይቅ፣ግሬት፣ ሚያዝያ 2015)*

በተጨማሪም ጨዋታው የእግርና የወገብ ቅርጽን፣ ሽንጥና ዳሌን ለማድነቅ እድል ይሰጣል። የቅርጭፋት ጨዋታ የዘላይዋ የእግር ቅርጽ፣ የዳሌና የወገብ ውበት እና አካላዊ ጥንካሬ በወንዶች የሚገመገምበት ነው። በአጠቃላይ የዘላይዋን ተክለሰውነትና ውበት ለመመልከት እድል ስለሚሰጥ ሚስት ለሚመርጡ ወጣት ወንዶች መልካም አጋጣሚን ይፈጥራል።

ምስል 19፡- የቅርጭፋት ጨዋታን የሚያሳይ ፎቶ



(በአጥኚው የእጅ ስልክ የተነሳ፣ በርቃቶ ቀበሌ ሚያዝያ 2015 ዓ.ም)

በጨዋታው ብዙ ያስቆጠረች/የመታች/ አድናቆትና ድጋፍ ይሰጣታል፡፡ ተመልካቹ "አይዞሽ በርች" በማለት ያበረታታል፤ ያደንቃል፡፡ ብዙ ቁጥር የመታች ይጨበጨብላታል፡፡ ጥቂት መትታ የደከመች ከሆነ ደግሞ ሽሙጥና ልግጫ ይቀርብባታል፡፡ በተለይም ጨዋታው የወገብ ጥንካሬን የሚፈትን በመሆን ጥቂት ብቻ የመታች እንደ "ሰነፍ" ትቆጠራለች፡፡

ቅርጭፋት በጥንድ ወይም በነጠላ የሚከወን የጨዋታ አይነት ሲሆን አልፎ አልፎ ጨዋታውን ለማድመቅ/ለመታደም/ የመጡ ሴቶች ይጫወቱታል፡፡ የፋሲካ ጨዋታ ሁሉም የሚደሰትበትና የሚጫወትበት በመሆኑ ወደ ጨዋታው ቦታ የመጣ ሁሉ ከልጃገረዶቹ ጋር ወይም ብቻውን የመጫወት እድል አለው፡፡ በአጠቃላይ ቅርጭፋትና ዝሎሽ ወንዶች ሴቶችን ለሚስትነት ለመምረጥና ውበታቸውን ለማድነቅ የሚያስችሉ የጨዋታ አይነቶች ናቸው፡፡

### 5.4.2.3 እባብ ወጣዬ እባብ ወረደይ

በዚህ ጨዋታ ክዋኔው ከመጀመሩ በፊት ከተሳታፊዎቹ መካከል በቡድን መሪነት ወይም በአለቅነት የሚመሩ ሁለት ጠንካራ ልጃገረዶች "እናትያ" በመባል ተሰይመው ይቆማሉ፡፡ ከዚያ ሌሎቹ ተሳታፊዎች በቁመታቸው ልክ እግራቸውን እየከፈቱ ከረጅም ወደ አጭር ተደርድረው ይቀመጣሉ፡፡ ይህም አንዷ እግሯን ከፍታ ስትቀመጥ ቀጣይዋ ለሌላኛዋ ተቀማጭ እንዲመች እግሯን በመክፈት በመጀመሪያዋ ልጃገረድ እግሮች መሃል

ትቀመጣለች፡፡ በዚህ ሁኔታ ለጨዋታ የመጡት በሙሉ በመደርደር ለቀጣዩ የጨዋታ ሂደት /ክዋኔ/ ይዘጋጃሉ፡፡

ጨዋታው የሚጀምረው አንዷ አጫዋች ትነሳና እያነከሰች የተቀመጡትን ዙሪያቸውን እየዞረች የተጠቀለለ ጨርቅ ወይም ኳስ ይዛ “አባብ ወጣዬ” ስትል ተደርድረው የተቀመጡት “አልወጣዬ” ይላሉ፡፡ ስትመለስ ደግሞ “እባብ ወረደይ” ስትል እነሱ “አልወረደይ” በማለት በምልልስ ጨዋታውን ይጀምራሉ፡፡ በመቀጠል አጫዋቿ ድንገት ሳያዩ በአንዷ አጠገብ የያዘችውን ኳስ ቢጤ አስቀምጣ ትሄዳለች፡፡ ቶሎ ያዩ ኳሷን አንስቶ አጫዋቿን ይመታል፡፡ በኳሷ ወርውሮ ያስነካ አጫዋች ይሆናል፡፡ የዚህ ጨዋታ የመጀመሪያ ክፍል በተወሰነ መልኩ አብዛኛው ልጅ ተጫውቶት ካለፈው ከ “መሀረቤን ያያችሁ” ጨዋታ ጋር ይመሳሰላል፡፡

በመቀጠል አንዷ እናትያ የእቃ/የቁስ/ ስም እየጠራች እንዲሰጧት ትጠይቃለች፡፡ የምትጠይቀው በአካባቢው የሚገኝ ማንኛውም ነገር ሊሆን ይችላል፡፡ እነሱም በአጠገባቸው ያገኙትን ኩበት፣ እንጨት፣ ድንጋይ፣ ወዘተ ይሰጧታል፡፡ ተቀብላ የሰበሰበችውን በመረጠችው ቦታ ላይ ታስቀምጣለች፡፡

ከተቀመጡት መካከል አንዷን አስነስታ ወደ ሁለተኛዋ እናትያ “ቅቤ ትቀባሽ”፣ “ምሳሽን ታብላሽ”፣ ወዘተ እያለች ትልካታለች፡፡ መልዕክተኛዋም ለሁለተኛዋ እናትያ የተባለችውን ትነግራለች፡፡ እንዲህ እየተላላኩ ከቆዩ በኋላ ሁለቱ እናትያዎች “እርጥብ” ወይም “ደረቅ” የሚል ምርጫ ይሰጣቸውና የየራቸውን ይመርጣሉ፡፡ ለምሳሌ፡- እርጥብና ደረቅ የሚል ምርጫ ቢቀርብ አንዷ እርጥብ ሌላዋ ደረቅ ሊመርጡ ይችላሉ፡፡ በዚህ መሰረት በመረጡት አቅጣጫ ይመደባሉ፡፡

የቡድን አባላቱ ደግሞ በተቀመጡበት ብብታቸውን በመኮርኮር “የሳቀ” እና “ያልሳቀ” በሚል በሁለት ቡድን ይከፈላሉ፡፡ የሳቀ በአንድ ቡድን ያልሳቀ በሌላ ቡድን ይሆናሉ፡፡

> *አንደኛዋ እናትያ ተደርድረው የሚጠብቁትን ከአንዱ ጫፍ በመጀመር ብብታቸውን በመኮርኮር “የሳቀና ያልሳቀ” በሚል የሳቁት በአንድ በኩል ያልሳቁት በሌላ በኩል ይሆናሉ፡፡ ከዚያ በሁለቱ ቡድን መካከል መስመር ይሰመርና ለመያዝ የሚመች ዱላ/በትር በመካከላቸው ይቀመጣል፡፡ ሁለቱ እናትያዎች ሸብረክ በማለትና መሬቱን በእግራቸው በመቆንጠጥ በሰልፍ በመቆም የዱላውን ጫፍና ጫፍ በሁለት እጃቸው ሲይዙ የቡድን አባላቱ ደግሞ የቡድን መሪዎቻቸውን ወገብ በመያዝ በገመድ ጉተታ ጨዋታ አይነት ይሰለፋሉ፡፡ (ፋኖስ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሰባጌ ቀበሌ፣ ሚያዝያ 2015)*

በመቀጠል  በሁለቱ ቡድኖች መካከል መስመር በማስመር ለመያዝ የሚመች ጠንካራ ዱላ ይቀመጣል፡፡ የተመረጡት አለቆችና የተቀመጡት የሁለቱም ቡድን አባላት በመነሳት በየቡድናቸው ወገብ ለወገብ ተያይዘው ይቆማሉ፡፡ በተመረጡት ሴቶች መሪነት ሁለቱም ቡድን የዱላዉን ጫፍና ጫፍ በመያዝ በገመድ ጉተታ ስፖርት ስልት ለመንተት ይዘጋጃሉ፡፡ በመጨረሻም አስጀማሪ ዳኛ ሲያዛቸው የተሰመረውን መስመር ለማሳለፍና አንዱ ሌላኛውን ቡድን ለማሸነፍ ይጓተታሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ የተሻለ አቅም ያለውና ጎትቶ መስመሩን ያሳለፈ ቡድን የጨዋታው አሸናፊ ይሆናል፡፡

በዚህ  ጨዋታ አሸናፊ ለመሆን ጥንካሬ፣ ብቃትና ስልት ይጠይቃል፡፡ በጨዋታዉ ዙሪያ ያሉ ታዳሚዎች የተሻለ ብቃት ያሳየውን ቡድን በድምጽና በጭብጨባ ድጋፋቸውን ያሳያሉ፡፡ በመጨረሻም አሸናፊው ቡድን በታዳሚው ሞቅ ያለ ድጋፍና አድናቆት ያገኛል፡፡

### *5.4.2.4 ቅጥልጥሎሽ*

ቅጥልጥሎሽ ከ3-6 የሚደርሱ ልጃገረዶች የሚከውኑት የቡድን ጨዋታ ነው፡፡ ከመካከላቸው አንደኛዋ የዛፍ ግንድ ወይም ለመያዝ/ለመደገፍ/ በሚመች ነገር ላይ ተደግፍ/ይዛ/ ትቆማለች፡፡ ሌሎቹ ተጫዋቾች የእሷን ወገብ በመያዝና እርስ በእርስ በመያያዝ ቅጥልጥሎሽ ይሰራሉ፡፡ ጨዋታው ስያሜውን ያገኘውም ከክዋኔው ሂደት ወይም ተጫዋቾቹ ከሚፈጥሩት ቅርጽ ነው፡፡

ምስል 23፡- ልጃገረዶች ቅጥልጥሎሽ ሲጫወቱ የሚያሳይ ፎቶ




(በአጥኝው የእጅ ስልክ የተነሳ፣ ግሬት ቀበሌ ሚያዝያ 2015 ዓ.ም)

የቅጥልጥሎሽ ጨዋታ ከፊሉ አጎንባሽ ከፊሉ ዘላይ በመሆን የሚከወን ጨዋታ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- አምስቱ ተያይዘው አጎንባሽ ቢሆኑ አምስቱ ደግሞ በአጎነበሱት ላይ ዘለው ይወጣሉ፡፡ አነዷ ዘልላ ከፊተኛዋ አጎንባሽ ላይ ፊጥ ስትል ሌሎቹ በየተራ እየዘላሉ

እንዳይወድቁ ተጠንቅቀው በአጎንባሾቹ ጀርባ ላይ ይደረደራሉ፡፡ ዘለው ለወጡት ቁጥር ይያዝላቸዋል፡፡ እስከ ሰባት ወይም እስከ አስር እስከሚቆጠር ድረስ ሳይወድቁ የቆዩ በዘላይነታቸው ይቀጥላሉ፡፡ በጨዋታው ከዘላዮቹ አንዷ ልብሷ ወይም እግሯ መሬት ከነካ ወይም ከወደቀች ተረኛ አጎንባሽ በመሆን እየተፈራረቁ የሚከወን የጨዋታ ዓይነት ነው፡፡ በቅጥልጥሎሽ ጨዋታ የዘላዮቹና የተሸካሚዎቹ ጥንካሬና ብልጠት የሚለካበት የጨዋታ አይነት ነው፡፡ በዚህ የክዋኔ ሂደት ቅጥልጥሎሽ የሚባለውን ጨዋታ ይጠናቀቃል፡፡

### 5.5 ጨዋታው ለማህበረሰቡ ያለው ፋይዳ

ባህል ለማህበረሰቡ ከሚሰጠው ጥቅም አኳያ ታይቶ መዳኘት እንዳለበትና ማንኛውም የፎክሎር ዘርፍ በህይወት የሚኖረው የሚያበረክተው አስተዋፅኦ እስካለው ድረስ ብቻ እንደሆነ Sims & Stephens (2005፤174) ያስረዳሉ፡፡ ስለሆነም የትኛውም የፎክሎር ዘርፍ የተወሰኑ ማህበራዊ፣ ባህላዊ ወይም ስነልቦናዊ ፍላጎቶችን የሚያሟላ መሆን እንደአለበት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ጨዋታ የማስተማር ወይም ልምድ የማቅሰም፣ የማከም፣ መረጃ የማቀበል፣ የመጠበቅእና አካልን የማበርታት አምስት ተግባራት እንዳሉት Schechner (2002) ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም ማህበራዊ ኑሮን ለማጠናከር፣ ፍቅርና መተባበርን ለማዳበር፣ ከአድካሚ ሥራ ተላቆ አንፃራዊ እረፍት ለማግኘት እንደሚከወን ካሕሳይ (2010፣ 209) ይገልፃሉ፡፡ በመርሐ ቤቴ የሚከወነው የልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታም ለማህበረሰቡ የሚያበረክተው የተለያዩ ፋይዳዎች አሉት፡፡ ጨዋታው ራስን ለማዝናናት፣ ለአካል ጥንካሬ፣ ማህበራዊ መስተጋብርን ለማጠናከር፣ ለስነ ልቡና ጥንካሬ፣ ለግለሰባዊ ጠባይ እድገት ፋይዳ እንዳለው ጥናቱ አሳይቷል፡፡

እንደ Schechner (2002፤ 101) ይህ የማህበራዊ ዓለም ልምድ በነባራዊው ዓለም በሚገኝ ተመክሮና ትምህርት የሚቀሰም ነው፡፡ ይህንን ማህበራዊ ዓለም ከሚለማመዱባቸው ልምድ መቅሰሚያ አጋጣሚዎች አንዱ ጨዋታ ነው፡፡ በዚህ ባህላዊ ጨዋታ ከተለያየ ሰፈሮች/ንዑስ ቀበሌዎች/ የመጡ ወጣቶች የሚገናኙበት፣ የሚተዋወቁበትና ስለጋራ ጉዳዮቻቸው የሚነጋገሩበት መድረክ ነው፡፡ የትንሳኤ በዓልና የፋሲካ ጨዋታ በባህሪው ቤተሰብ የሚጠያየቅበት፤ ፍቅር የሚመሰረትበት፣ ተራርቀው የቆዩ ወዳጅ ዘመዶች የሚገናኙበት አጋጣሚ ነው፡፡

ከፋሲካ ጨዋታ ጥቅሞች መካከል አንዱ በወጣቶቹ/በከዋኞቹ/ መካከል ማህበራዊ መስተጋብር እንዲፈጠርና እንዲጠናከር እና ፍቅርና ሰላም እንዲሰፍን ማድረግ ነው፡፡ በመርሐ ቤቴ ወረዳ የሚከወነው የልጃገረዶች ጨዋታ በግለሰቦችና በቡድኖች መካከል ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ከተለያዩ ንዑሳን ቀበሌዎች የመጡ ልጃገረዶች እርስ በእርስ ይተዋወቃሉ፤ ይግባባሉ፤ ይጠያየቃሉ፡፡ ስለወደፊት ህይወታቸው ይመካከራሉ፤ ልምድ ይለዋወጣሉ፡፡ አጋጣሚው በሰዎች መካከል እርቅና ሰላም እንዲሰፍን ያደርጋል፡፡ ጨዋታው ያለውን ማህበራዊ ፋይዳ በተመለከተ (ጸሃይ ባዩ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ዓለም ከተማ፣ ሚያዝያ 2015) እንዲህ ያስረዳሉ፡፡

> *ጨዋታው አንድነትን ያጠናክራል፡፡ ትውውቅን ይፈጥራል፡፡ በበዓሉ ምክንያት የማይተዋወቁ ሰዎች ይገናኛሉ፤ ይተዋወቃሉ፤ ይጠያያቃሉ፡፡ ሌላው የአባት የአያቶቻችንን ባህል እንዲያውቁና ወደ ፊት እንዲቀጥል ያደርጋል፡፡ ወጣት ወንዶች ሚስት ይመርጡበታል/ያገኙበታል፡፡ ከአጎራባች ቀበሌ ሚስት የምትሆነውን ለማየትና ለመመረጥ ይመጣል፡፡ ሴቶች ወጥተው እንዲጫወቱ ቤተሰብ የሚፈቅደው በዚህ በዓል ነው፡፡ አንድ ሳምንት ሙሉ ወንዶች ባሉበት ቦታ እንደልብ የመጫወት ነጻነትና እድል የሚያገኙት ነው፡፡*

ወጣቶቹ በዚህ ጨዋታ ላይ ለመታደም ሲያስቡ ከመምጣታቸው በፊት የሚታረቁ አሉ፡፡ ምክንያቱም በደስታቸው ቀን፣ በክርስቶስ የትንሳኤ በዓል ላይ ቂም ይዘው በጨዋታዉ ላይ መታደም ተገቢ እንዳልሆነ /ሀጥያት እንደሆነ/ ያምናሉ፡፡ "የተጣሉ ወጣቶች ካሉ 'ፋሲካ መጥቷል እንግዲህ ቂም ይዘን እንዴት አብረን መጫወት እንችላለን? ለእኛ ብዙ መስዋዕትነት ተከፍሎልናል፤ ቂም ይዘን መሳተፍ የለብንም' በማለት እርቅ ያወርዳሉ፡፡" (ህይወት ታደሰ፣ ቃለ መጠይቅ ሚያዝያ 2015 ዓ.ም) ፡፡ ስለሆነም ከጨዋታው ፋይዳዎች መካከል በተጫዋቾቹ መካከል ሰላም ማስፈን፣ አንድነትን ማጠናከርና መከባበርን ማጎልበት ነው፡፡ ግለሰብ ወይም ቡድን ሰላም በፈጠረ ቁጥር ደግሞ ትሩፋቱ ለአካባቢና ለሃገርም ስለሚተርፍ የጨዋታው ፋይዳ ከግለሰብና ከቡድን የዘለለ ነው፡፡

ሁለተኛው የልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ ፋይዳ ለትዳር /ለቤተሰብ/ መመስረቻ መልካም አጋጣሚ መፍጠሩ ነው፡፡ ጨዋታው ለትዳር የሚፈላለጉ ወጣቶች የሚገናኙበትና ሚስት የሚፈልጉ ወጣቶችም የምትሆናቸውን የሚመርጡበት ነው፡፡ ስለዚህ የፋሲካ ጨዋታ የቤተሰብ መመስረቻ ለሆነው ትዳር አይነተኛ የመፈላለጊያና የመገናኛ መድረክም ነው፡፡ "እንዲያውም በፋሲካ ጨዋታ ላይ ተያይተው ትዳር የፈጸሙ ሰዎች ትዳራቸው ይጸናል/አይፈርስም/ ይባላል፡፡" (ህይወት፣ ቃለ መጠይቅ፣ሚያዝያ 2015) ፡፡ ስለሆነም ይህ ጨዋታ አንዱ የማህበራዊ ትስስር መፍጠሪያ አጋጣሚ ነው፡፡

የዚህ ጨዋታ ሶስተኛው ፋይዳ ሃይማኖትንና ባህልን ጠብቆ በማስቀጠል በኩል ያለው ትልቅ ጥቅም ነው፡፡ ጨዋታው የክርስትና ሃይማኖትን መነሻ አድርጎ የሚከወን እንደመሆኑ ይሄ መሰረት እንዲቀጥልና ወጣቱን በሥነ ምግባር እንዲታነጽ፣ በባህሉ እንዲኮራና ማንነቱን እንዳይለቅ የላቀ አስተዋጽኦ አለው፡፡ የፋሲካ ጨዋታ በትውልዱ መካከል የባህል ሽግግር እንዲኖር በማድረግ በኩል ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

> *ጨዋታውን ከመንፈሳዊ ጥቅም አኳያ ስናየው ወጣቱ/ትውልዱ መንፈሳዊና ባህላዊ እሴቶችን ይዞ እንዲቀጥል ያደርጋል፡፡ ትውፊቱ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ያደርጋል፡፡ በሌላ በኩል ኢትዮጵያ በህገ ልቡና፣ በህገ ኦሪትና በህገ ወንጌል ያለፈች ሃገር ናት፡፡ ይህ ባህል ደግሞ ህገ ኦሪቱንና ህገ ወንጌሉን በማስተሳሰር ረገድ ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡ (ብርሃኑ ልብሰወርቅ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ዓለም ከተማ፣ ሚያዝያ 2015)*

ስለሆነም የፋሲካ ጨዋታ ወጣቱ በራሱ ባህል እንዲኮራ፣ የሌላ ባህል ሰለባ /ጥገኛ/ እንዳይሆንና በራስ መተማመኑ እንዲጠነክር ያደርጋል፡፡ በአጠቃላይ ትውልዱ በምእራባውያን ትምህርትና አማላይ ቴክኖሎጅ ማንነቱ እየተነጠቀ ባለበት ዘመን እንዲህ ያሉት የማንነት መገለጫ ባህሎች መዳኛ መንገዶች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

ሃገረሰባዊ ጨዋታዎች ከባህላዊ ልማድ ውስጥ እንደ አንድ የሚቆጠሩ ሲሆኑ በልጆች ስነልቡናዊ፣ እውቀትና ስሜት እድገት ግንባታ ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖ እንዳላቸው (Kovačević and Opić 2014) ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም አራተኛው የዚህ ጨዋታ ጥቅም ከወጣቶች ሥነ ልቡና ግንባታ አኳያ ያለውን ፋይዳ ነው፡፡ ትውልዱ ማንነቱን እንዳያጣ/እንዳይለቅ፣ በራስ መተማመኑ እንዲጎለብት ይጠቅማል፡፡ ጨዋታው በተሳታፊዎቹ መካከል ልምድ የመለዋወጥ አጋጣሚ ስለሚፈጥር የሌሎችን ሃሳብ የማዳመጥና የመቀበል ክህሎትና አመዛዝኖ የመወሰን ችሎታ እንዲያዳብሩ ያደርጋቸዋል፡፡ የፋሲካ ጨዋታ ያለተጽዕኖ መተቸትና ማሞገስ እንዲችሉ እድል ስለሚሰጥ ልጃገረዶቹ ሃሳባቸውን በነጻነት የመግለጽና በራስ የመተማመን ብቃታቸው ከፍ እንዲል ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም የቡድኑ አባል በመሆናቸው በቡድኑ ህግ፣ ሥርዓት፣ ደንብ የመገዛትና በዚህ ስርዓት ጥላ ስር ውስጥ የመኖር ሥነሥርዓትን፣ መብትና ግዴታን ማወቅ የሚለማመዱበት መድረክም ስለሆነ በህይወታቸው ህግ የማክበር ስነ ልቡናን እንዲያዳብሩ ያደርጋቸዋል፡፡

አምስተኛው የጨዋታው ፋይዳ ወጣት ሴቶች ስሜታቸውን በነጻነት እንዲገልጹ እድል ይሰጣል፡፡ ከዋኞቹ በአደባባይ የማሞገስና የመተቸት ነጻነት አላቸው፡፡ “ጨዋታው ለሴቶች

ሙሉ ነጻነት የሚሰጥ ነው፡፡ በራስ የመተማማን አቅማቸውንም ያጎለብታል፡፡ ጠንካራ ሰራተኛ ገበሬንና ጀግናን ያሞግሳሉ፤ ሰነፍና ፈሪን በነጻነት እንዲተቹ ጨዋታው እድል ይፈጥርላቸዋል፡፡" (መምህር ዋጋዬ ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዝያ 2015)፡፡ ሴቶች ወጥተው እንዲጫወቱ ቤተሰብ የሚፈቅደው በዚህ በዓል ነው፡፡ አንድ ሳምንት ሙሉ ወንዶች ባሉበት ቦታ እንደልብ የመጫወት ነጻነትና እድል የሚያገኙት በዚህ የጨዋታ ጊዜ ነው፡፡ ለባብሳ፣ አምራና አጊጣ ከስራ ጫና ነጻ ሆና ስምንት ቀን ሙሉ ነጻነት የምታገኘው በፋሲካ ጨዋታ ነው፡፡ በተለይም ይህ ጨዋታ ሴቶች ከጓዳ ወጥተው ራሰቸውን በነጻነት የሚገልጹበት፣ የሚጫወቱበት፣ የሚደሰቱበት፣ ሰው የሚያዩበትና የሚተዋወቁበት በመሆኑ ለልጃገረዶቹ ከፍተኛ ጥቅም አለው፡፡

ከፋሲካ ጨዋታ ጥቅሞች መካከል ስድስተኛው የማስተማር (ልምድ የማቅሰም) እና ለህግ/ሥርዓት ተገዥ እንዲሆኑ የማድረግ ተግባር ነው፡፡ የሰው ልጅ ውስብስብ የሆነ ማህበራዊ ዓለም ይመራል፡፡ ይህንን ማህበራዊ ዓለም ምን እንደሚመስል? እንዴት እንደሚመራ? በማን እንደሚመራ? ልጆችና ወጣቶች ማወቅ እና መማር አለባቸው፡፡ በዚህ ጨዋታ ታዳጊዎችና ወጣቶች ሥነምግባርን፣ ለህግ መገዛትን፣ ብልጠትን፣ የሌላ ሰውን ኃይለ ስሜታዊ ሁኔታ መረዳትን፣ በተለዋዋጭ ሁኔታ ውስጥ መኖርን ይለምዳሉ፡፡ በጨዋታው ሂደት ተራን ጠብቆ አለመጫወት ከጨዋታዉ ሊያስወጣ ይችላል ወይም ቅጣት ሊያስከትል ይችላል፡፡ የጨዋታውን ተለምዶአዊ ህግ አለመጠበቅና የሌሎችን የመጫወት እድል መከልከል በተጫዋቾቹም ይሁን በማህበረሰቡ ዘንድ ተገቢ እንዳልሆነ ስለሚረዱ ተሳታፊዎቹ ለስርዓትና ለህግ ተገዥ ይሆናሉ፡፡ በሌላ በኩል የፋሲካ በዓል ተራርቀው የነበሩ ወዳጅ ዘመዶች የሚሰባሰቡበትና የሚጠያየቁበት በዓል በመሆኑ ወደ አካባቢው የመጡ ወጣቶች ባህላቸውን እንዲያውቁና ልምድ እንዲቀስሙ እድል ይፈጠርላቸዋል፡፡ በጨዋታው ላይ የሚታደሙና የሚሳተፉ ተተኪ ታዳጊዎችና ህጻናት የጨዋታውን የአከዋወን ሥርዓት ከታላላቆቻቸው ይቀስማሉ፤ እንዴት መከወን እንዳለባቸው ተግባራዊ ልምምድ ያደርጋሉ፡፡

የዚህ ጨዋታ ሰባተኛው ፋይዳ በአካል ጥናካሬና ግንባታ እና በማዝናናት ረገድ ያለው ጥቅም ነው፡፡ በ Schechner (2002፤ 101) እንደተገለጸው ጨዋታው ዝላይ፣ ፈንጥዝያ፣ ልፊያ፣ መውደቅ መነሳት፣ ውድድር (ፉክክረ) ስላለበት ለአካል ግንባታና ብርታት የሚኖረው ትልቅ አስተዋጽኦ እና ከውጥረት /ከጭንቀት/ ለማምለጥና ለመዳን ያለው

የማክም ተግባር ነው። በዚህ የፋሲካ ጨዋታ አብዛኛዎቹ የተገለጹት ባህሪት ይንጸባረቃሉ። የፋሲካ ጨዋታ ውድድር/ፉክክር/፣ ጉተታ፣ ዝሎሽ፣ ቡረቃ፣ ልፊያና መውደቅ መነሳት ስላለበት ለወጣቶቹ አካል ጥንካሬና ብርታት ያለው አስተዋጽኦ የላቀ ነው። ወጣቶቹ ከስራ ጫናና ከወጥረት በመላቀቅ የተዝናኖት ጊዜ እንዲኖራቸውም ያደርጋል።

በመጨረሻ  የምንመለከተው ጨዋታው ገበያ ከመፍጠር አንጻር ያለውን ጥቅም ነው። በጨዋታው መከወኛ አካባቢ የተለያዩ ፍራፍሬዎች ይሸጣሉ። ተሳታፊዎቹም እየገዙ ይጠቀማሉ። በቅርብ ያሉ ሱቆች አጋጣሚውን ሲጠቀሙበት ተመልክተናል። ጨዋታውን ይበልጥ በማጠናከር እንዲጠበቅ፣ እንዲተዋወቅና፣ እንዲለማ ማድረግ ከተቻለ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ከፍ ሊል ይችላል። የተቀናጀና ውጤታማ ስራ ከተሰራ ጨዋታው ወደ ፌስቲቫል እንዲያድግ በማድረግ እንደ አሸንዳ/ አሸንድዬ/ሻደይ፣ ፍቼ ጫምባላላ  እና ሌሎች በዓላት የጎብኝ መስህብ በመሆን ገንዘብ ሊያመነጭ /ሊያመጣ/ ይችላል።

## 5.6 በጨዋታው ላይ የሚታዩ ስጋቶች

### 5.6.1 የሚታዩ ስጋቶች

ዓለም አንድ መንደር እየሆነች በመጣችበት በሉላዊነት (Globalization) ዘመን ተገቢ ጥበቃ ካልተደረገና ግንዛቤ መፍጠር ካልተቻለ ሀገር በቀል ባህላዊ እሴቶችን፣ ሥርዓቶችንና ክዋኔዎችን ሊያደበዝዛቸው የሚችል ስጋት መፈጠሩ አይቀርም። የመርሐቤቴ ልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታም እንደማንኛውም ማህበራዊ ክንውን የተለያዩ ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች እንደተጋረጡበት መገንዘብ ይቻላል።

ለጨዋታው መቀጠል እንደስጋት ከተነሱት ችግሮች መካከል በዋነኛነት የተጠቀሱት ዘመናዊነት/ቴክኖሎጅ/፣ የመጫወቻ ቦታ ማጣት፣ ለባህል ዘርፍ ትኩረት አለመስጠትና ግንዛቤ አለመፍጠር፣ ወቅታዊ የጸጥታ ችግር፣ የልጃገረዶች ጠለፋ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ዘመናዊነት በጨዋታው ቀጣይነት ላይ የተጋረጠ አንድ ችግር መሆኑን “አንዱ ችግር ዘመናዊነት ነው። ወጣቶቹ በዘመን አመጣሽ ነገሮች የሚሳቡ ከሆነና ጨዋታውን የሚያስቀጥል ስራ ካልተሰራ ወደፊት በጨዋታው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳርፍ ይችላል።” በማለት መምህር ጸጋዘአብ (ቃለ መጠይቅ ሚያዝያ 2015) ይገልጻሉ። በተለይም አማላይ የማህበራዊ ሚዲያ ዝግጅቶች በየእጅ ስልኮቻቸው በቀላሉ በሚደርሱበት በዚህ ዘመን ወጣቶቹ በተጽእኖ ስር መውደቃቸው አይቀርም። ለምሳሌ፡- ግሬት ቀበሌ

በነበረን ምልከታ ቴፕ (ማጫወቻ) ይዘው መጥተው በዘመናዊ ሙዚቃዎች መጨፈርና ለባህላዊ ክዋኔው ትኩረት አለመስጠት ተመልክተናል። እንዲሁም  አንዳንድ ወጣቶች ከጨዋታው ይልቅ ለእጅ ስልኮቻቸው ብዙ ጊዜ ትኩረት ሲሰጡ ታይቷል።

ሌላው በወረዳው ውስጥና ከወረዳው ውጭ የሚታየውና የሚሰማው የጸጥታ ችግር በጨዋታው ላይ ተጽእኖ እንዳሳረፈ መገንዘብ ይቻላል።

> *አንዱ ስጋት በሃገሪቱ የሚታየው የጸጥታ ሁኔታ ነው። በዚህ ችግር ምክንያት በአንዳንድ ቀበሌዎች ልጃገረዶቹ እንዳይጫወቱ የመከልከልና በማስገደድ በጊዜ እንዲበተኑ የማድረግ ሁኔታዎች ታይተዋል። ምንም የመሳሪያ አጠቃቀም የማያውቁ ወጣቶችና አርሶአደሮች በህጋዊም ይሁን በህገወጥ መንገድ አብዛኛው ባለመሳሪያ ሆኗል። በተለይም በአሁኑ ጊዜ በየቦታው የጥይት ተኩስ አለ። የሚታየውና የሚሰማው መልካም አይደለም። በሶሻል ሚዲያው አማካይነት አሉባልታ የበዛበት ነው። በጨዋታው ለመሳተፍ ስጋት አለ። ይህ ችግር ካልተፈታ ቤተሰብ ልጆቹን ወደ ጨዋታው ለመላክ ይፈራል። ይህም ወደፊት በጨዋታው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊፈጥር ይችላል። (የማሪያምወርቅ፣ ቃለ መጠይቅ ሚያዝያ 2015 ዓ.ም)*

በምልከታም እንዳረጋገጥነው ወቅቱ የፈጠረው የጸጥታ ስጋት በጨዋታው ክዋኔ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል። "በሃገሪቱና በወረዳውም ባለው የጸጥታ ስጋት ቤተሰብ ልጆቹን ለመላክ ይፈራል። በጨዋታው ላይም አንዳንድ ወጣቶች የተለያየ የጦር መሳሪያ ይዘው ስለሚመጡ ቤተሰብ ላይም ሆነ ልጆቹ ላይ ስጋት ፈጥሯል።" (ጉልቻ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዝያ 2015) ። በአንዳንድ ቀበሌዎች ደግሞ የቀበሌ አስተዳዳሪዎችና ታጣቂዎች በጸጥታ ስጋት ምክንያት ጨዋታው ጭራሽ እንዳይከወን ልጃገረዶቹን የበተኑበት ሁኔታ አለ (ለምሳሌ፡- ዘይታ ማጋስ ቀበሌ)። በተወሰኑ ቀበሌዎች ደግሞ ከጨዋታ ማጠናቀቂያ ጊዜ (ሰዓት) ቀድሞ ጨዋታው እንዲቆም ሲያደርጉ (ለምሳሌ፡- ግሬት ቀበሌ) ተመልክተናል።

አንዳንድ ቦታዎች ላይ እንደበፊቱ እንዳይከወን ከማድረግ ባሻገር የጨዋታው ይዘትና የአከዋን ስርዓት እንዲቀየር በማድረግ ማደብዘዝ ጀምሯል። "በአካባቢው ባህል መሰረት ሴት ሆ! አትልም፤ እንደ ነውርም ይቆጠራል። ነገር ግን በወቅቱ ተጽእኖ ምክንያት በአካባቢው ወጣት ሴቶች ዘንድ የመበደልና የመገፋት ስሜት በመፍጠሩ ልጃገረዶቹ ሆ! ይላሉ።" (ህይወት፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዝያ 2015) ።

በምልከታም እንደታዘብነው ‘ታጠቅ፣ ተዋጋ’ የሚሉ ይዘት ያላቸውን ስሜት ቀስቃሽ ግጥሞችን በማውረድ ልጃገረዶቹ ሲጨፍሩ/ሆ! ሲሉ/ ተመልክተናል፡፡ በአካባቢው የተፈጠረው የተበዳይነት ስሜት ልጃገረዶቹ፣

*ገና ነው ገና፣*

*መች ተዋጋና  መች ተዋጋና፣*

*ይታያል ገና፣*

*አትገዛውም ወይ፣  ሆ በል!*

*ብር የለህም ወይ!*

*አዲስ አበባ መውዜር አበራ!*

በማለት ከነበረው የአከዋወን ስርዓት ባፈነገጠና ባልተለመደ ሁኔታ ሴቶች “ሆ!” እንዲሉ እያደረገ  እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ በአንዳንድ ቀበሌዎች ሰፊውን የጨዋታ ሽፋን የሚይዘው የልጃገረዶቹ ሆታ ሆኗል፡፡ ይህ ሁኔታ ልጃገረዶቹ ቀድሞ በፍቅር ሲጫወቷቸው የነበሩ  ብዙ አይነት ጨዋታዎች እንዲተውና እንዲደበዝዙ እያደረገ ይገኛል፡፡

ለጨዋታው መደብዘዝ በስጋትንት ከተነሱት ችግሮች መካከል ሌላው የመጫወቻ ቦታ ማጣትና ትውልዱ በባህሉ እንዲኮራ አለማስገንዘብ ናቸው፡፡ በየዓመቱ ጨዋታው የሚከወንባቸው የወል መሬቶች /ሜዳዎችና መስኮች/ ለሌላ አገልግሎት እንዲውሉ መደረጉ በጨዋታው ቀጣይነት ላይ ስጋት ማሳደሩን (ዋጋዬ ማሞ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ዓለም ከተማ፣ ሚያዝያ 2015) እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> *ልጆቹ በተወሰኑ ቀበሌዎች የመጫወቻ ስፍራ እያጡ ነው፡፡ መንገድ ዘግተው የሚጫወቱበት ሁኔታ እየታየ ነው፡፡ ወደ መኪና መንገድ ለመውጣት እየተገደዱ ነው፡፡ ቀደምት የመጫወቻ ቦታዎች ወደተለያዩ አገልግሎቶች እየተቀየሩ ነው፡፡ ይሄ ደግሞ ወደፊት መጫወጫ ቦታ እንዳያጡ ያሰጋል፡፡ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ክዋኔዎች እናዳይቋረጡና እንዳይደበዝዙ የመከወኛ ቦታዎች ሊታሰብባቸው ይገናባል፡፡ ለምሳሌ፡- ቀድሞ መጫወቻ ቦታ የነበረው “ሽተቴ” እሚባለው መጫወቻ ቦታ ለመኖሪያ ቤት መስሪያ ስለተሰጠ ልጆቹ ወደ መንገድ ወጥተዋል፡፡ ስለዚህ በየአመቱ ጨዋታው የሚካሄድበት የተከለለ ቦታ ሊኖር ይገባል፡፡*

ሌላው ችግር ባህሉን የሚያስተላልፉ፣ የሚመሩና የሚመክሩ ሰዎችና ተቋማት በትኩረት አለመስራት ነው፡፡ ይሄን መልካም እሴት ለትውልድ የሚያሸጋግሩ አባቶችና እናቶች ሃላፊነታቸውን ካልተወጡ እና በባህል ላይ የሚሰሩ ተቋማት ለሃገር በቀል እውቀቶች፣

ለሃይማኖታዊና ባህላዊ እሴቶች ትኩረት ሰጥተው ካልሰሩ በዚህ የፋሲካ ጨዋታ ይዘትና አከዋወን ሂደት ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በዘርፉ ላይ አደጋ መጋረጡ አይቀርም፡፡ ለአብነትም የወረዳው ወጣቶች የራሳቸውን ባህላዊ አለባበስ መተውና በሌላ አካባቢ አለባበስ ተጽእኖ ስር መውደቃቸው አንዱ ችግር ሆኖ ቀርቧል፡፡ ወጣቶቹ የጎረቤት ወረዳዎችን አለባበስ በመኮረጅ የወረዳው ባህላዊ አለባበስ በሚመስል ሁኔታ የእነሱ ያልሆኑ አልባሳትን ያዘወትራሉ፡፡

> *የወረዳችን ህዝብ ባህላዊ አልባሳት ከጥጥ የተሰሩና ያማሩ የሸማ ውጤቶች ሆነው ሳለ ዛሬ ወጣቱ አዝራር የበዛበት የውጭ ሃገር ልብስ አዘውታሪ ሆኗል፡፡ ቀደም ሲል የውጭ ሃገር (ካሽሚር) ቢሆኑም ልሙጥ ነበሩ፡፡ አሁን ግን ባልተለመደ ሁኔታ ቁምጣና ኮቱም ሆነ ቀሚሱ በአዝራርና በጋንች የተተበተበ ነው፡፡ (ህይወት፣ ቃለ መጠይቅ ሚያዝያ 2015)*

በዚህም ወጣቶች ቀስ በቀስ የነበረውን ባህላዊ አለባበስና አጋጊያጥ በመተው በሌላ አካባቢ ባህል ሰለባ/ተገዥ ይሆናሉ፡፡ ይህም ሁኔታ የጨዋታውን ቀደምት ገጽታ ይቀይራል ወይም ያጠፋል፡፡

ሌላው በጨዋታው ድምቀትና ቀጣይነት ላይ በስጋትነት የተነሳው የልጃገረዶች ጠለፋ ነው፡፡ ይህንንም ችግር መምህር ጸጋዘአብ (*ቃለ መጠይቅ ሚያዝያ 2015) ሲያብራሩ* “ሌላው ስጋት በጣም ቀንሶ የነበረው ጠለፋ እንደገና እየተጠናከረ መምጣት ነው፡፡ ልጀገረዶቹ ጠለፋ በመፍራት ወደ ጨዋታዉ ቦታ ለመምጣት ላይደፍሩ ይችላሉ፡፡” በማለት ያረጋግጣሉ፡፡ በአጠቃላይ ክፍ ሲል የተጠቀሱት እና ተያያዥ ምክንያቶች በመርሐ ቤቴ የልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ ክዋኔ ይዘትና ቀጣይነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች እንደሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

## ማጠቃለያና ይሁንታ

ይህ ምዕራፍ ጥናቱ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የተጓዘባቸውን አበይት ሂደቶችና የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች ተጠቃልለው የቀረበቡት እና የይሁንታ ሃሳቦች የተጠቆሙበት ክፍል

ነው፡፡ ስለሆነም ጥናቱ የተመለከታቸው ጉዳዮችና "ቢደረጉ" የተባሉ የይሁንታ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 6.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት የመርሐ ቤቴ ልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ ክዋኔ እና ፋይዳ በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ ለጥናቱ መነሻ ከሆኑኝ ዋና ዋና ምክንያቶች መካከል ከትንሳኤ እስከ ዳግም ትንሳኤ የሚከወነው የመርሐ ቤቴ ልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ እየደረሰበት ካለው የመደብዘዝና የመጥፋት ስጋት ለመታደግ የየጨዋታዎቹን ክዋኔና ፋይዳ ሰንዶ የማቆየት ፍላጎት ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ባደረግሁት የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ በዚህ ርዕስ ጉዳይ የተሰሩ ጥናቶች አነስተኛ ሆነው በማየቴ ይህን ክፍተት ለመሙላት በማሰብ ነው፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማም በመርሐ ቤቴ ወረዳ ለአንድ ሳምንት የሚካሄደውን የልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ ክዋኔ ሂደትና ያለውን  ፋይዳ መመርመር ነው፡፡

የጥናቱን ዓለማ ከግብ ለማድረስ በዋናነት የፋሲካ ጨዋታ ታካዊ አጀማመር መነሻ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው? በፋሲካ ጨዋታ ስንት ዓይነትና ምን ምን አይነት ጨዋታዎች ይከወናሉ? በወረዳው የሚከወነው የፋሲካ ጨዋታ ክዋኔ  ሂደት ምን ይመስላል? የፋሲካ ጨዋታ ለተጠኝው ማህበረሰብ ምን ፋይዳ አለው? በጨዋታዎቹ ክወኔ ቀጣይነትና ይዘት ላይ ምን ዓይነት ስጋቶች ይስተዋላሉ? የሚሉ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ጥያቄዎቹን ለመመለስ በሁለት መንገድ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ አንደኛ ከአብያተ መጻሕፍና ከኤሌክትሮኒክስ የመረጃ መረብ በንባብ ሲሆን ሌላው የመርሐ ቤቴ ወረዳን ይወክላሉ ተብለው ከተመረጡት ከዓለም ከተማ፣ ከአፈዘዝ በርቃቶ፣ ከግሬት ወቸዋርኝ፣ ከአገሪት ቁምአምባ እና ሰባ ሃሮገንዳ ቀበሌዎች በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በተተኳሪ የቡድን ውይይት መረጃ ተሰብስቧል፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎች በአግባቡ ተደራጅተው የተነሱ ጥያቄዎችን ከመመለስ አንጻር በክዋኔያዊ (Performance theory) እና ተግባራዊ ንድፈ (Functional theory) ተተንተነዋል፡፡ ከትንታኔው የተገኙ ውጤቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

የልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ ታሪካዊ ዳራው/መነሻው/ የክርስትና ሃይማኖት መሆኑ፤ ይሄውም ጨዋታው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን "የትንሳኤ በዓል ነው" ብላ ባወጀችበትን እለት በየአመቱ መከወኑ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ (ማቴ 27፡56፣ዮሐ 20፡1-

18) የክርስቶስን መነሳት ቀድመው ያዩትና ደስታዉን ያበሰሩት ሴቶች ከመሆናቸው ጋር በማገናዘብ፣ በጨዋታው ከሚታዩ ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች (መጓተት፣ መገፋፋት፣ መደብደብ) ጋር በማዛመድና አካባቢው ቀድሞ የክርስትና ሃይማኖትን እንደተቀበለ ካለው አፋዊ ታሪክ ጋር በማያያዝ ጨዋታዉ ሃይማኖታዊ መሰረት/መነሻ/ እንዳለው እና ረጅም ዘመን እንዳስቆጠረ  በጥናቱ ታይቷል፡፡

ከትንሳኤ እስከ ዳግም ትንሳኤ ድረስ አንድ ሳምንት በሚቆየው የፋሲካ ጨዋታ አስር ዓይነት ጨዋታዎች ባህሉ የሚፈቅደውን ህግ በመከተል በቡድን  የሚከወኑ መሆናቸው፤ ጨዋታዎቹ በዜማ የሚታጀቡና ውድድራዊ ጠባይ ያላቸው ናቸው፡፡ አጋጋሙዬ/እቶት እቶቴ/፣ ማሬ ዘንባባዬ፣  ሸወይባ፣ ቡፍጨ ገላ፣ አሽም እምቢ/ነይ ዞማ/ እና ሰላም ሰላሙ በዜማ የሚታጀቡት ጨዋታዎች ሲሆኑ፣ ዝሎሽ፣ ቅርጭፋት/ቅርጥፋት/፣ እባብ ወጣዬ እባብ ወረደይ እና ቅጥልጥሎሽ ደግሞ ውድራዊ ባህሪ ያላቸው ጨዋታዎች  እንደሆኑ ሌላው በጥናቱ የታየ ጉዳይ ነው፡፡

የመርሐ ቤቴ ልጃገረዶች የጨዋታው ጊዜ ከመድረሱ ቀደም ብለው በሁለት መንገድ ቅድም ዝግጅት እንደሚያደርጉና ከጫና ነጻ ሆነው በጨዋታው ላይ እንደሚሳተፉ፣ የመጀመሪያው ራሰቸውን በአልባሳትና ጌጣጌጥ አስውበው በጨዋታው  ለመገኘት የሚያደርጉት ቅድመ ዝግጅት ሲሆን ሁለተኛው ከስራ ነጻ ሆነው በጨዋታው ለመታደም የሚድርጉት ቅድመ ዝግጅት ነው፡፡ በጨዋታው በዋናነት የሚሳተፉት ከ13 እስከ 25 ዓመት እድሜ ክልል ያሉ ልጃገረዶች ሲሆኑ ወጣት ወንዶች በመጫወቻ ሜዳው ዙሪያ በመሆን የልጃገረዶቹን ጨዋታ በጭብጨባና በድምጽ ያደምቃሉ፤ የራሳቸውን ጨዋታ ይጫወታሉ፤ ልጃገረዶቹን ከጥቃት ይከላከላሉ፤ ልባቸው ያረፈባትን ቆንጆ ለትዳር አጋርነት ይመርጣሉ፡፡

ጨዋታው ለማህበረሰቡና ለቡድኑ ብዙ ጠቀሜታዎች ያሉት መሆኑ፤ ማህበራዊ መስተጋብርን በማጠናከር፣ ባህልና ሃይማኖትን በማስቀጠል፣ ወጣቶች በባህላቸውና በማንነታቸው እንዲኮሩ በማድረግ፣ አካላዊና ሥነልቡናዊ ጥንካሬአቸውን በማዳበር፣ በራስ መተማመናቸውን በማጎልበትና ሃሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ በማድረግ በኩል ከፍተኛ ማህበራዊ፣ ሥነለቡናዊና አካላዊ ፋይዳ  እንዳለው ጥናቱ አመላክቷል፡፡

ጨዋታው ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎች ፋይዳዎች ቢኖሩትም በውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች ምክንያት ስጋት የተጋረጠበት መሆኑ፤ ከውስጣዊ ችግሮች መካከል የመጫወቻ ቦታ

ማጣት፣ በጸጥታ ችግር ምክንያት ጨዋታውን ለመከወን መቸገር፣ ታላላቆችና የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ባህሉን ለትውልዱ በማስተላለፍ በኩል ዳተኛ መሆን ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ዘመናዊነትና ቴክኖሎጅ ደግሞ በወጫዊ ችግርነት የሚጠቀሱ ስጋቶች እንደሆኑ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ከመደምደሚያው በመነሳት ቀጥለው የቀረቡት ይሁንታዎች ተሰጥተዋል፡፡

## 6.2. ይሁንታ

ባህልን የማስተዋወቅና የመጠበቅ ተግባር በአንድ አካል ትክሻ ላይ ብቻ የሚወድቅ ወይም ለአንድ አካል ብቻ የሚሰጥ ተግባር አይደለም፡፡ የማህበረሰቡ ባህል እንዲተዋወቅ፣ እንዲጠበቅና እና እንዲለማ የሚመለከታቸው አካላት ተገቢ ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡ በየዓመቱ የሚከወነው የመርሐ ቤቴ ልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ የባህል አካል እንደመሆኑ ያንዣበቡበት ስጋቶች እንዲቀንሱና እንዲወገዱ ማህበረሰቡ፣ የመንግስት ተቋማት፣ የሃይማኖትና ሲቪል ተቋማት፣ መገናኛ ብዙሃን የየበኩላቸውን ሚና ሊወጡ ይገባል፡፡

የመርሐ ቤቴ የልጃገረዶች የፋሲካ ጨዋታ በርካታ ክዋኔዎች የሚታዩበት እና ማኅበራዊ የህይወት ልምዶች የሚቀሰሙበት ሃገረሰባዊ ጨዋታ ነው፡፡ ጨዋታው ከሚያስገኘው ማህበራዊም ሆነ ስነ ልቡናዊ ፋይዳ አንፃር እየተደረገለት ያለው ጥበቃና እንክብካቤ አጥጋቢ/በቂ/ ለማለት አይቻልም፡፡ የጥናቱን ውጤቶች መነሻ በማድረግ በሚመለከታቸው አካላት ሊደረጉ ይገባቸዋል የሚባሉ ምክረ ሃሳቦችን እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡

- ❖ ጨዋታው እንዲተዋወቅና እንዲያድግ የሚመለከታቸው አካላት ሚናቸውን መወጣት አለባቸው፡፡ አንደኛውና በዋናነት ኃላፊነት ያለበት ራሱ ማህበረሰቡ ነው፡፡ ማህበረሰቡ ጨዋታው ወደ ቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፍ ማስገንዘብ አለበት፡፡ ትውልዱ በአማላይ የቴክኖሎጅ ውጤቶች ተማርኮ የራሱን ባህል ችላ እንዳይል ማስተማር ያስፈልጋል፡፡ የተማረው የህብረተሰብ ክፍል፣ የሐይማኖት አባቶች፣ የእድሜ ባለጸጋ አባቶችና እናቶች የባህል ሽግግር እንዲኖርና ትውልዱ በየኔነት ስሜት ባህሉን እንዲያስቀጥል ኃላፊነታቸውን ሊወቢወጡ፣
- ❖ እንደ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ያሉ የሚመለከታቸው የመንግስት መዋቅሮች በቂ የተማረ የሰው ሃይልና ፋይናንስ እንዲመደብላቸው በማድረግ ለባህሉ ዘርፍ ትኩረት መስጠት ቢቻል መልካም ይመስለኛል፡፡ ጨዋታው ካሉት ማህበራዊ ፋይዳዎች ባሻገር

እንደ አሸንዳ፣ ሻደይና ጨምባላላ የጎብኝዎች መስህብ በመሆን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዲኖረው ከመገናኛ ብዙኀንና ከሚመለከታቸው የመንግስትና የግል ተቋማት ጋር በጋራ ቢሰራ፤ መገናኛ ብዙሃንም እንደነዚህ ዓይነት ቱባ ባህሎች ላይ በስፋት እንዲሰሩ እድሉን መፍጠር ቢቻልና ማህበራዊ ሚዲያዎችን በመጠቀም የማስተዋወቅ ስራ ቢሰራ፣

- በባህል ላይ የሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ሲቪል ማህበራትና የትምህርት ተቋማት በአጋርነት እንዲሰሩ እድል መፍጠር ቢቻል፣
- ጨዋታው በችግሮች ምክንያት መከወኑ ከተስተጓጎለ ወይም ክልከላ የሚደረግ ከሆነ በቀጣይነቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ አይቀርም፡፡ ስለሆነም ሰላማዊ የጨዋታ ሁኔታ እንዲኖር ጸጥታውን ማስከበር፣ የየቀበሌው አመራሮች ጨዋታው በሰላም እንዲከናወን ግንዛቤ መፍጠር፣ ልጃገረዶቹ ለጥቃት እንዳይጋለጡ መጠበቅ ቢቻል፣
- ልጆቹ መጫወቻ ቦታ ባጡ ቁጥር ጨዋታው በወጣቶቹ ዘንድ ትኩረት እያጣ ሊመጣ ይችላል፡፡ ስለሆነም የመጫወቻ ሜዳዎቹ ይዞታ ቋሚ ማረጋገጫ እንዲኖራቸው በማድረግ ቦታዎች በቋሚነት ለዚህ ተግባር እንዲውሉ ቢደረግ፣
- በጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የተሰራ ጥናት የለም ብሎ መደምደም ባይቻልም ጉዳዩ በሚገባው ደረጃ/ልክ/ አልታየም ለማለት ይቻላል፡፡ ስለሆነም የመስኩ ምሁራን በጨዋታው ላይ ከዚህ ጥናት በበለጠ ሰፊ ጊዜና በጀት መድበው ጥናት ቢያደርጉ፣ ባህልን ትኩረት አድርገው የሚሰሩ በየደረጃው ያሉ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት /ድርጅቶች/ ማህበራዊ መስተጋብር በመፍጠር ለሃገር ትልቅ ፋይዳ ባላቸው እሴቶች ላይ ትኩረት አድርገው ቢሰሩ የሚል ምክረ ሃሳብ አለኝ፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


ሀብታሙ ተሾመ። (2014 ዓ.ም) ። "የጸታዊ ሚና አቀራረጽ ልማድ በልጆች ጨዋታ ውስጥ በሁለት እጁ እነሴ ወረዳ በደብረ ማርያም ቀበሌ ማሳያነት"። ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ።

ለእናት ሆስፒታል ምረቃ የተዘጋጀ "መሬ" መጽሔት (ልዩ እትም) ። 1996 ዓ.ም።

ማኅተመሥላሴ ወልደ መስቀል (ብላቴን ጌታ) ። (1962 ዓ.ም) ። <u>ዝክረ ነገር።</u> አዲስ አበባ፣ አርቲስቲ ክማተሚያ ቤት።

ማዕዛሽወርቅ እርገጥ። (2011 ዓ.ም) ። የመርሐ ቤቴ ሕዝብ በቃል ግጥሙ፡ የሕይወት አረዳዱና ስለ ራሱ ያለው ግንዛቤ በፎክሎር። የዶክትሬት ዲግሪ ለማግኘት በማሟያነት የቀረበ ጥናት፣አዲስ አበባ ዩኒርስቲ።

ምስጋናው ብርሃን። (2012) ። ባህላዊ የልጆች ጨዋታ የማህበራዊ ስነ ልቦናን የመገንባት ፋይዳ በአለፋ ወረዳ ተተኳሪነት። የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ፣ ባህርዳር ዩኒቨርስቲ።

በመርሐቤቴ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት ፕላን ኮ/ል/ዕ/ክ/ግ/ቡድን የልማት አመላካች አመታዊ መጽሄት/ያልታተመ። (2015 ዓ.ም) ።

በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞን የመርሐቤቴ ወረዳ ፕላንና ልማት ስታትስቲካል መጽሄት/ያልታተመ። (2014 ዓ.ም) ።

ብርሃኑ አድማስ (ዲ/ን) ። (2013 ዓ.ም) ። <u>በዓላት ምን? ለምን? እንዴት?</u>። ማኅበረ ቅዱሳን ኅትመት አገልግሎት።

ብርሃን አሰፋ አራጋው። (1997 ዓ.ም) ። "የአሆላሌ ጨዋታ ክዋኔና የግጥሞቹ ይዘት ትንተና"። የአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

ሰላማዊት ጌታሁን። (2015 ዓ.ም)። "የሽውዬእና ምሻምሾ ባህላዊ ጨዋታ ክዋኔ እና ፋይዳ በዝቋላ ወረዳ ማህበረሰብ" ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ።

ሰሎሞን ተሾመ። (2007 ዓ.ም) ። <u>ፎክሎር ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ።</u> አዲስ አበባ፣አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ሰሎሞን ንጋቱ። (2013 ዓ.ም) ። የንሆይ አከዋወንና ስነልቦናዊ ፋይዳ በላይ ጋይንት ወረዳ። ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ፣ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ። (1961ዓ.ም) ። <u>የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ።</u> 4ኛ እትም፣ አዲስአበባ፣ ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ።

ኅሩይ ወልደሥላሴ። (1915 ዓ.ም) ። የሕይወት ታሪክ በኂላ ለሚነሱ ልጆች ማስታወቂያ መስታወት። አዲስ አበባ፣ ልዑል ራስ ተፈሪ ማተሚያ፣

______________ ። (1923)። "የኢትዮጵያ ታሪክ"። አሳታሚው ልተገለጸ።

አለም እሸቱ። (2001) ። የምርምርና የዘገባ አጻጻፍ። አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች ድርጅት።

ኪዳነወልድ ክፍሌ (አለቃ) ። (1948 ዓ.ም) ። መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ። አዲስ አበባ፣አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ካሕሳይ ገብረ እግዚአብሄር። (2010) ። ባህልና ክርስቲያናዊ ትውፊት በኢትዮጵያ። አዲስ አበባ፣በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን ሰ/ት/ቤቶች ማ/መ/ ማኅበረ ቅዱሳን።

ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ። (2011 ዓ.ም) ። ሥነ-ምግባር። በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን ሰ/ት/ቤቶች ማ/መ/ ማኅበረ ቅዱሳን።

ዓለማየሁ አበበ። (2008 ዓ.ም) ። የሸንቁጥ ልጆች፡ የፀረ ፋሺስት ኢጣልያ ተጋድሎ በመርሐ ቤቴና አካባቢው (ከ1928 ዓ.ም -1933 ዓ.ም) ። አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ።

ዘሪሁን አስፋው። (1998 ዓ.ም) ። የስነ ጽሁፍ መሰረታዊያን። አዲስ አበባ። ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር። (1980 ዓ.ም)። መጽሐፍ ቅዱስ። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል። (1993 ዓ.ም) ። አማርኛ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ። አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ያለው እንዳወቀ። (2004 ዓ.ም) ። የምርመር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ይትረፍ አየለ። (20012) ። የሰነ ብዕና አገነባብ በደብረታቦር ከተማና አካባቢው ሀገረሰባዊ የልጆች ጨዋታ ማሳያነት። ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ።

ዮሐንስ ታደሰ። (1986 ዓ.ም) ። "የቡሄ አከባበር እና ግጥሞች በአርሲ ነገሌ"። ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

ደስታ ተክለ ወልድ። (1962) ። አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት።

ግርማ ዘነበ።(2002)። የአማርኛ የልጆች ጨዋታ አይነቶች ባህርዮቻቸውና ሙያዎቻቸው። አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

ፈቃደ አዘዘ። (1991 ዓ.ም) ። የሥነ-ቃል መምሪያ። አዲስ አበባ፤ ኢትዮ ጥቁር ዓባይ አሳታሚዎች።

Abrahams, R. D. (1978). Towards a Sociological Theory of Folklore: Performing Services. Western Folklore, 37(3), 161—184. https://doi.org/10.2307/1498062

African Union. (2006). the African Youth Charter. Adopted By the Seventh Ordinary Session of the Assembly, Held in Banjul, the Gambia,

Ambretti, A. et al. (2019). Traditional Games Body and Movement. Journal of Sports Science 7 (2019) 33-37.

Bauman, Richard. (1992). Folklore, Cultural Performance, and Popular Entertainments: ACommunication-Centered Handbook. (Ed.) New York: Oxford Universit_Press.

------------------. (1975). Verbal art as performance. Vol. 77, No. 2, /Jan 1975/ PP.209- 311.

Bauman, Richard, and Briggs L, Charles. (1990). Poetics and Performance As Critical Perspectives on Language and Social Life፡ Annual Review of Anthropology New York: Vassar College.

Bascom, Wiliam R. (1954). Four Functions of Folklore.The Journal of American Folklore, Vol.67, No.266. (Oct. - Dec., 1954), pp. 333-349.

Ben - Amos, Dan. (1971). Toward a Definition of Folklore in Context. The Journal of American Folklore, 84 (331), 3-15. http://dx.doi.org/10.2307/539729

Campbell, M. 2017. Girls Rock! Best Practices and Challenges in Collaborative Produc-tion at Rock Camp for Girls. In: Graham, J. And Gandini, A. (Eds.). *Collaborative Production in the Creative*

*Industries.* Pp. 177—196. London: University of Westminster Press. DOI: https://doi.org/10.16997/book4.j.

Cardozo-Freeman, Inez. (1975). Games Mexican Girls Play. The Journal of American Folklore, Vol. 88, No. 347, Women and Folklore (Jan. — Mar., 1975), pp. 12-24. American Folklore Society

CSA/Central Statistics Agency. (2007). Population and Housing Census. Conducted By Central Statistic Agency of Ethiopia, Addis Ababa, Ethiopia.

Dawson, Catherine. (2002.). Practical Research Methods. United Kingdom, Oxford University Press.

Dorson, Richard (1972). Folklore and Folklife: An Introduction. Chicago; University of Chicago Press.

---------------------- (1972). Concept of Foklore and folklife studies. In Richard M.Dorson(Ed), Folklore and folklife: An Introduction (pp.1-50) Chicago: the University of Chicago press.

Dundes, Alan. (1980). "Who are the folk?" In Interpreting Folklore. Bloomington: Indiana University Press.

------------------. (1965).The study of Folklore. Englewood Cliffs: prentice-Hall.

Eichberg, H. (2015). Play, Game, Display, Sport and Democratic Self Determination . Denmark: University of Southern Denmark.

Erikson, Erik. (1959). Identity and the Life Cycle. New York: International University Press, Inc.

Finnegan, Ruth. (1992). Oral Tradition and Verbal Art. Routledage, Inc. NewYork.

______________. (1977). Oral Poetry: Its nature, significance and social Context. Cambridge, University Press.

Goldstein, Kenneth (1964). AGude for Field Workers in Folklore. American Folklore Society by Folklore Associate. Hatboro, Pennsylvania

Gray, David E.. (2004). Doing research in the real world. SAGE Publications,

London, Thousand Oaks, New Delhi.

Kapchan, Deborah A. (1995). “Performance”.The Journal of American Folklore. University of Llinois press, Vol. 108, No. 430, pp 479-508. Autumn.

Kramer, W. (2000). What is a game? December. The Games Journal/ A Magazine About Boardgames, 1-9.

Kothari, C.R. (2004). Research Methodology: Methods and Techniques. (2nd Ed). New Age International (P) Ltd, Publishers.

Kovačević and Opić: Contribution of Traditional Games to the Quality of Students’ Relations and Frequency of Students’ Socialization in Primary Education.Croatian Journal of Education, Vol.16; Sp. Ed. No.1/2014, pages: 95-112.

Magoulick, Mary. (2009). Fieldwork / Ethnography and Performance Theory.

Malinowski, Bronislaw. (1939). “The Group and the Individual in Functional Analysis”. In American Journal of Sociology, The University Of Chicago Press.

Okpewho, Isdore. (1992). African Oral Literature: Background, Character, And Continuity. Bloomington and Indianapolis, Indiana University Press.

Oring, Elliott. (1976). “Traditional Functionalism: Once More with Feeling.The Journal of American Folklore 90, no. 355: 73—76. https://doi.org/10.2307/539022.

-----------------. (1986). Folk Groups and Folklore Genres an Introduction. Utah State University Press Logan Utah.

Reinecke, Leonard. (2009). Games at Work: The Recreational Use of Computer Games during Working Hours. Hamburg Media School, University of Hamburg, Germany.

Schechner, Richard. (2002). Performance Studies: An Introduction.

Routledge. Theatre Journal, Vol. 56, No. 3, Latin American Theatre (Oct., 2004), PP, 535 — 537

Segal, R. A. (2010). Functionalism since Hempel. Method & Theory in the Study Of Religion, 22(4), 340—353. http://www.jstor.org/stable/23555754

Sims, Martha, C. and morthine Stephens. (2005). Living Folkelore: an Introduction to the Study of people and their tradition. Utah State Univeristy press.

Tucker, Elzabeth. (1948 ). Children's folklore : a handbook. London: Greenwood Press.

Vehrer, Adél. (2017). Hungarian Folk Customs and Traditions. Széchenyi István University, Gyor. https://www.researchgate.net/publication/316500727

Wetherell, W. D. (1998). Watching Girls Play. The Georgia Review, summer 1998, Vol. 52, No. 2, pp. 249-264. Georgia Review.

Winick, Stephen and Bartis, Peter. (2016). Folklife and Fieldwork: An Introduction to Cultural Documentation (4th Ed). Washington, DC, Library of Congress.

# አባሪዎች

**አባሪ አንድ**

**ሀ/ ለጥናቱ መረጃ ለመሰብሰብ የተዘጋጁ መሪ/መነሻ/ ጥያቄዎች፤**

**ጠቅላላ መመሪያ፡-**

ውድ መረጃ ሰጪዎች ቀጥሎ የቀረቡት ‹‹የልጃገረዶች ጨዋታ ክዋኔና ማህበራዊ ጠቀሜታ በመርሐ ቤቴ ወረዳ›› በሚል ርዕስ ለሚደረግ ጥናት መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ጥያቄዎችን ናቸው፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች ለውይይት መነሻ እንዲሆኑ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ በቃለ ምልልሳችን ውስጥ እንደ ሁኔታው እንዲነሱ የሚፈለጉ ሌሎች ጥያቄዎች ይካተታሉ፡፡ መረጃዎች የሚሰበሰቡት ለትምህርታዊ ዓላማ ብቻ ሲሆን የሚገኙት መረጃዎች በምንም መንገድ ከዚህ ዓላማ ውጪ እንደማይውሉ ቃል እገባላችኋለሁ፡፡ ለምታደርጉልኝ ትብብር እጅግ አመሰግናለሁ፡፡

**የመረጃ ሰጪዎች ግላዊ መረጃዎች**

የመረጃ ሰጪ ሙሉ ስም ፡ --------------------------------------

ዕድሜ ፡ -----------------------------

ስራ፡ ---------------------------

ፆታ፡ ---------------------------

ሐይማኖት፡ -------------------------------------

የጋብቻ ሁኔታ፡ ---------------------------------

የትምህርት ሁኔታ፡ -----------------------------------

በአካባቢው የኖሩበት ዓመት፡ -------------------------------------

መረጃው የተሰበሰበበት ቦታ (ቀበሌ)፡-----------------------------

መረጃው የተሰበሰበበት ቀን፡ --------------------------

**መሪ የቃለ - መጠይቅ ጥያቄዎች**

1/ የጨዋታው ታሪካዊ አመጣጥ በአጭሩ ቢገልጹልን፡፡

2/ ጨዋታው ከትንሳኤ በዓል ጋር ያለው ትስስር ምንድነው?

3/ ጨዋታዉን የሚሳተፉት ሴቶች ብቻ ወይስ ወንዶችም ይሳተፋሉ? ወንዶች የሚሳተፉ ካሆነ በክዋኔው ወቅት ሚናቸው ምንድነው?

4/ የከዋኞቹ የእድሜ ሁኔታ/ከስንት እስከ ስንት የእድሜ ክልል ያሉ ልጃገረዶች በጨዋታው ይሳተፋሉ?

5/ ከክዋኔው በፊት ምን አይነት ቅድመ ዝግጅት ይደረጋል? (በአልባሳትና ጌጣጌጥ፣ በጸጉር አሰራር፣...?)

6/ የጨዋታው ክዋኔ ሂደት ምን ይመስላል? በክዋኔ ወቅት ተጫዋቾቹ ምን ያደርጋሉ?

ስንት አይነት ጨዋታ ይጫወታሉ?የዘፈኖቹ ግጥሞች ይዘት ትኩረት ምን ላይ ነው?

7/ ከክዋኔ በኋላ ምን የሚከናወን ተግባር አለ?

8/ ይህ ባህላዊ ጨዋታ ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ጥቅም/ፋይዳ ምንድነው?

9/ ለጨዋታው መከወን እየተደረጉ ያሉ መልካም ድጋፎችና ለክዋኔው ስጋት የሆኑ ችግሮች አሉ? ካሉ ምን ምን ናቸው?

## አባሪ ሁለት

### ሀ/ የጥናቱ የቃለ መጠይቅ መረጃ ሰጭዎች፤

| ተ.ቁ | ስም | ጾታ | እድሜ | አድራሻ | ስራ | የትም/ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ብርሃኑ ልብሰወርቅ | ወ | 63 | ዓለም ከተማ | የግል/ጡረታ | የመጀመሪያ ዲግሪ |
| 2 | ቀሲስ ካሳዬ አስናቀ ሰብስቤ | ወ | 37 | ዓለም ከተማ | ቀሲስ/መምህር | የመጀመሪያ ዲግሪ |
| 3 | መ/ር ዋጋዬ ማሞ | ወ | 63 | ዓለም ከተማ | መምህር/ጡረታ | የመጀመሪያ ዲግሪ |
| 4 | መላከገነት ቀሲስ ጌቱ አሸኔ | ወ | 50 | አገሪት ቁምአምባ | ቄስ | ማንበብና መጻፍ |
| 5 | መ/ር ጸጋዘአብ ተክለ ማሪያም | ወ | 38 | አፈዘዝ በርቃቶ | መምህር | ሁለተኛ ዲግሪ |
| 6 | ደረሰ ቸርነት | ወ | 53 | ግሬት | አርሶ አደር | 8ኛ ክፍል |
| 7 | ሞገስ ከበደ | ወ | 42 | አፈዘዝ በርቃቶ | አርሶ አደር | 4ኛ ክፍል |
| 8 | ስንታየሁ ገ/ኪዳን | ወ | 38 | አፈዘዝ በርቃቶ | አርሶ አደር | ማንበብና መጻፍ |
| 9 | የማሪያምወርቅ በላይሁን | ሴ | 32 | ዓለም ከተማ | የጽ/ቤት ሃላፊ | የመጀመሪያ ዲግሪ |
| 10 | ህይወት ታደሰ | ሴ | 32 | ዓለም ከተማ | የባህል ባለሙያ | የመጀመሪያ ዲግሪ |
| 11 | ፀሐይ ባዩ | ሴ | 32 | ዓለም ከተማ | የባህል ባለሙያ | የመጀመሪያ ዲግሪ |
| 12 | ወንድማገኝ | ወ | 25 | ዓለም ከተማ | ባለሙያ | የመጀመሪያ ዲግሪ |
| 13 | ቃለህይወት | ወ | 26 | ዓለም ከተማ | ባለሙያ | የመጀመሪያ ዲግሪ |
| 14 | አበበች አረጋኸኝ | ሴ | 16 | ሰባጌ ሃሮገንዳ | ተማሪ | 10ኛ ክፍል |
| 15 | መቅደስ ጌታው | ሴ | 18 | ሰባጌ ሃሮገንዳ | ተማሪ | 11 ክፍል |
| 16 | እታቱ በላይሁን | ሴ | 19 | ሃገሪት ቁምአምባ | ተማሪ | 7ኛ ክፍል |
| 17 | አየናቸው ያግሉ | ሴ | 17 | ሃገሪት ቁምአምባ | ተማሪ | 9ኛ ክፍል |
| 18 | ተናኘ ገላዉ | ሴ | 20 | አፈዘዝ በርቃቶ | ተማሪ | የዩኒቨርስቲ ተማሪ |
| 19 | አሰገደች አናጋው | ሴ | 20 | ግሬት | ተማሪ | 9ኛ ክፍል |
| 20 | ረድኤት አስፋው | ሴ | 21 | አፈዘዝ በርቃቶ | ተማሪ | የኮሌጅ ተማሪ |
| 21 | ፋኖስ አባቡ | ሴ | 22 | ሰባጌ ሃሮገንዳ | አርሶ አደር | ማንበብና መጻፍ |
| 22 | ባየች ምንቸት | ሴ | 20 | አፈዘዝ በርቃቶ | ተማሪ | የዩኒቨርስቲ ተማሪ |
| 23 | የክቴ አደላ | ሴ | 18 | ግሬት | ተማሪ | 12ኛ ክፍል |
| 24 | ሽቶ አበበ | ሴ | 52 | ግሬት | የቤት እመቤት | 3ኛ ክፍል |
| 25 | ውድነሽ ክብረት | ሴ | 50 | አፈዘዝ በርቃቶ | የቤት እመቤት | ማንበብና መጻፍ |
| 26 | አንችንአሉ እባበይ | ሴ | 40 | ሃገሪት ቁምአምባ | የቤት እመቤት | 3ኛ ክፍል |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 27 | እታለም አሳምን | ሴ | 55 | ሰባጌ ሃሮገንዳ | የቤት እመቤት | ማንበብና መጻፍ |
| 28 | ዋጋ ሲያዳልጠኝ | ወ | 18 | አፈዘዝ በርቃቶ | ተማሪ | 12ኛ ክፍል |
| 29 | አሻግሬ አለማየሁ | ወ | 18 | አፈዘዝ በርቃቶ | ተማሪ | 10ኛ ክፍል |
| 30 | አፈምርቅ አርቀው | ወ | 20 | አፈዘዝ በርቃቶ | ተማሪ | 11ኛ ክፍል |
| 31 | ጉልቻ አባቡ | ወ | 30 | ግሬት | ነጋዴ | ማንበብና መጻፍ |
| 32 | ከፈለኝ አጋጨው | ወ | 22 | ግሬት | አርሶ አደር | ማንበብና መጻፍ |

## ለ/ የጥናቱ የተተኳሪ ቡድን ውይይት መረጃ አቀባዮች፤

| ተ.ቁ | ስም | ጾታ | እድሜ | አድራሻ/ቀበሌ | ስራ | የትም/ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቡድን አንድ | | | | | | |
| 1 | አሰለፍ መንገሻ | ሴ | 40 | አፈዘዝ በርቃቶ | የቤት እመቤት | ማንበብና መጻፍ |
| 2 | እቴወይ አባቡ | ሴ | 50 | | የቤት እመቤት | ማንበብና መጻፍ |
| 3 | ፋኖስ ስጦት | ሴ | 45 | | የቤት እመቤት | ማንበብና መጻፍ |
| 4 | እናቱ ገለታ | ሴ | 35 | | የቤት እመቤት | ማንበብና መጻፍ |
| ቡድን ሁለት | | | | | | |
| 1 | ማሞ ምንልኬ | ወ | 75 | ግሬት | አርሶ አደር | ማንበብና መጻፍ |
| 2 | አበበ ወልደሚካኤል | ወ | 55 | | አርሶ አደር | 5ኛ ክፍል |
| 3 | አበረ አያሌው | ወ | 34 | | አርሶ አደር | ማንበብና መጻፍ |
| 4 | አይደንፉ ይታገሱ | ወ | 60 | | አርሶ አደር | ማንበብና መጻፍ |
| ቡድን ሶስት | | | | | | |
| 1 | አበበች ከስክስ | ሴ | 45 | አገሪት ቁም አንባ | የቤት እመቤት | ማንበብና መጻፍ |
| 2 | አዛለች ታችበሌ | ሴ | 50 | | የቤት እመቤት | ማንበብና መጻፍ |
| 3 | ድንብላል ደርቤ | ሴ | 52 | | የቤት እመቤት | 7ኛ ክፍል |
| 4 | አንጓች ተሾመ | ሴ | 46 | | የቤት እመቤት | ማንበብና መጻፍ |

## አባሪ ሶስት

## ፎቶ ግራፎች

### 1/ የቃለ መጠይቅ ማሳያ ፎቶግራፎች

### ሀ/ ከታሪክ አዋቂዎችና ከሃይማኖት አባቶች ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ



ከግራ ወደ ቀኝ አጥኝው ከአቶ ብርሃኑ ልብሰወርቅ፣ ከመምህር ዋጋዬ ማሞና ከመ/ር ጸጋዘአብ ተክለማሪያም ጋር ቃለ መጠይቅ ሲያደርግ፣
(ዓለም ከተማና አፈዘዝ ቀበሌዎች ሚያዝያ 2015 ዓ.ም)

### ለ/ ከባህልና ቱሪዝም ሃላፊና ባለሙያዎች ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ



ከግራ ወደ ቀኝ አጥኝው ከወ/ሮ የማሪያምወርቅ በላይሁን፣ ከወ/ሮ ህይወት ታደሰ እና ከወ/ሮ ጸሐይ ባዩ ጋር ቃለ መጠይቅ ሲያደርግ፣ (ዓለም ከተማ ሚያዝያ 2015 ዓ.ም)

### ሐ/ ከጨዋታው ተሳታፊ ልጃገረዶችና ወጣት ወንዶች ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ



ከግራ ወደ ቀኝ አጥኝው ከወጣት አበበች አረጋኸኝ፣ ከወጣት አፈወርቅ አርቀው፣ ከወጣት መቅደስ ጌታው ጋር ቃለ መጠይቅ ሲያደርግ፣ (አፈዘዝ ቀበሌ ሚያዝያ 2015 ዓ.ም)

መ/ ተጫውተው ካሳለፉ እናቶች ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ



ከግራ ወደ ቀኝ አጥኚው ከወ/ሮ ሽቶ አበበ፣ ከወ/ሮ ውድነሽ ክብረት እና ከወ/ሮ እታለም አሳምን ጋር ቃለ መጠይቅ ሲያደርግ፣ (ግሬትና አፈዘዝ ቀበሌዎች ሚያዝያ 2015 ዓ.ም)


## 2/ የቡድን ውይይት ማሳያ ፎቶግራፎች

ሀ/ ከአባቶች፣ ከእናቶችና ከወጣቶች ጋር የተደረገ የቡድን ውይይት



አጥኚው ከወጣቶች፣ ከአባቶችና ከእናቶች ጋር የቡድን ውይት ሲያደርግ
(ግሬት፣ አፈዘዝና አገሪት ቀበሌዎች ሚያዝያ 2015 ዓ.ም)

**አባሪ አራት**
**የትብብር ደብዳቤዎች**



የሂዩማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
☎ +251-11-123-93-00 Ext. 127/159
+251-11-123-97-02
✉ 1176

College of Humanities, Language Studies, Journalism & Communication
Department of Amharic Language, Literature and Folklore
E-mail: deall@ls.aau.edu.et
http://www.aau.edu.et/index.php/ethiopian-languages-and-literature


ቀን፡- 15/07/2015ዓ

ለ [illegible]

ጉዳዩ፡- ትብብር ይመለከታል

የክፍል ትምህርታችን የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር ተማሪ [illegible] በሚል ርዕስ ጥናታዊ ጹሑፍ በማዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡ ስለዚህ ጥናታቸውን አጠናቀው ለማቅረብ የሚያስችላቸውን አስፈላጊውን መረጃ በመለገስ ረገድ ትብብራችሁን እየጠየቅን ለሚደረግላቸው ሁሉ በቅድሚያ እናመሰግናለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ግርማ ገበሬ (ዶ/ር)
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ሊቀመንበር

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ADDIS ABABA UNIVERSITY

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
+251-11-123-98-00 Ext. 127/159
+251-11-123-97-02
1176

College of Humanities, Language Studies, Journalism & Communication
Department of Amharic Language, Literature and Folklore
E-mail: dcdl@ils.aau.edu.et

http://www.aau.edu.et/index.php/ethiopian-languages-and-literature

ቀን፡- 15/07/2015 ዓ.ም

ለ- [illegible]


ጉዳዩ፡- ትብብር ይመለከታል

የክፍለ ትምህርታችን የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር ተማሪ [illegible] [illegible] በሚል ርዕስ ጥናታዊ ጹሑፍ በማዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡ ስለዚህ ጥናታቸውን አጠናቀው ለማቅረብ የሚያስችላቸውን አስፈላጊውን መረጃ በመለገስ ረገድ ትብብራችሁን እየጠየቅን ለሚደረግላቸው ሁሉ በቅድሚያ እናመሰግናለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ADDIS ABABA UNIVERSITY
College of Humanities, Language Studies, Journalism & Communication
Department of Amharic Language, Literature & Folklore

ግርማ ገብሬ (...
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ሊቀመንበር



ቁጥር ባ/ቱ/ ዓጠ/42 /855/15

ቀን 02/08/2015 ዓ.ም

ለ----------------------------ቀበሌ አስተዳደር

<u>ባሉበት</u>

**ጉዳዩ፡- <u>መረጃ የሚሰጡ አካላትን ማዘጋጀት ይመለከታል</u>**

ከላይ በርዕሱ ለመግለፅ እንደተሞከረው የመርሐቤቴ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ፅ/ቤት የወረዳውን ባህል ታሪክ በማጥናት ለተለያዩ አካላት ያስተዋውቃል፡፡ ስለሆነም በዘንድሮው ዓመት እንደሻደይና አሸንዳ የፋሲካ ጨዋታችን ተመርጦ ሊጠናና ሊተዋወቅ ስለሆነ ወደ ቀበሌያችሁ ----------- ቀን ከአድስ አበባ ዩንቨርስቲ ፣ ከደ/ብርሐን ዩንቨርስቲ እና ከፌደራል ባህልና ቱሪዝም ሚንስተር አጥኒ ምሁራን በማምጣት በቀበሌያችሁ ባህላዊ ክዋኔ ላይ በመገኘት ስለሚያጠኑ ለሙህራኑ ሰዎች መረጃ የሚሰጡ የቀበሌውን ባህል እሴት ታሪክ የሚያውቁ

1. 6 ወጣት ወንዶች
2. 6 የፋሲካ ጨዋታ ተጫውተው ያለፉ እናቶች
3. 3 ታሪክና ባህል አዋቂ አባቶች
4. 3 ታሪክና ባህል አዋቂ የሐይማኖት አባቶች
5. ስለተለያዩ ጉዳዮች ገለፃ የሚያደርጉ 9 ወጣት ሴቶችና 3 ወንዶች በጠቅላል 30 ሰዎችን በማዘጋጀት ለታሪካዊ ስራው ያላችሁን ድርሻ እንዲትወጡ በማለት በአክብሮት እንገልፃለን፡፡

" ከሰላምታ ጋር !!

የማርያምወርቅ በላይሁን

የመርሀቤቴ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃላፊ

<u>ማሳሳቢያ</u> ፡- አጥኝዎቹ (ምሁራኖቹ) ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ብዙ ወጭ በማውጣት ጊዜያቸውን ገንዘባቸውን ማህበራዊ ጉዳያቸውን ትተው ስለሆነ የሚመጡት መዝረክረክና ክፍተት እንዳይኖር አደራ ፡፡

ቁጥር ሰሸባቱ/መ-2064-/2015

ቀን 25/07/15 ዓ.ም

ለመርሐቤቴ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ፅ/ቤት

ለመርሐቤቴ ወረዳ አስተዳደር ፅ/ቤት

ለመርሐቤቴ ወረዳ መንግስት ኮሚኒኬሽን ፅ/ቤት

ዓለምከተማ

ጉዳዩ ፡- ትብብር እንዲደረግላቸው ስለመግለፅ

በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የፎክለርና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል ተማሪ የሆኑት አቶ ታደሰ አዳነ ትኩ ‹‹የልጅ አገረዶች ጨዋታ ክዋኔ እና ማህበራዊ ፋይዳ›› በሚል ርዕስ ጥናታቸው በማጥናት ላይ ይገኛሉ፡፡

ስለሆነም ጥናታቸውን እስኪያጠናቀቁ ድረስ በእናንተ በኩል አስፈላጊውን ትብብር እንድታደርጉላቸው እንጠይቃለን፡፡

"አዲስ እሳቤ ለቱሪዝም"

ብዙ በቀለ ወልደየስ

የሰሜን ሸዋ ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ኃላፊ

Tell number 0116814694 011 681 18 90 011 637 50 08
Email address north shewa culture tourism@gmail.come Fax 011 637 50 46